"አባቴን የገደልከው ለዚሁ አይደል!" ሲል ጩኸ ተናገረ ገብሩ።

"እንደዚያ አሰብክ? እንደዚያ አሰብክ ገብሩ? እንደዚያ አሰብክ?" አለ ደምመላሽ እንባ እየተናነቀው። ጥሩ ነው። ባይወልደኝም፣ አባቴ ነው። አባትህን አውቀህ ገደልክ ነው የምትለኝ? ገብሩ ከልጅነት ጀምሮ እንደወላጅ አባት፣ ከማንኛችሁም አስበልጦ ያሳደገኝን አባቴን ገደልከው አልከኝ?" አለ፣ ብሶት ባንኮታኮተው ድምጽ።

"አዎ አውቀህ ነው የገደልከው! ተሳካልህ! ቤተዘመድ በሙሉ ንብረቱን እንድታስተዳድርና እንድትበላ ስልጣን ሰጠህ! ያሰብከው ይሄ ነበር ተሳካልህ!" ሲል ጮኸ ገብሩ።

ደምመላሽ ምንም ሳይናገር አልጋው ላይ ተቀመጠና አንገቱን አቀረቀረ። "እሺ ጥሩ። ገብሩ እኔን ባታውቀኝ ነው። እኔ በላቤ፣ በጉልበቴ ደክሜ መኖር የምፈልግ ሰው ነኝ። በሰው ላብ፣ ሰው ደክሞ ባፈራው ሀብት ውርስ መኖር እንደማልፈልግ፣ ባለማወቅህ ነው፣ የልቤን ባለመረዳትህ ነው። ከቀናት በኋላ ታየኛለህ። ትንሽ ታገስ። ይህ ቁስል እስኪድንልኝ ድረስ ታገሰኝ። እኔ ከዚች ቤት ሰባራ ሣንቲም አልፈልግም። ሁሉም ለአንተ ይሆናል። እስከዚያ፣ በፈጠረህ አምላክ አባቴን ገደልክ አትበለኝ። ከምንም አብልጬ የምወደውን አባቴን ገደልከው አትበለኝ።"

ድንገት በሩ ተከፈተ። ሽታዬ ተንደርድራ ገባች። ከኋላዋ ዩኒፎርም የለበሱ ሁለት ፖሊሶች ተከትለዋት ገቡ። "ይኸው። እኔን በመደብደቡ ብቻ ሳይሆን፣ በነፍስ ገዳይነትም የሚጠየቅ ሰው ነው።"

ፖሊሶቹ ገብሩን ይዘውት ወጡ።

## 33

ከቀኑ አሥር ተኩል ሲል የእጅ ሰዓቱ ነገረው። የሲሳይ መምጫ ጊዜ ደርሷል። እስካሁን ግን ብቅ አላለችም። ግርማ በቀጠሮው ቦታ ቀደም ብሎ በመገኘት ሲጠብቅ አሥራ አምስት ደቂቃዎች አልፈዋል።

ከንግሥት ጋር የነበረውን የፍቅር ግንኙነት ካቋረጠ በኋላ፣ ሲሳይን በግንባር አግኝቶ የተነጋገሩበት ጊዜ አልነበረም። ዛሬ ጠዋት ቢሮዋ ደውሎላት ሊያገኛት መፈለጉን በገለፀላት መሠረት ነው በዚህ ካፌቴሪያ ውስጥ በአሁኗ ሰዓት ለመገናኘት የተቀጣጠሩት።



ግርማ፣ ዶክተር ናትናኤል በአንድ ምሽት ከንግሥት ጋር አብረው ሳሉ መጥተው የነገሩት ነገር በጊዜው ቢያስደነግጠውም፣ ከቀናት በኋላ ችላ ብሎት ነበር። ከልጃቸው ጋር የጀመረውን ፍቅር በመጥላት፣ ዶክተር ሆን ብለው ያቀረቡት ምክንያት መስሎ ነበር የታየው። ይሁንና፣ ከንግሥት ጋር የነበረውን ግንኙነት ቆርጧል። ዶክተሩ የነገሩትን ወደ ኋላ ብሎ የንግሥትን ፍቅር መቀጠልም አልደፈረም፣ ሀኪሙ ያሉት እውነት ሊሆን ይችላል በማለት።

ሲሳይ ካፌቴሪያው ውስጥ ገባችና ግርማ ወደ ተቀመጠበት ቦታ ተጠጋች። ጠቆር ያለ ሱሪና ቀይ ሹራብ ለብሳለች። አጭር ከርዳዳ ፀጉሯ የጥድ ክርክም መስሏል። ከግርማ ጋር ጉንጭ ለጉንጭ ተሳሳሙና ተቀመጠች።

"እንደምን ነህ ግርማ?"

"ደህና። አንቺ ደህና ነሽ ?"

"ደህና ነኝ። አንተስ?"

"ደህና ነኝ።"

"ጠፋህ። "

"አዎ። ምን ጊዜ አለኝ ብለሽ ነው። ብዙ ጊዜ አዲስ አበባ አልቀመጥም።" አለና አሳላፊውን ጠራው።

"ምን ልታዘዝ?" አለ አሳላፊው።

"ለስላሳ።" አለች ሲሳይ። አሳላፊው ከሄደ በኋላ፣ "ቢሆንም፣ ስትመጣ እንኳ አላስታወስከንም።" ስትል ተናገረች።

"አዎ ፣ እዚህ ስመጣም ጊዜ የለኝም። ከፍለሀገር ቆይቼ ስመጣ ብዙ ጉዳዮች ተፈጥረው ይጠብቁኛል። እነሱን ለመፈጸም ስል ዘመድ፣ ጓደኛ እረሳለሁ።"

አሳላፊው ለስላሳውን ይዞ መጣና ከፍቶ ሄደ።

"በተረፈ ግን ደህና ነህ ?"

"ደህና ነኝ።"

ዝምታ ተፈጠረ። ሁለቱም የግል ሀሳባቸውን ማስተናገድ ጀመሩ። ሲሳይ ግርማ ስልክ ደውሎ እንዲገናኙ ቀጠሮ ካስያዛት ጊዜ ጀምሮ፣ ለምን ጉዳይ እንደተፈለገች ራሷን ስትጠይቅ ነው የዋለችው። ስለንግሥት ይሆናል ብላ ግን ገምታለች። 'ስለ ንግሥት ምን? አስታርቂኝ ብሎ ሊጠይቅ ወይስ ምን?' የሚሉት ጥያቄዎች በአእምሮዋ ውስጥ ሲመላለሱ ነው የዋሉት። ግርማም በበኩሉ 'በንግሥት ላይ ተከሰተ ስለተባለው ነገር ፣ በፊቱኑ ታውቅ ይሆን? ካላወቀችስ እንዴት

ብዬ ነው የምነግራት? ከነገርኳት በኋላስ ምን ማድረግ እንዳለባት ምንድን ነው የምመክራት? ግን ዶክተሩ የነገሩኝ ነገር ሁሉ ውሸት ቢሆንስ? ከእርሷ ጋር ያለኝን ግንኙነት እንድተው የፈጠሩት መላ ቢሆንስ? ግን እንዲህ ብለው ይዋሻሉ? ለምን አይዋሹም? ከዚህ ቀደምስ ንግሥት ፀንሳለች ብለው አልዋሹኝም?' እያለ ራሱን ሲጠይቅ ነው የቆየው።

የሲሳይ የራስ ለራስ ጥያቄዎች የተነሱት ዛሬ ቢሆኑም፣ የግርማ ግን ሰንበትበት ብለዋል። አልፎ አልፎ ቢዘነጋቸውም፣ ስለንግሥት ባስታወሰ ወይም ስለበሽታው ሲነሳ በሰማ ቁጥር ጥያቄዎቹ እንደገና ነፍስ ይዘራሉ።

"አንተ ምንም አትጠጣም እንዴ?" ስትል፣ ሲሳይ ከሀሳብ ቀሰቀሰችው።

"ቡና ጠጣሁ። ቀደም ብዬ ነበር የመጣሁት።" አለ።

ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ዝም አለች። "ዛሬ ለምንድ..." ብላ ሳትጨርስ ግርማ ተናገረ።

"ንግሥት ደህና ናት?" ሲል ጠየቀ።

"ደህና ነች። አትገናኙም እንዴ?" አለች፣ ሳቅ ብላ።

"ሳትሰሚ ቀርተሽ ነው?" አለ፣ እሱም ፈገግ ብሎ።

"ምኑን?"

"መራራቃችንን።"

ልትዋሸው አልፈለገችም። "ሰምቻለሁ።" አለች፣ ፈገግ ብላ።

"ታዲያ ምን አስጠየቀሽ?"

"ለማረጋገጥ።" አለች። ዝምታ ተፈጠረ። "ግን በምን ተጣላችሁ?" ስትል ጠየቀች።

"አልተጣላንም። ግን አንድ ችግር ተፈጥሮ ነው የተራራቅነው።"

"የምን ችግር?"

ጥያቄዋን በቀጥታ ሊመልስላት አልፈለገም። እስካሁን ካደረጉት ቃለ ምልልሶች፣ ሲሳይ ንግሥት የህዋስ ተሸካሚ መሆኗን እንዳላወቀች ተረዳ።

"እስኪ መጀመሪያ፣ ስለንግሥት ንገሪኝ። ስለጤንነቷ፣ ስላጋጠሟት ችግሮችና ስለእሷ የሰማሻቸውንና ያወቅሺውን በሙሉ ንገሪኝ።" አለ ግርማ።



"እንዴት?" አለች፣ ትንሽ ኮስተር ብላ።

"ምንም ያጋጠማት ችግር የለም?"

"እኔ እስከማውቀው ድረስ ምንም ችግር አልገጠማትም። ቢገጥማት ታጫውተኝ ነበር።" አለች፣ ግራ በመጋባት ስሜት።

"በጤንነቷ በኩልስ ያጋጠማት ችግር የለም?"

"አመመኝ ያለችበትን ጊዜ ሰምቼ አላውቅም።" አለች።

ከንግሥት ጋር ለመጨረሻ ጊዜ አብሮ በነበረበት ምሽት ዶክተር ናትናኤል የነገሩት ነገር ውሸት መሆኑን አመኑ። ከእርሷ እንዲርቅ የፈጠሩት ዘዴ መሆኑን ተገነዘበ። ባለችው አነስተኛ ገቢ ንቀውት ከርሷ ጋር ያለውን ግንኙነት እንዲቆርጥ ያደረጉ መስሎ ታየው።

"ለምን ጠየቅኸኝ?"

"አባቷ ግን ጥሩ ሰው አይደሉም። በጣም ታዝቤያቸዋለሁ። እኔና እሷን ለማለያየት በየጊዜው የፈጠሯቸውን ምክንያቶች ብትሰሚ በጣም ትጠያቸዋለሽ። እኔ ልንገርሽ ሲሳይ፣ ንግሥትን በጣም እወዳታለሁ። ጠልቼያት ወይም ንቄያት የተለየኋት ነው የመሰላት። ግን አይደለም። አባቷ ናቸው እንድሸሻት ያደረጉኝ።" አለ፣ ንዴትና ሀይል ባለው ቃና።

"እርግጥ አባቷ ከፍተኛ ቁጥጥር ያደርጉባታል። አንተን ጠልተው ሳይሆን፣ እሷ ስለፍቅር እንድታስብ አይፈልጉም። ከቤት እንድትወጣ አይፈቅዱም። አሁን አሁንማ ጭራሽ ሥራሽን ተይና ተቀመጭ እያሉ ጭቅጭቅ ጀምረዋል።" አለች ሲሳይ።

"ለምን? ልጃቸውን ሊያገቡ ፈለጉ እንዴ?"

"ያሰኛል።" አለች፣ ፈገግ ብላ። "ግን ንግሥት አስቀይማህ ችላ ያልካት መስሎኝ ነበር።"

"ለምን? ንግሥት ሰውን አታስቀይምም። ንግሥትዬ በጣም ጥሩ ልጅ ናት። አብረን በማደጋችን በደንብ አውቃታለሁ። ቂም አታውቅም። ባስቀይማት፣ በቀጥታ ትነግረኛለች። እሷ ምንም አላለችም። አባቷ ግን ሰው አይደሉም።" ብሎ ጥቂት ዝም አለ። "አንድ ቀን ቀጠሩኝና ንግሥት ፀንሳለች ብለው ዋሹኝ።"

"አዎ ሰምቼአለሁ። ንግሥት ነግራኝ ነበር።" አለች፣ ሲሳይ ቀበል አድርጋ።

"ሰምተሻል?"

"አዎ።"

"እየውልሽ እንግዲህ እኔና ንግሥት ተኛተን አናውቅም። ይህንን መጀመሪያ ጠይቀውኝ ካወቁ በኋላ ፣ መፀነሷንና ማስወረዷን ነገሩኝ። ይህ ማለት እንግዲህ፣ እኔ ንግሥትን ከሌላ ሰው ጋር ትወጪያለሽ ብዬ እንድጠላት ነው።"

"ሰምቼዋለሁ።"

"ይህ ሲገርመኝ፣ አንድ ቀን ማታ፣ ትዝ ይልሻል አንድ ለቅሶ ቤት የተገናኘን ቀን?"

"እ፣ አዎ።"

"የዚያን ቀን ማታ ከንግሥት ጋር ሌሊቱን አብረን ልናሳልፍ ወስነን ነበር። የነበርንበት ሆቴል ድረስ መጥተው ያሉኝን ብነግርሽ በጣም ታዝኚለሽ።"

"ምን አሉህ?" ብላ ጥያቄዋን እንዳነሳች፣ አንዲት ጠየም ያለች ልጅ መጥታ ሰላም አለቻት። ልጅቷ ከሄደች በኋላ፣ "አታውቃትም እንዴ ግርማ?" ስትል ጠየቀችው።

"አላውቃትም ።"

"እሷ ግን ታውቅሀለች። ከንግሥት ጋር ብዙ ጊዜ አይታሀለች። እነ ንግሥት መሥሪያ ቤት ነው የምትሠራው።"

"ልብ አላልኳትም።" አለ።

"እሺ ምን አሉህ?"

"እሳት ጎርሰው እሳት ለብሰው መጡና 'ይህቺ ልጅ ትቅርብህ ብልህ እምቢ ማለትህ ነው? የራስህ ጉዳይ። እኔ ለአንተ ብዬ ነው። ልጅቷ የኤድስ ቫይረስ አለባት። ብትጠነቀቅ ይሻላል።' አሉና አስፈራሩኝ።"

"እንዲህ አሉህ ?" አለች በመገረም።

"አዎ።"

"ሙት!"

"ሙች!"

ዶክተር ናትናኤል የልጃቸውንና የግርማን ጉድኝት ለምን እንደጠሉትና እንደዚህ ዓይነት መጥፎ ታሪክ እየፈጠሩ ግርማን ለማባረር እንደተነሱ ሊገባት አልቻለም። በልጃቸው የፍቅር ጉዳይ ላይ፣ እንደቀድሞዎቹ አባቶች፣ እጃቸውን የሚያስገቡ ሰው ናቸው ብላ ፈጽሞ አትገምትም ነበር። ሁለቱን ሰዎች ለመለያየት ከዚህ በፊት ካቀረቡት ፈጠራ ይልቅ፣ የአሁኑ እንድትጠላቸው አደረጋት።



"በጣም ቅሌታም ሰው ናቸው ማለት ነው። በልጃቸው ላይ እንዴት እንዲህ ያለ ነገር ያሟርታሉ?"

"በጣም የሚገርም ነው።" ብሎ ጥቂት ዝም አለ። "ግን አንቺ ምንም የሰማሽው ነገር የለም?"

"በፍጹም! በጣም ባለጌ ናቸው! አንተ ግን እንዴት አመንካቸው?"

"ላለማመን አልደፈርኩም። የህይወት ጉዳይ ስለሆነ ፈራሁ።"

"ነገሩስ የሚያስፈራ ነው። ግን ከንግሥት ጋር መነጋገር ነበረባችሁ።"

"እንደዚያ እንዳላደርግ ደግሞ፣ እንዳልነግራት ለመኑኝ። በዚህ በሽታ መለከፏን ካወቀች፣ ራሷን ታጠፋብኛለችና አትንገር ሲሉ ለመኑኝ። ይህ ሁኔታቸው ደግሞ፣ በጣም አሳመነኝ።"

"ዘዴያቸው ቀላል አይደለም።"

"በጣም መጥፎ ሰው ናቸው።" አለ። "እኔ ግን፣ አደውልና እነግራታለሁ።" ሲል ቀጠለ።

"ምን ብለህ?"

"ይቅርታ እጠይቃለሁ። ይቅርታውን ከተቀበለች እንቀጥላለን። "

ሲሳይ ሀሳብ አልሰጠችም። ዝም ማለቱን መረጠች።

"ጥሩ አይመስልሽም?"

"ይቅርታ መጠየቁ ጥሩ ነው።"

"ፍቅራችንን መቀጠሉስ?"

መልስ ሳትሰጥ ዝም አለች። ምን መናገር እንዳለባት አላወቀችም። ግን አንድ ሀሳብ መጥቶ ወዲያው ገላገላት። "እሱን እኔ ምን አውቃለሁ ባለቤቷ ናት የምታውቀው።" አለች።

## 34

አቶ ምስጋናው የእጅ ሰዓታቸውን አዩ። ዶክተር ናትናኤል በአሁኑ ደቂቃ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ሊገኙ እንደሚችሉ ገመቱ። ስልክ ደውለው ሊያነጋግሯቸው ፈልገዋል። ግሩምን ያዳነው የባህል መድሀኒታቸው ሽታዬ ላይ ባለመሥራቱ ስጋት አሳድሮባቸዋል። መድሀኒቱን በማግኘታቸው ሊያገኙ የነበረው ታላቅ ዝና፣ ክብርና ብዙ ብር በሽታዬ ላይ በተደረገው ሙከራ በመክሸፉ አዝነዋል።

ይሁንና ተስፋ አልቆረጡም። ለግሩምና ለሽታዬ የሰጡአቸውን መድሀኒቶች ለዶክተር ናትናኤል በማሳየት መርምረው ቁርጡን እንዲነግሯቸው ተገደው ነበር። በዚህ መሠረት፣ ዶክተር ናትናኤል ውጤቱን ዛሬ ሊነግሯቸው እንደሚችሉ ቀጠሮ ይዘውላቸዋል። ግን ዶክተሩ አቶ ምስጋናው ቤት ብቅ አላሉም። ስልክም አልደወሉም።

የስልኩን መናገሪያ አነሱና ወደ ዶክተር ናትናኤል ቤት የሚወስዷቸውን ቁጥሮች አዞሩ።

የመናሪያ ቤታቸው ስልክ እንደሚፈልጋቸው ሸዋዬ ስትነግራቸው ዶክተር ናትናኤል የሥራ ካፖርታቸውን ለብሰው በግል ክሊኒካቸው ውስጥ የሚያካሂዱትን ህክምና ለመጀመር በመጣደፍ ላይ ነበሩ።

"ማን ነኝ አለ?" ሲሉ፣ ሸዋዬን ጠየቁ።

"አቶ ምስጋናው የሚባሉ ሰው ናቸው።" አለች፣ ሸዋዬ።

ዶክተር ከምስጋናው ጋር ቀጠሮ እንደነበራቸው ዘንግተውታል። የባህል ሀኪሙ ስም ሲነሳ፣ በማስታወስ ዓይነት ትንሽ እንደመደንገጥ አሉ። ስልኩ ወደተቀመጠበት ቦታ ተጠጉ። የጥናታቸውን ውጤት ምን ብለው እንደሚናገሩ አላወቁም።

ዶክተር ናትናኤል፣ ከምስጋናው የኤድስ ቫይረስ በሽተኞችን ያድናሉ የተባሉትን መድሀኒቶች እንዲመረምሩ ከመቀበላቸው በፊት፣ በሽታዬ ደም ውስጥ ባገኙት መረጃ መሠረት፣ በራሳቸው መላምት ከመረጧቸው ሶስት እፅዋት፣ አንደኛው የፀረ ቫይረስ ባህርይ አሳይቷቸዋል። ይህ፣ ምስጋናው የተጠቀሙበት ነው ብለው የገመቱት ዕፅ፣ የኤድስ ቫይረስ ፀር የመሆን ፍንጭ ያሳየ ቢሆንም፣ ምስጋናው እንዲመረመርላቸው ከሰጡዋቸው ዕፅዋት ፍጹም የተለየ ነው። የምስጋናው መድሀኒቶች ውጤታማ አለመሆናቸውን አረጋግጠዋል። ይህንን ዜና፣ በታላቅ ጉጉትና ተስፋ ይጠብቁ ለነበረው የባህል ሀኪሙ መንገሩ እንደማርዳት መስሎ ነው የታያቸው።

"ሀሎ!" አሉ፣ ስልኩን አነሱና።

"ጤና ይስጥልኝ፣ ዶክተር።" አሉ ምስጋናው፣ ልባቸው ተንጠልጥሎ።

"ጤና ይስጥልኝ አቶ ምስጋናው! ደህና ዋሉ?"

"ደህና ነኝ። እርስዎስ?"

"ደህና ነኝ። እልፎ እልፎ ያመኛል። በተረፈ ደህና ነኝ።"

ምስጋናው ቸኩለዋል። "ዛሬ እቤት እመጣለሁ ብለውኝ ነበር።" አሉ፣ በቀጥታ ወደ ጉዳዩ እንዲገቡላቸው በመፈለግ።



"አዎ። አልቻልኩም። ትንሽ ሥራ በዝቶብኝ ነበር።" ብለው ዝም አሉ።

ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ፣ ዝምታ የስልኩን መሥመር ያዘው።

"የሰጡኝን መድሀኒቶች ጥናት አድርጌባቸው ነበር። እኔ ብቻ ሳልሆን፣ አንድ ኮሚቴ አዋቅረን በርከት ብለን ነበር የመረመርናቸው።"

"እና ውጤቱ ምን ሆነ?" ሲሉ በችኮላ ጠየቁ፣ ምስጋናው።

"አልሆነም።" አሉ ዶክተር፣ በዝቅተኛ ድምጽ።

"እንዴት?" አሉ፣ የባህል ሀኪሙ በድንጋጤ።

"ፀረ ቫይረስ ባህርይ አላገኘንባቸውም።" አሉ። ከወዲያኛው የስልክ ጫፍ ድምጽ ሲያጡ ጊዜ፣ "ግሩምንም በድጋሚ መርምረነዋል። በአካል ጤና መስሎ ቢታይም፣ ህዋሱ በደሙ ውስጥ ተገኝቷል። የሆና ሆና፣ በግሩም ላይ ታይተው የነበሩ የበሽታ ምልክቶች ጠፍተዋል። ይህንን ያደረገው የርሶ መድሀኒት በመሆኑ በርከት ያሉ ባለሙያዎች የያዘ ቡድን እንዲያጠናው ትኩረት ተሰጥቶታል። ይሄ ጥሩ ዜና መሰለኝ።" አሉ።

"እንደዚያ ከሆነ የበሽታው መድሀኒት አልተገኘም ማለት ነው?" ሲሉ ጠየቁ ምስጋናው ቅር ብሏቸው።

"አዎ። ይሁንና፣ የህዋሱ ተሸካሚዎችን ባይረዳም፣ የኤድስ በሽተኞችን ዕድሜ ሊቀጥልላቸው ይችላል። ለዚህ ነው የተመራማሪዎችን ትኩረት የሳበው። የርሶ የባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆና ጥናቱ ይቀጥላል። "

አቶ ምስጋውን የሚያስደስት ዜና ቢሆንም፣ አልረኩም። እርሳቸው ሙሉ ለሙሉ ህዋሱን የሚያጠፋ ነው ብለው የተቀበሉት ነገር በዘመናዊ የህክምና ባለሞያዎች ባለመጽደቁ ቅር ተሰኝተዋል። ስለዚህም፣ ግሩምን ካዳኑ በኋላ አብሮአቸው ከርመው የነበሩት ተስፋና ኩራት እንደጤዛ ረገፉ። በህይወታቸው ዘመን አንድ ጊዜ ያገኙት እንዲህ ያለ ትልቅ ደስታ በዶክተር ናትናኤል ያልተጠበቀ መርዶ እንደ አቧራ በነነ። የባህል ሀኪሙ ተስፋ በመቁረጥ ስሜት ውስጥ ሆነውና ብስጭታቸውን ዋጥ አድርገው ዶክተርን በመሰናበት ስልኩን ዘጉት።

# 35

ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ነው። ሲሳይ ወደ ንግሥት ቤት ለመሄድ በያዘችው ታክሲ ውስጥ ሆና በሀሳብ ተከዛለች።

በአንድ ካፌቴሪያ ውስጥ፣ እንዴ ተገናኘተው ግርማ የነገራትን ነገር፣ በጊዜው አቅልላ ነበር ያየችው። ዶክተር ልጃቸውን ከግርማ ለመለየት ያቀረቡት ምክንያት መስሎ ነበር የታያት። ይሁንና ሲውል ሲያድር፣ ነገሩ እየከነከናት መጥቷል። በተለይ፣ ንግሥት የአባቷን ፀባይ መለዋወጥ አስመልክታ የነገረቻት፣ ከፊት ለፊቷ ድቅን እያለባት፣ ግርማ የነገራትን ነገር እንድታምን አስገድዷታል። 'ንግሥት የበሽታው ተጠቂ በመሆኗ ነው እንጂ፣ ባይሆን ኖሮ፣ አባቷ በየት ወጣሽ በየት ገባሽ እያሉ አይጨቀጭቋትም ነበር። ልጃቸው ሌሎች ሰዎችን እንዳትበክልባቸው ተጨንቀው ይሆናል፣ የምትውልበትና የምታመሽበት ቦታ ሁሉ የሚከታተሏት።' አለች ለራሷ። ከዚህ በፊት በአፈወርቅ ለቅሶ ላይ መጥተው ንግሥት የት እንደሄደች የጠየቋት ጊዜ ትዝ አላት። ጥርጣሬዋን አጠናከረላት። 'አሁን እንዴት ብዬ ነግሬያት ነው ዳንኤልን የማድነው? ወይ እዳዬ!' እያለች ከራሷ ጋር ስትሟገት፣ መውረጃዋ ቦታ መድረሱን እንኳ አላወቀችም ነበር። ባለታክሲው ነው፣ በሩን ከፍቶ እንድትወርድ ያስታወሳት።

የንግሥት መኖሪያ ቤትን ግቢ አስከፍታ ገባች። ባኞ ቤት ውስጥ መሆኗ ስለተነገራት፣ መኝታ ቤቷ ውስጥ ሆና ለመጠበቅ ወደዚያው አመራች። አልጋው ላይ ጋደም አለች። ከግርጊ ተተኩሰው ለመለበስ የተዘጋጁ ልብሶች አየች። ንግሥት የምትወዳቸውና ለየት ባሉ ጊዜያት የምትለብሳቸው ናቸው። ዛሬ ከዳንኤል ጋር ቀጠሮ እንዳላት መጠርጠር አላቃታትም። ምን አልባትም፣ ምሽቱንና ሌሊቱን አብረው ለማሳለፍ አቅደው ሊሆን ይችላል፣ የሚል ግምት አደረባት። ሲሳይ በጣም ተጨነቀች። 'እባክሽ ዳንኤልን አድኚው! እባክሽ የተቻለሽን አድርጊ!' እያለ በመጮህ የሚማፀናት ስሜት ተሜናት። እንዴት አድርጋ? ከዚህ ቀደም ዳንኤልና ንግሥት ወሲባዊ ግንኙነት አድረገው እንደሆነና እንዳልሆነ የምታውቀው ነገር የለም።

በእንዲህ ያለ ጭንቀት ውስጥ ሆና አሥር ደቂቃዎች አሳለፈች– ሲሳይ።

ወዲያው የመኝታ ቤቷን በር ከፍታ ገባች፣ ንግሥት። ረጅም ፀጉሯ ተበታትኗል። ፒጃማ ለብሳለች። ፎጣ ጀርባዋ ላይ ጣል አድርጋለች።



"ሲሱ እንደምን ዋልሽ?" ጉንጯን ሰጠቻት።

ሲሳይ ከአልጋው ላይ ተነሳችና ጉንጮቿን አጋጨችላት።

"ቆየሽ እንዴ ከመጣሽ?"

"ትንሽ።" የሚል አጭር መልስ ሰጠቻትና አተኩራ አየቻት ንግሥትን። ምንም የአካል ለውጥ አላየችባትም። ክሳት የሚባል ነገር ዞር ብሎ አላያትም። ወደ ጥቁረት የሚያዘነብለው ጠይም ፊቷ ፈካ ብሎአል። ጉንጮቿ ወዛ ብለዋል። 'የኤድስ ህዋስ ተሸካሚ ምን ይመስላል?' ስትል ራሷን ጠየቀች። እንዲህ ነው ብሎ የነገራት ሰዉት አልነበራትም።

"ምነው አተኩረሽ አየሽኝ?" አለች ንግሥት፣ ሱሪዋን በፒጃማዋ ውስጥ እየለበሰች።

"አተኩሬ አየሁሽ?"

"የቆዳዬ ቀለም እስኪገፈፍ ድረስ ነዋ!" አለች፣ የወገቧን ቁልፍ እያጠበቀች። "ናፈቅሁሽ እንዴ?"

"ይመስላል? "

"እዎ።" አለች ንግሥት። ሲሳይ ምንም ሳትናገር ስትቆይ ጊዜ ሀሳብ ገባት። ሲሳይን በተጫዋችነቷ ነው የምታውቃት። 'ማውራት አይታክትሽ' ትላታለች አንዳንዴ። ዛሬ ግን ምንም ቃል የለም። 'ለምን? ይሄኔ ስንቱን ታወራ ነበር?' አለች በሀሳቧ። ወዲያው አንድ ነገር ትዝ አላት። ሲሳይን ከግርማ ጋር ትናንትና አየኋት ብላ ፣ አንድ የመሥሪያ ቤት ጓደኛዋ የነገረቻት ትውስ አላት። ለምን እንደተገናኙ ሲሳይ ደውላም ሆነ በግንባር ተገኝታ አልነገረቻትም። ይህ ሁኔታ አስገርሟታል። መጠነኛ ጥርጣሬ ሳያሳድርባትም አልቀረም። እርሷ ራሷ አንስታ ስለሁኔታው መጠየቁን አልወደደችውም።

"ንግሥትዬ?" አለች ሲሳይ።

"ወዬ?" አለች ንግሥት።

"ዳንኤል ደህና ነው?"

"ዳኒ ነፍስ! ደህና ነው።"

ምን እንደምትል ግራ ገባት ሲሳይ።

"ሲሱ ምን እንደሚሰማኝ ታውቂያለሽ?" አለች ንግሥት።

ቃላት ከአፏ ሳይወጡ፣ በግንባሯና በዓይኖቿ 'ምን?' ብላ ጠየቀቻት ሲሳይ።

"ዳኒ በፍቅሩ አቃጥሎ ሊገለኝ ነው። ቢል ብያለሁ። ቀን ቢሮ ቁጭ ብዬ ፣ ከቢሮ መልስ ቤት ሆኜና እንዲሁም ሌሊት፣ ስለዳኒ ሆኗል የማስበው። ዓይኖቼን ስጨፍንም ሆነ ስከፍት የማየው የእሱን ምስል ብቻ ነው። ሁልጊዜ ከርሱ ጋር ብውል ፣ ባመሽ ፣ ባድር፣ በጣም ነው ደስ የሚለኝ። ሲሱ ሙች! ከባድ ፍቅር ነው የያዘኝ። አንዳንዴማ ምን ይለኛል እያልኩ እየፈራሁ ነው እንጂ በየደቂቃው ደውይለት ደውይለት ይለኛል።"

ሲሳይ ዝም ብላ እየቻት። የንግሥት ይሂን ያህል ግልጽ ሆና መገኘት አስገረማት። በሌላ በኩል ደግሞ፣ እንዲህ ዓይነት ይሉኝታ አሳጥቶ የሚያናግር ፍቅር ያስያዛትን ልጅ ይቅርብሽ ብሎ መናገሩ በህይወት ላይ አስቸጋሪ ተብሎ ከሚታይ ነገር ልቆ ታያት። ቢሆንም፣ የዳንኤልን ህይወት ለማዳን ስትል ወደ ኋላ ማለት እንደሌለባት አመነች።

"ሲስዬ ፣ ዛሬ ምነው እንዲህ አፍጠሽ የምታይኝ?" አለች፣ ፈገግ ብላ።

"ዛሬ ቀጠሮ አላችሁ እንዴ?"

"አዎ! ታዲያ እንዲህ የምለባብሰው የት ለመሄድ መሰለሽ?"

ሲሳይ የእጅ ሰዓቷን አየች። "ከእንግዲህ ወዲያ? አልመሸም?"

"ይምሻ።" አለች ትከሻዋን እየሰበቀች። "ከመሸም ማደር ነው።" አለች በመቀጠል።

"ማደር?" ስትል ጠየቀች፣ ድንጋጤ ተሰምቷት።

"አዎ። ምነው?"

"አይ ምንም።" ብላ ዝም አለች። "ከዚህ በፊት አላደራችሁም?"

አንገቷን በመነቅነቅ አለማደራቸውን ተናገረች።።

"ወጥታችሁ አታውቁም?"

"በፍጹም!"

የሲሳይ ልብ ረጋ አለ። ደስታ ተሰማት። ይሁንና የፈራችው ነገር፣ ዛሬ ከመከሰቱ በፊት ማድረግ ያለባት ከብዶ ታይቷታል። "የት ነው ቀጠሯችሁ? በስንት ሰዓት?" ብላ በማከታተል ጠየቀች፣ ቀደም ብላ በቀጠሮው ቦታ በመገኘት ዳንኤልን ልታስጠነቅቀው አስባ።

"ከዚህ ነው ፒክ የሚያደርገኝ።" ብላ የእጅ ሰዓቷን አየች። አሥር ከአርባ አምስት ይላል። "አሥራ አንድ ሰዓት ላይ ይመጣል።" አለች በመቀጠል።



ሲሳይ ጭንቅ ጭንቅ አላት። ፍርሀት ፍርሀት አላት። የምታደርገው ጠፋት። ለጥቂት ሲኮንዶች ያህል ድምጿን አጥፍታ ንግሥትን አተኩራ እየችና ፣ "ንግሥትዬ ፣ ዳንኤል ይቅርብሽ። ከእርሱ ጋር ያለሽ ግንኙነት ይቅር!" ስትል፣ ሳይታወቃት ጮኸች።

ንግሥት፣ ሲሳይ የተናገረቻቸው ቃላትና በፊቷ ላይ ያየችው የስሜት መለዋወጥ አስደነገጣት። ምንም ሳትናገር ጓኛዋን ትኩር ብላ እየቻት።

"ንግሥትዬ፣ ዳንኤል የሚሆንሽ ሰው አይደለም።"

"ለምን?" አለች ግንባሯን ቅጭም አድርጋ።

"አይሆንሽም።"

"እኮ ለምን?"

"እንዲሁ።"

"እንዴት እንዲሁ?"

"ብቻ ተይው።"

"ምንድን ነው የምታወሪው?" አለች፣ ንድድ ብሏት። "ለምንድነው የማይሆነኝ?" ስትል፣ አስከትላ ጠየቀቻት።

ሲሳይ የምትመልሰው ጠፋት። ምን ትበል? እሱ ደህና ነው። ግን አንቺ አትሆኚውም። የሰው ልጅ ጠላት የሆነው ህዋስ በደምሽ ውስጥ አለ!

ይህን ሁሉ ለማለት አልደፈረችም። ብቻ በደፈናው፣ "ጥሩ ሰው አይደለም።" አለች።

"ምን አየሽበት?"

"ብቻ ሁኔታው ደስ አላለኝም።" አለች ሲሳይ፣ የምትለው ጠፍቷት።

ንግሥት ብው አለች። ሲሳይ ቀድሞ የምታውቃት ጓደኛዋ ሆና አልታየቻትም። ዳንኤልን የመሰለ፣ ሴት የምትፈልገውን ሁሉ የሚያሟላ ወንድ በማግኘቷ፣ የቀናች መስሎ ነው የታያት። ከግርግ ጋር ያደረገችው የምስጢር ግንኙነት እንድትጠረጥራት አድርጓት ነበር። ፊቱን ወደ እርሷ እንዲያዞር ያደረገችው ወዳው ነው ብላ አስባ ነበር። የአሁኑ ሁኔታ ደግሞ፣ ሲሳይ በርሷ ላይ እንደምትቀና ያረጋገጠላት መሰላት። ሁኔታው አበሳጫት። "ምንድነው አንቺ ከኔ የምትፈልጊው?" ስትል ጮኸችባት።

"ምን አፈልጋለሁ ንግሥትዬ?" ስትል ረጋ ባለ ሁኔታ ፣ ጥያቄዋን በጥያቄ መለሰችላት።

"እንጃልሽ! አላቅልሽም! ምንድን ነው እንዲህ የሚያስመቀኝ ሽ?" አለች ንግሥት። የዳንኤል በመጥፎ መነሳት አቃጥሏታል። የግንባሯ ሥሮች ተግተረተሩ። ዓይኖቿ ፈጠጡ። የምታስፈራ አውሬ መስላ ታየቻት።

"ምንድ ነው የተመቀኘሁሽ?"

"እንጃልሽ በቃ! ምንም ነገር እንዳትናገሪኝ!"

ሲሳይም ብልጭ አለባት። "ዳንኤልን ፈልጋዋለች ብለሽ ነው፣ እንዲህ የሚያመናቅርሽ?"

ንግሥት ዝም አለች። "ቆይ፣ ዳንኤልን የት አውቀሽው ነው፣ 'እሱ አይሆንሽም፣ መጥፎ ሰው፣ ትብርጥቢ።' እያልሽ የምትቀባጥሪው!" ስትል በማሾፍና በመቆጣት ተናገረች።

"አይ እንግዲህ አትሳደቢ! የእንቺን ዳንኤል ከፈለግሽ በእንቀልባ አዝለሽው ልትዞሪ ትችያለሽ!"

"ሥነ ሥርዓት ቢኖርሽ ጥሩ ነው! ድንበር ያለፍሽ መሰለኝ!"

"ባልፍስ ምን ልትሆኚ ነው?" ስትል ቆማ አፈጠጠችባት፣ ንግሥት ላይ።

"ልትሰድቢኝ ነው እንዴ ቤቴ ድረስ የመጣሽው?"

"ኸረ እኔ አላበድኩም! ልሄድልሽ ነው!" ብላ ውልቅ አለች፣ ሲሳይ። ከንግሥት መኝታ ቤት ከወጣች በኋላ፣ ስሜቷን ምን እንደለዋወጠውና የመጣችበትን ዓላማ ሳታሳካ ለምን እንደወጣች አልታወቃትም። እንደዚህ ዓይነቱን ነገር የጠበቀችው ቢሆንም፣ የዳንኤልን ህይወት ለማትረፍ ሁሉን ችላ ንግሥትን ማሳመን መቻል ነበረባት። ተመልሳ ንግሥትን ለማሳመን መሞከር የማይቻል ነገር ሆና ታያት። ከእንግዲህ ወዲያ የምታቀርባቸው ምክንያቶች በንግሥት ዘንድ ተቀባይነት እንደማይኖራቸው አውቃለች። ንግሥት ወዳ አይደለም። ዳንኤልን ከፈጣሪዋ እኩል ታመልከዋለች። ታምነዋለች። ልቧን ሰጥታዋለች። ንግሥትን ዋሽቶ ከዳንኤል እንድትርቅ የሚደረግ ሙከራ፣ ዕድሜውን ሙሉ በጾም በፀሎት ያሳለፈን ባህታዊ አምላኩን እንዲክዳ ከማድረግ የከበደ ነገር ሆኖ ነው የታያት። ስለዚህ እውነቱን አፍርጣ ነግራት ለመገላገል አሰበች። ወሰነች። ንግሥት ወደአለችበት ክፍል ስታመራ ድንገተኛ ድምጽ ከግቢ ውጭ ተሰማ።



የመኪና ጥሩንባ!

የዳንኤል መኪና መሰላት። ጥቂት ከራሷ ጋር ሙግት ካደረገች በኋላ ከቤቱ ወጣች፣ ሁኔታውን ለንግሥት ከመንገር ይልቅ ለዳንኤል መናገሩ እንደሚሻል መርጣ።

ተገኝ የግቢውን በር ከፈተ። መኪናዋ የዳንኤል ሳትሆን የዶክተር ናትናኤል ሆነች።

ሲሳይ፣ ዳንኤል አለመሆኑን ስታውቅ የቀድሞው ጭንቀቷ ተመለሰ። ይሁንና፣ አሁንም ለንግሥት ከመንገር ይልቅ ዳንኤልን እንዲያተርፉ ለዶክተር መናገሩን መረጠች። መኪናቸውን ካቆሙበት ጋራዥ ውስጥ እንዳሉ ተጠግታ ሰላምታ ካቀረበችላቸው በኋላ፣ "ዶክተር! ንግሥት የኤድስ ቫይረስ ሰለባ ሆናለች ይባላል። እውነት ነው?" ስትል ጠየቀቻቸው።

ዶክተር ናትናኤል ደንግጠው ቀሩ። ይህንን ምስጢር ከርሳቸውና ከግርማ ሌላ የሚያውቅ እንደሌለ ያምናሉ። ይሁንና፣ ሌላ ሶስተኛ ሰው አውቆ መገኘቱን ሰሙ። እንዴት? ማን ነገራት? ማን ነው እንዲያ ያለው?" ሲሉ፣ ጥያቄዋን በጥያቄ መለሱላት።

ከፊታቸው ላይ ያነበበችው ድንጋጤ ነገሩ ለርሳቸውም እንግዳ የሆነ አስመስሉ ነገራት። "ግርማ ነው የነገረኝ።"

" የቱ ግርማ?" አሉ፣ ፊታቸውን ቅጭም አድርገው።

"ግርማ ድሮ ሰፈራችሁ፣ ጎረቤታችሁ፣ የነበረው።"

"ትዝታም ነው ባክሽ! እኔ ስቀልድ ነው።" አሉ የሚናገሩት ጠፍቷቸው። የልጃቸው ምስጢር እንዲወጣ አይፈልጉም። ንግሥት ነገሩን ሰምታ በስቃይና በስጋት እንድትታኘክ አይፈልጉም። ስለዚህ መካድ እንዳለባቸው አምነዋል።

"የእሱ ቤተሰቦችና እኔ በጣም ወዳጆች ነን። ለብዙ ዓመታት አብረን በመኖራችን እንደ ሥጋ ዘመድ ነው የምንተያየው። ግርማ የንግሥቴ ወንድም መስሎ ነው የሚታየኝ። ስለዚህ ሁለቱ በፍቅር እንዲፈላለጉ አልሻም። እሱ እንዲተዋት የፈጠርኩት ምክንያት ነው፤ ውሸት ነው።"

"እውነቶን ነው ዶክተር?"

"ምን ማለትሽ ነው እውነቴን ነው።" ሲሉ ተናገሩ።

ሲሳይ በእፎይታ ተነፈሰች። "ተመስገን!" አለች ለራሷ። ተሰናብታቸው ከግቢው ወጣች።

ዶክተር በዓይኖቻቸው ተከተሏት።

# 36

ከሲሳይ ጋር የተፈጠረው አለመግባባት በስሜቷ ላይ ትልቅ ለውጥ አምጥቷል። ተበሳጭታለች። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ጀምራው የነበረውን የራስን ማስዋብ ተግባር ርግፍ አድርጋ ትታ አልጋዋ ላይ ጋደም አለች። ዓይኖቿን ኮርኒሱ ላይ ሰክታ ሲሳይን በዓይነ ህሊናዋ ትመረምራት ጀመር። 'ምንድን ነው እንዲህ የሚያደርጋት? እስኪ ቆይ ምን አገባት በእኔና በዳንኤል መሀል? ከዚህ በፊት የሌለባት ፀባይ ዛሬ ከየት መጣ? ለምንድን ነው ዳንኤልን እንድተው የፈለገችው? ምን ብታስብ ነው? ቀንታ ይሆን? መሆን አለበት! አቤት የሰው ነገር! የማምናትና የምወዳት ጓደኛዬ እንዲህ ትሁን?' እያለች ከራሷ ጋር ሙግት ጀመረች። ላነሳቻቸው ጥያቄዎች አጥጋቢና ትክክለኛ መልሶች የሰጣት ምንም ወገን አልተገኘም። ቀስ በቀስ፣ ንዴት በውስጧ እየገባ፣ የጥላቻ ነፍስ እየዘራ ሄደ።

ስሜቷ እንዲህ ተለውጦ በዳንኤል ፊት መታየት አልፈለገችም። ዛሬ ከርሱ ጋር መገናኘትና አብራ ማምሸት ወይም ማደር ጥሩ መስሎ አልታያትም። 'ስለዚህ ምን ምክንያት ፈጥሬ ልቅር? አዎ ትንሽ ስላመመኝ ከቤት መውጣት አልችልም። ተኝቼ ማሳለፍ ፈልጌያለሁ እለዋለሁ።' እያለች የራስ ከራስ ሙግት ስታደርግ፣ ድንገት የመኪና ጥሩንባ ተሰማ።

ንግሥት የአሁኑ ድምጽ፣ ከዳንኤል መኪና ጥሩንባ የተላከ መሆኑን አውቃለች። ቀደም ሲል ተሰምቶ የነበረው የአባቷ መኪና መሆኑን በማወቋ እንዳሁኑ አልተረበሸችም።

ጥሩንባው ተደገመ።

ተነስታ ወጣች። የዳንኤል 506 ፔጆ መኪና ቆማለች። ዛሬ እንደሌላ ጊዜ ሙሉ ሱፍ አልለበሰም። ነጭ ጃኬትና ጠቆር ያለ ሸሚዝ መልበሱን አየች። በሩን ከፍታ ገባችና ቁጭ አለች። እንደሌላው ጊዜ ጉንጭ ለጉንጭ ሳይሆን የከንፈር ሰላምታ አደረጉ።

"ዘገየሁ እንዴ ንግሥትዬ?" አለ፣ ፈገግ ብሎ እያያት።

"በፍጹም።" አለች፣ አፀፋዊ ፈገግታ እያሳየችው።

"እንሂዳ።"

ጥቂት ዝም አለች። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት አልጋዋ ላይ ጋደም ብላ በወሰነችው ውሳኔ ላይ መጽናት እንደማትችል አወቀች።



ስትናፍቀው የነበረውን ደቂቃ ባልሆነ ምክንያት ልታሳልፈው አልፈለገችም።

"ምነው ዝም አልሽ?"

"እንደዚህ ሆኜ ልሂድ?"

"ምን ጎደለሽ?"

"ፀጉሬ አልተበጠረም እኮ። ከባኞ እንደወጣሁ ነው የመጣኸው። ሊፕስቲክ አልተቀባሁም።" አለች።

ከእግር እስከራሷ እንደተቀመጠች እያትና፣"ምንም የጎደለሽ ነገር የለም። የከንፈር ቀለሙም ቢሆን፣ ለዛሬ የሚያስፈልግ አይደለም።" አለ፣ ፈገግ ብሎ እያያት።

"ለምን?" ብላ ከጠየቀች በኋላ ፣ ምክንያቱ ገባት።

"ብትቀቢም ከንፈሮችሽ ላይ ብዙ ጊዜ አይቆይም ብዬ ነው" አለ አሁንም፣ ፈገግ ብሎ።

ሳታስበው ከት ብላ ሳቀች። ትንሽ ቆይታ 'ምንድነው የሚያስቀኝ?' ብላ ሳትጠይቅ አልቀረችም።

"ቶሎ በያ፣ ጊዜ አትግደይ።"

"እሺ መጣሁ። አንድ ወይም ሁለት ደቂቃዎች ጠብቀኝ" አለችና ከመኪናው ውስጥ ወጥታ ወደ ግቢው ገባች።

ዳንኤል የዛሬውን ምሽትና ሌሊት ከንግሥት ጋር ለማሳለፍ ወስና ነው የመጣው። ለተወሰኑ ሰዓታት ያህል በተለያዩ የመዝናኛ ቦታዎች ውስጥ ካሳለፉ በኋላ፣ መኖሪያ ቤቱ ወስዶ ራት ሊጋብዛት አስቧል።

ንግሥት ወዲያው ተመልሳ መጣች። በእጇ ቦርሳ ይዛለች።

የመኪናውን ሞተር ለማስነሳት ቁልፉን እያዞረ፣"ዛሬ መመለስ የለም። እዚህች ቦታ የምንመጣው ነገ ጠዋት ነው። እሺ?" አሉ።

ፈገግ ብላ ፣"ማን ነው ያለው?"አለች።

"እኛ ነና፣ ሁለታችንም።"

"እኔ አላልኩም።" አለች ፈገግ ብላ ፣ በቀልድ ዓይነት።

መኪናዋ መሮጥ ጀመረች። እረፍት ያደረገችው ግዮን ሆቴል ስትደርስ ነበር። ጎን ገቡ። ለቆይታቸው ተስማሚ የመሰላቸውን ቦታ መርጠው ያዙ። ቢራ መጣላቸው። እየጠጡ ማውራት ጀመሩ።

"እንዴት ነው ቦታውን ወደድሽው?" ሲል ጨዋታ ጀመረ ዳንኤል።

ግራ ቀኙን አማተረችና፣ "አዎ። ግን ይገርምሀል፣ እዚህ ሆቴል ብዙ ጊዜ እየመጣሁ እዋኛለሁ። እዚህኛው መዝናኛ ውስጥ ግን ገብቼ አላውቅም።"

"ለምን?"

"እኔ እንጃ።"

"ዋና ትችያለሽ?"

"ትንሽ ትንሽ።"

"በጣም ጥሩ ነው።"

"አንተስ ትዋኛለህ?"

"ብዙ አልችልም። ርግጠኛ ነኝ ትበልጪኛለሽ።"

"የት አየኸኝ?" አለች ፈገግ ብላ።

"ይመስለኛል። ወደፊት አይሽ የለ?"

"እኔስ ወደፊት አይህ የለ?"

"ግን እዚህ አይደለም የምንተያየው። ሶደሬ ነው የማይሽ።"

"ደስ ይለኛል።"

"መቼ እንሂድ?"

"የት?"

"ሶደሬ።"

"ደስ ባለህ ቀን። ቅዳሜና እሁድ ከሆነ ሁልጊዜ እችላለሁ።"

"መልካም።"ዝምታ ሰፈነ።"ጠጪ።"

"እሺ።" አለችና ብርጭቆዋን አነሳች።

ዝምታ ሰፈነ።

"ዛሬ እቤት መመለስ እንደሌለብሽ እኔ ብቻ ነኝ ያልኩት?"

"እንዴት?"

"ቅድም ስለማደሩ ጉዳይ ሳነሳ ቅር ያለሽ መስሎኝ ነው።"

"ብሎኛል።" አለች ፈገግ ብላ።

"ለምን?" ሲል ጠየቀ። መልስ ሳትሰጠው ስትቀር፣"መቼም አንዳንድ ሁኔታሽ እንደሚነግረኝ ግልጽ ትመስይኛለሽ። ከአብዛኛው የአገራችን ሴቶች የምትለይ ይመስለኛል።" አለ።

"አብዛኛው የአገራችን ሴቶች ምን ይመስላሉ?" ስትል ጠየቀችው።

"በወንድና ሴት ግንኙነት ላይ ግልጽ አይደሉም። ስሜታቸውን ያፍናሉ። መኝታ ቤት እንግባ ተብለው ከሚጠየቁና እሺ



የሚል መልስ ከሚሰጡ ይልቅ ተጎትተው መግባትን ይወዳሉ። እምልሽ፣ ከቃል ይልቅ ድርጊት ይወዳሉ። ይህ ሁኔታ ደግሞ፣ ወሲባዊ ግንኙነትን መቼ እንደሚፈልጉና እንደማይፈልጉ ማወቅ አያስችልም። በሌላ በኩል ደግሞ፣ በቃላት ስምምነት ሳይኖር በድርጊት የሚደረገው ሁኔታ ስህተት ሊያመጣ ይችላል። ያልተፈለገ ርግዝናና ሥጋት ያለው የግብረሥጋ ግንኙነት ጥሩ አይደለም። በውጭው ዓለም የወሲባዊ ግንኙነትን ከተፈጥሮ እንደተሰጣቸው ታላቅ ፀጋ ቆጥረው ይጠቀሙበታል። የጋራ ርካታን ከፍ ለማድረግ ግልጽ የሆነ ውይይት ያደርጋሉ። የወሲብ ግንኙነት ርካታን እንዴት የመጨረሻው ደረጃ ላይ ማድረስ እንደሚቻል የሚመክሩ ሳይንሳዊ መጻሕፍትን በጋራ ያነባሉ። እና ይጠቀሙበታል። እኛ አገር ግን፣ በወንድና በሴት መካከል ግልጽ የሆነ የፍቅር ውይይት አይደረግም። በተለይም በእናንተ በሴቶች ላይ ግልጽነት አይታይም። እንዲያውም፣ አንዳንድ ሴቶች ወንዱን ለማስደሰት እንጂ፣ እነሱ ከተፈጥሮ የተሰጣቸው ስሜት የሌላቸው መስለው ይታያሉ።"

"ውሸት ነው። ሁሉም ሴቶች እንዲህ ዓይነት አይደሉም።"

"አውቃለሁ። ሁሉም ሴቶች እንዲህ ዓይነት አይደሉም። አብዛኛዎቹ ግን እንደዚህ ዓይነት ባህርይ ያላቸው ናቸው። አንቺ ግን አትመስይኝም።" አለ ፈገግ ብሉ እያያት።

"እኔም ያው ነኝ።"

"አይደረግም።"

"ሙት! ቆይ፣ የምትለው ሁሉ ለሴት ልጅ እኮ አስቸጋሪ ነው።" አለች በማከታተል።

"አስቸጋሪ አይደለም። መስተካከል አለበት። " አለና ቢራ እንዲደገምላቸው አሳላፊውን አዘዘ።"ንግሥትዬ፣ ዛሬ አንድ ነገር ልነግርሽ ፈልጊያለሁ። ምን አልባት ስለዚህ ጉዳይ አሁን ማንሳቱ የቸኮልኩ ያስመስለኛ ይሆናል። ግን፣ ቀደም ብዬ ማሳወቅ እንዳለብኝ፣ በእኔነቴ ውስጥ ያደረው ነገር አስገደደኝ።"

"ምንድን ነው እሱ?" ስትል ጠየቀችና ብርጭቆዋ ውስጥ ቀርቶ የነበረውን ቢራ ጨለጠች።

አሳላፊው ቢራ ይዞ መጣና ከፍቶ ሄደ።

ዳንኤል በግማሽ የተቀዳውን የቢራ ብርጭቆ ሞላና ቀና ብሉ አያት። "በጣም እንደምወድሽ ደግሜ ደጋግሜ ነግሬሻለሁ። ለአንቺ ያለኝ ፍቅር ከቀን ወደቀን እየጨመረ መጥቷል። ባልባሰት ስለ አንቺ ብዙ ነገሮች የማውቅ ይመስለኛል። እስካሁን ካየኋቸው

ሁኔታዎች፣ ከአንቺ ጋር የማንግባባበት ምንም ነገር አላየሁም። ይሄ ደግሞ ለአንድ የትዳር ጓደኛ ከሚያስፈልጉ ነገሮች ትልቁ መሰለኝ።" ብሎ ቢራውን ፉት አለ።

ንግሥት ድንገጥ አለች። ከሁለቱም ወገን ጠንከር ያለ ፍቅር መኖሩን ብታውቅም፣ ጥቂት ጊዜያት አብረን እንቆያለን ብላ እንጂ፣ እንጋባለን የሚል ሀሳብ መጥቶባት አያውቅም። ያልጠበቀችውን ርዕሰ ጉዳይ ዳንኤል ስላመጣው ስሜቷን ትንሽ ቆንጠጥ አደረገው። ይሁንና፣ ትዳር የሚለውን ቃል ዳንኤል ያነሳው፣ በትክክል ስለትዳር ለማውራት መሆኑን ተጠራጥራ፣ ተጨማሪ ማብራሪያ ከዳንኤል በመፈለግ፣ ማድመጡን ቀጠለች።

"እና ንግሥትዬ፣ ከአንቺ ጋር ያለኝ ግንኙነት በትዳር ቢታሰር ምኞቴ ነው። ይሄ የእኔ ስሜት ነው።"

ንግሥት አሁንም ልታምን አልቻለችም። ላልጠበቀችውና ላላሰበችው ጉዳይ ምን ዓይነት አስተያየት መስጠት እንደምትችል አላወቀችም። አስተያየት ቢኖራትም እንኳ፣ ማሰቢያ ቀናት ያስፈልጓታል። ትዳር ማለት አብዛኛውን የህይወት ዘመን፣ ከአንድ ጓደኛ፣ ከአንድ ፍቅረኛ ጋር አብሮ መኖር ነው። ትዳር ማለት የተለያየ ጾታ ያሏቸው ሰዎች አንድ ሀሳብ፣ አንድ እምነት ኖሮአቸው፣ በአካልና በመንፈስ አንድ ሆነው የሚኖሩበት ረጅም የህይወት ቆይታ ነው። አንድ ሰው በዚህች ዓለም ሲኖር የሚመኘው ነገር በደስታ ኖሮ ማለፍ ነው። በደስታ ለመኖር አብዛኛው የህይወት ዘመን ቆይታ፣ትዳር፣ የተቃና መሆን አለበት። በህይወት ዘመን ደስተኛ ሆኖ ለማለፍ ተገቢ የሆነ የትዳር ጓደኛ መምረጥ ያሻል። ትዳር ይህ ብቻ አይደለም። ትዳር የህይወት ምንጭ ነው። ትዳር የህይወት መተኪያ ነው። እምባያን መፍጠሪያ ነው። ብቁ ዜጋን ማፍሪያ ነው። ትዳር ሁሉም ነገር ይመስላል። እና ምርጫን ዓይኖችንና ጆሮዎችን እንዲሁም ሌሎች የስሜት ህዋሳትን አቅንቶ ማጣጣም ያስፈልጋል።

"መልሱን አሁን እንድትሰጪኝ አልሻም። ጊዜ ይኖርሻል።" አለና ቢራውን ተጎነጨ።

"እሺ።"አለች፣ ፈገግ ብላ።

ያልታሰበ ዝምታ ተፈጠረ።

ንግሥት አንዳንድ ጥያቄዎችን ልታነሳ ፈለገች። 'ትዳር ለመያዝ የሚያስፈልጉ ነገሮች እንደ መኖሪያ ቤትና የቤት ዕቃዎች መጀመሪያ ማሟላት አይኖርብንም' የሚል መጠይቅ ለማቅረብ አስባ ተወችው። ዳንኤል እነዚህን ነገሮች ማሟላት አለማሟላቱን ከእስከዛሬው ቆይታቸው የተረዳችው ነገር አልነበረም።



"ቢራውን ጠጨ። "አለ ዳንኤል የእጅ ሰዓቱን እያየ።" ሌላ ቦታ እንሂድ መሰለኝ።"

"የት?"

"ከቤት ውጭ አገልግሎት የሚሰጥበት ባር እንፈልግና መኪናችን ውስጥ ሆነን እንጫወት። አይሻልም?"

"ጥሩ።"

ሂሳብ ከፍለው ወጡ።

መኪናዋን ወደ ቦሌ መንገድ አዞረና ጉዞ ቀጠሉ። "ለቤት ትርብ የሚሆነውም እዚህ አካባቢ በሚገኙ መዝናኛ ቤቶች መስተናገድ ነው።"

"ቤትህ ወደ እዚህ ነው እንዴ?"

"እም። አልነገርኩሽም ለካ። ኤርፖርት አካባቢ ነው።"

ቀበርቾ ሬስቶራንት በር ላይ መኪናዋን አቆመ። ጊዜው መሽቷል። ለአንድ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሆኗል።

በመኪናዋ ጥሩንባ የተጠራው አሳላፊ እየሮጠ መጣ። "ምን ልታዘዝ?" አለ፣ እጆቹን ወደ ኋላ አጣምሮ ጎንበስ በማለት፣ ዳንኤልን እያየው።

"ውስኪ ደብል አድርገህ አምጣልን።" አለ ዳንኤል።

"እንዴ ዳኒ በቢራ ላይ ውስኪ ስጠጣ እሰክራለሁ። ለእኔ ቢራ ይሻለኛል። " አለች ንግሥት።

ትኩር ብሎ እያትብፈገግታ። አሁን ከተናገረቻቸው ቃላት መሀል አንዱ ልዩ ስሜት ፈጥሮበታል። ዳኒ!

"ምነው አየኸኝ?" አለች ፈገግ ብላ።

"ለምንድን ነው ግን እስከዛሬ እንዲህ ብለሽ ያልጠራሽኝ ?"

"እኔ እንጃ!" እንደማፈር እየቃጣት።

ዳንኤል ግን ምክንያቱን ያውቀዋል። ሰዎች በፍቅርም ሆነ በጓደኝነት እጅግ ሲቀራረቡና ሲዋደዱ፣ እስበውት ሳይሆን፣ መቀራረቡና መፋቀሩ በቁልምጫ እንዲጠራሩ ያደርጋቸዋል። ይህን መሰል ሀይል እንዳለ ያውቃል።

"እፍሬ ይሆናል።" አለች፣ በዓይኖቿም በጥርሶቿም እየሳቀች።

"ይልመድብሽ።"

አሳላፊው በሁለት መለኪያዎች የተቀዳ ውስኪ የአንቦውሃ ጠርሙስና በረዶ ያለበት ብርጭቆ የያዘ ትሪ ይዞ መጣ።

"እኔ ግን ቢራ ብጠጣ ይሻለኛል።" አለች፣ ዳንኤልን በመለመን ዓይነት እያየችው።

"ምን እሆናለሁ ብለሽ ነው?"

"እሰክራለሁ።"

"ምንም አትሆኚም።"

አሳላፊው በውስኪው መለኪያዎች ውስጥ እንደየፍላጎታቸው እምበውሃና በረዶ ጨምርላቸው ሄደ።

"ቺርስ!" አለች፣ የጨበጠችውን መለኪያ ከፍ አድርጋ።

"ውስኪ አፍተር ቢራ ኢዝ ጉድ በት ቢር አፍተር ውስኪ ኢዝ ባድ ይባላል።"አለ ዳንኤል።

"እኔ እሰክራለሁ ብዬ ነው ስጋቴ።"

"አንዳንዴ ብትሰክሪ ምናለ ታዲያ ?"

"ኸረ ባክህ ተው!"

"ሀይለኛ ሳይሆን መጠነኛ ስካር፣ ሞቅታ፣ ደስታ ሳይሰጥ ይቀራል?"

"የማይሆን ነገር አታውራልኝ።"

"ሙች! ንግሥትዬ ሙች! አንዳንድ ጊዜ የተወሰነ መለኪያ ወይም ጠርሙስ መጠጥ ከወሰድኩ በኋላ በማገኘው ሞቅታ የማገኘው ደስታ አለ።"

"ምን ዓይነት ደስታ?"

"የምጠላው ወይም የሚያስጨንቀኝ ነገር ካለ ረሳዋለሁ። የማየው፣ የምሰማው፣ የማደርገው እና ሰው የሚያደርገው ሁሉ ደስ ይለኛል። አንዳንዴ ይሄ አሁን የሚያስጨንቅ ነገር ሆኖ ነው የምጨነቀው? ያ የሚያናድድ ነገር ሆኖ ነው የምናደደው? ደካማ ነኝ ለካ! እያልኩ ራሴን እወቅሳለሁ። በመኖር እደሰታለሁ። ብቻ የህይወት ጥሩ ጎኗ ብቻ ነው የሚታየኝ። ታዲያ እንደዚያ ዓይነት ስሜት ሊሰጠኝ የሚችልን የመጠጥ መጠን፣ በአንድ መለኪያ ወይም ጠርሙስ ከአሳደግሁት ወይም ካሳነስኩት ይበላሻል።"

በመገረም እየችውና ሳቀች።

"ምን አሳቀሽ?"

"እስከዛሬ ስለመጠጥ መጥፎነት ሲወራ ነው ስሰማ የነበረው።"



"ዌል፣ መጠጥ በአጠቃላይ ጎጂ ነው። በመጠኑ ከተወሰደ ግን ጥቅም እንዳለው የሚናገሩ የምርምር ሰዎች አሉ። በተለይ የበላናቸውን ምግቦች ለሚፈጩ የውስጥ አካሎቻችን እገዛ ያደርጋሉ።"

"ይህንን አምናለሁ። ሌላው ጥቅም ምን እንደሆነ ግን አልገባኝም።"

"ፍልስፍና ቢጤ ስለሆነ ቶሎ አይገባም። እያደር ግን ይገባሻል።" አለ፣ ፈገግ ብሎ እያያት።

ምንም አስተያየት አልሰጠችም። አቀርቅራ ዝም አለች። ወዲያው ሳታስበው ቀኝ እጁን ትከሻዋ ላይ ጣል አደረገው። ቀና ብላ አየችው። ከንፈሮቹ ከንፈሮቿ ላይ ሲያርፉ ተሰማት።

አንድ... ሁለት... ሶስት ደቂቃዎች ተቆጠሩ - በዚህ ሁኔታ...ከተላቀቁ በኋላ ሁለቱም ግራና ቀኙን አዩ - ሰው አየን አላየን በሚል ስሜት። ትኩረት የሰጣቸው ፍጥረት አልነበረም። ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ሳይነጋገሩ አሳለፉ። ሁለቱም የየግል የልብ-ትርታቸውን ማድመጥ የያዙ ይመስላል።

"ጠጪና ወደ ቤት እንሂድ።" አለ፣ ችኮላ ባለው ቃና።

ከሁኔታቸው የተረዳችው ነገር አለ፡ እሷም ላይ ችኮላ ይታያል። ለመጨረሻ ጊዜ ከወንድ ጋር መኝታ ቤት ቆይታ ያደረገችው ከመላኩ ጋር ነው። 'ወይኔ ዓመት ሊያልፈኝ ነው?' አለች በልቧ። ገዳም የገባች ሳይመስላት አልቀረም። ከጥቂት ጊዜያት በፊት ከሻምበል አርአያ ጋር ያለውዴታዋ ያሳለፈችው ምሽት አልታወሳትም።

ከተወሰኑ ደቂቃዎች ቆይታ በኋላ፣ ዳንኤል የመኪናውን ሞተር አስነሳ። ወደ ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ የሚወስደው ዋና ጎዳና ውስጥ ገባ። የመንገዱ፣ በአካባቢው ያሉ የቤቶችና የመኪኖች መብራት ከጨለማ ጋር እየታገሉ ነው።

ላለመነጋገር የወሰኑ ይመስላሉ። ዳንኤል ፊት ለፊት የሚታየው መንገድ ላይ አተኩሯል። ንግሥት በሩን በጀርባዋ ተደግፋ ከፊት ለፊቷ ዳንኤልን ከግራና ከቀኝ ደግሞ የሚከተሏቸውንና የቀደሟቸውን መኪናዎች እያየች በዝምታ ተውጣለች። ሁለቱንም ትካዜ ውስጥ የከተታቸው በዝቅተኛ ድምጽ የተከፈተው የዶንዊልያምስ ለስላሳ ሙዚቃ ሳይሆን አይቀርም።

"ንግሥትዬ!"

"ወዬ!"

"ምንድነው የምታስቢው?"

"አንተስ ምንድነው የምታስበው?"

"መጀመሪያ ንገሪኝ።"

"መጀመሪያ አንተ ንገረኝ።"

"መጀመሪያ የጠየቅሁሽ እኔ ነኝ። አንቺኛ ንገሪኝ። ስለምንድን ነው የምታስቢው?"

"ስለአንተ!"

"አታስደስቺኝ!"

"ሙት!"

"እኔም ስለአንቺ ነበር የማስበው።"

"ይገባኛል።"

"ለምን ጠየቅሽኝ ታዲያ?"

"ለማረጋገጥ ብዬ።" ብላ ከበስተኋላ የሚከተላቸውን መኪና ድንገት ስታይ፣ ከው ብላ ቀረች። ወገቧ በመቀስ ለሁለት ክፍል ብሎ ጭንቅላቷንና እግሮቿን የያዙት አካሎቿ ግራና ቀኝ የወደቁ ነው የመሰላት። ዓይኖቿን ልታምን አልቻለችም። አፍጣ አየች። ርግጠኛ ናት። ያየችው ትክክል ነው። ቀደም ሲል እንደጭዛ ተመልክታ ነበር ግን አልጠረጠረችም።

"ዳንኤል እቤቴ መሄድ እፈልጋለሁ። እቤት ውሰደኝ።"

ዳንኤል ጆሮዎቹን ባለማመን ትኩር ብሎ አያት - በድንጋጤ።

"ዳኒ፣ በጣም ደክሞታ። ወደ ቤት መሄድ እፈልጋለሁ።"

"ለምን? ምን ሆንሽ?" አለ አሁንም፣ ግራ በተጋባ ስሜት።

"መሄድ እፈልጋለሁ። ቤቴ መግባትና ብቻዬን መሆን እፈልጋለሁ።"

"ተይ እንጂ ንግሥትዬ። አባዬና እማዬን ከሰው ጋር አስተዋውቃችኋለሁ ብዬ ነግሬያቸው እየጠበቁኝ ነው እኮ።"

"እዝናለሁ ዳኒ። ነገሩ ከአቅሜ በላይ ነው። እባክህ ቤቴ አድርሰኝ።"

የመኪናውን ፍጥነት ቀነሰና ዳር ይዞ ቆመ። "እመመሽ እንዴ ንግሥትዬ?"

"አዎ። እሞኛል።" ስትል ዋሸች።

"ምንሽን ነው ያመመሽ ?"

"አላውቀውም።"አለች፣ ቀድሞአቸው ያለፈውን መኪና በጎን እያየች።

"ታዲያ ቤት ለምን ትሄጃለሽ? ሀኪም ቤት ልውሰድሽ ?"

"በፍፁም፣ ቤቴ አድርሰኝ።"



ምንም ሳይናገር ረዘም ላሉ ሴኮንዶች አተኩሮ አያት። ገጽታዋ የነገረው ነገር አልነበረም። መኪናውን አዞረና ወደ መጡበት አቅጣጫ ተመለሱ። አልፎአቸው ሄዶ የነበረው መኪና ዞሮ መጥቶ እየተከተላቸው መሆኑን አወቀች። የባሰ አበገናት። አንጫረራት። ያለ የሌለ ርግማኗን አወረደች– በልቧ።

"ንግሥትዬ፣ የሆንሽውን ነገር ለምን አትነግሪኝም? እውነት እሞሽ ነው?"

"አዎ፣ እሞኝ ነው።"

"ታዲያ ለምን ሆስፒታል አልወስድሽም?"

"ቤቴ እታከማለሁ። "አለች።

ከዚህ በኋላ የተነጋገሩት ነገር አልነበረም፣ ቤቷ መግቢያ በር ላይ እስኪደርሱ ድረስ። በከፍተኛ ፍጥነት ሲያሽከረክራት የነበረችውን መኪና አቆመና ንግሥትን አያት።

በሩን ከፍታ ልትወጣ ስትል እጇን ያዘና ፣" ንግሥትዬ፣ እወድሻለሁ።" አለ፣ በሚያሳዝንና አንጀት በሚበላ ድምፀት።

እንባ ባቀረሩት አይኖቿ አየችው። መናገር አልቻለችም። ሳታስበው ከንፈሮቿ ከንፈሮቹን አገኟቸው። ብዙ ዓመታት ተለያይተው እንደተገናኙ እውነተኛ ፍቅረኛሞች በረሀብና በስቀቀን፣ ከንፈሮቻቸው ተቆላለፉ። ድንገት ከአቅፉ አውጥቶ እያያት፣"ንግሥትዬ የሆንሽውን አትነግሪኝም?"

"ሌላ ቀን። "ብላ፣ ዘላ ከመኪናው ወጣች።

ዳንኤል መኪናውን አዙሮ ወደ ቤቱ ጉዞ ጀመረ።

## 37

ዶክተር ናትናኤል በሩ እንደተከፈተላቸው በፍጥነት እየነዱ ወደ ጋራዣቸው አመሩ። የመኪናው በር ተገንጥሎ እስኪሰበር ድረስ አላትመው ወደ ቤት ገቡ። ውድ ጊዜያቸውን፣ ከመጠጥ ቤት ወደ መጠጥ ቤት እየተዘዋወሩ፣ ልጃቸውን ሲከታተሉ በማምሸታቸውና ልጃቸው ምክራቸውን ተቀብላ አርፋ አልቀመጥ በማለቷ ተበሳጭተዋል። ከዚህ ሌላ፣ እሳቸውን ብለው የመጡ ህሙማን እስካሁን ሲጉላሉ በመቆየታቸው ቤንዚን የተጨመረበት እሳት ሆነዋል። በህይወታቸው እንደዛሬ የተበሳጩበት ቀን ትዝ አይላቸውም። ይህ

ሁኔታቸው ደም ብዛታቸውን አስነስቶ ወደ ሞት ሳያደርሳቸው አይቀርም።

በቀጥታ ወደ ንግሥት መኝታ ቤት አመሩ። ከፍተው ገቡ።

ንግሥት በፊት ለፊቷ ጋደም ብላ ነበር። ኮቴ ስትሰማ ቀና አለች። ዓይኖቿ የእንባ ፍሬ ያረግፋሉ።

" የት ነው ያመሸሽው ? " ሲሉ፣ ጮኸው ጠየቋት።

ምንም መልስ አልሰጠቻቸውም። የእሷ ንዴት ከእሳቸው በልጦ እንደእሳተ ጎመራ ሊፈነዳ ትንሽ ነው የቀረው።

" ስሚ እንጂ ! የት አባሽ ነው ያመሸሽው ? " አሉ አሁንም፣ ካለፈው በበለጠ የጩኸት አነጋገር።

"ያመሸሁበትን እያወቅኸው ለምን ትጠይቀኛለህ ? " አለች፣ ርሷም ቆጣ ብላ።

"ከማን ጋር ነው የነበርሽው ? "

"ከፍቅረኛዬ !"አለች በድፍረት፣ ቆጣ ብላ። እልህ አኝኪታል።

ዘለው የሸሚዟን ኮሌታዎች እንደማነቅ አድርገው፣ "አንቺ ልጅ!ተይ! አርፈሽ ተቀመጭ ብዬሽ አልነበር ?... ስሚ እንጂ! " አሉ፣ ጉሮሮአቸውን በዘጋው የንዴት ቃና። እንገቷን ለቀቁት።

"አባዬ ለምንድን ነው እንዲህ የምትለኝ? እኔ ህፃን ልጅ ነኝ? ራሴን አውቃለሁ እኮ!"

"ምን ራስሽን ታውቂያለሽ! ራስሽን ብታውቂ ኖሮ መቼ እንዲህ ትሆኚ ነበር!"

"ምን ሆኜ አየኸኝ አባባ? ምን አጥፍቼ አየኸኝ ? ስምህን አስነስቼ አውቃለሁ? ንገረኝ አባባ?" አለችና በእልህ አለቀሰች።

የዶክተር ናትናኤል ልብ እንዳነሳሱ አልሆነም። መሸርሸር ጀመረ- በሀዘን። ስሜታቸው ሰከነ። ለአነሳቻቸው ጥያቄዎች በሙሉ መልስ መስጠት አልቻሉም። ንግሥትን ጊዜ አግኝተው ተቆጣጥረው፣ ገስፀው፣ ይህንን አታድርጊ ያንን አድርጊ ብለው የመከሩበት ጊዜ ባይኖርም ባለጊ አልሆነችም። እንደ አግድም አደጎቹ ተንዘላዝላ ቤተሰቧንና ራሷን ያስደበችበት ጊዜ የለም። አባቷን አክባሪ ናት።

የአባቷን መሸነፍ በማየቷም ይሁን በሌላ ንዴቷ አሻቀበ። "የቻልኩትን ያህል ተምሬ ሥራ ይዣለሁ። ራሴን ችያለሁ። ክፉና ደጉን መለየት እችላለሁ። በእኔ ላይ ክትትል ማድረግ ተገቢ ነው ወይ? እንደ ተናተኛ ባል በየት ወጣሽ ? በየት ገባሽ ?ከማን ጋር ዋልሽ?



ማለቱ ከአንድ ከተማረ አባት የሚጠበቅ ነው ? ዕድሜዬም ከሀያ በላይ ነው፣ እኔን መቆጣጠር ለምን አስፈለገ ? አባዬ !አንተ አባቴ እንጂ ባሌ አይደለህም ! አባዬ ! አትከታተለኝ ! ራሴን መገራት የሚችል አእምሮ አለኝ!"

"አውቃለሁ ንግሥትዬ። አውቃለሁ። ቢሆንም፣ ገና ወጣት ነሽ። የቤተሰብ ምክር ያስፈልግሻል። በወጣትነት ዕድሜሆችን ውስጥ የምናደርጋቸው ነገሮች ብዙ ጊዜ ችግር ላይ ይጥሉናል። "

"ምን ሆነክ አባዬ ?በዚህ ዕድሜዬ እንደ ህፃን ልጅ አትመልከተኝ።"

"አሁን ሊላውን ተይውና እኔ ያልኩሽን ስሚ !"

ድንገተኛ ዝምታ ተፈጠረ። ንግሥት አልጋዋ ላይ ተቀምጣ መሬት መሬቱን ማየት ጀመረች። እርሳቸውም እጆቻቸውን አጣምረው መሬት መሬት እያዩ ነው።

"ምን ያህል ጊዜ ሆነ ከዚህ ሰውዬ ጋር አብራችሁ ከሆናችሁ?" አሉ፣ ረጋ ባለ ስሜት።

እንደዛ ጨሶ የነበረው ስሜታቸው በአንድ ጊዜ ቀዝቅዞ፣ ይህንን ጥያቄ ያነሱበት ምክንያት ሊገባት አልቻለም። መልስ ሳትሰጥ ዝም አለች።

"አልሰማሽኝም ? "

"ሰምቻለሁ። "

"ምን ያህል ጊዜ ሆናችሁ ? "

"ብዙ ጊዜ ሆኖናል። "አለች፣ እንዳቀረቀረች።

የጊዜው መርዘም ስሜታቸውን ቆንጠጥ አደረገው፣ ተስፋቸው እንደመሟጠጥ አለ። ይሁንና፣ ስለሁኔታው ለማረጋገጥ ሌላ ጥያቄ ማንሳት አለባቸው። ቀደም ባለው ተመሳሳይ አጋጣሚ የሚያነሱላት ጥያቄ በርሷ ላይ የደረሰውን ሁኔታ የሚነገር እንዳይሆን ሲጨነቁ ነበር። አሁን ግን መጨነቁን የተው ይመስላሉ። ሊያነሱ የነበረውን ጥያቄ ግን ደፍረው አላወጡትም።

"ሁለተኛ ከዚህች ቤት እግርሽ እንዳይወጣ ! ሥራ እሄዳለሁ፣ እዚህ ቦታ እሄዳለሁ ማለት የለም! ቤት ውስጥ ምንም የጎደለ ነገር የለም ! ከዛሬ ጀምሮ ከቤት መውጣት የለም!" አሉ ሰክና የነበረው ንዴታቸው እንደገና ንሮ።

በእሳቸው ላይ የታየው ንዴትም በርሷ ላይ ተጋባ። "ይህንን በፍጹም አልቀበለውም! ራሴን መሆን እፈልጋለሁ! ሠርቼ በጉልበቴ እንጂ ዘላለም የቤተሰብ ተቀጽላ ሆኜ አልኖርም! ነፃነት እፈልጋለሁ!"

"እና ከእኔ ቁጥጥር ወጥተሽ እንደልቢ ልሁን ነው የምትይው?" አሉ በቁጣ።

"እንደዛ አላልኩም። በጉልበቴ ልኑር ነው ያልኩት!"

"አያስፈልግም። በሥራ ስም ነው እንዲህ የተንዘላዘልሽው! ከዚህ ልጅ ጋር ዳግም እንዳላይሽ !አለበለዚያ ከቤቴ ነው የማስወጣሽ!"

" አሁንስ እሱ ሳይሻለኝ አይቀርም።"

" እንዴት ባክሽ ! "

"አዎ። እንዲህ የሚያበሳጭና ነፃነት የሚነፍግ ኑሮ ከመኖር ይሻለኛል !" ስትል ጮኸች።

የዶክተሩ ፊት ተለዋወጠ። ስሜታቸውን መቆጣጠር አልቻሉም። ንግሥት ከቤት ከወጣች በሰዎች ላይ የምታደርሰው ጥፋት ምን እንደሆነ ያውቃሉ። በምክራቸው እግሯን አስረው ማስቀመጥ አልቻሉም። ያላቸው አማራጭ አንድ ብቻ ነው። እስካሁን ድረስ አምቀው የነበረውን፣ እርሳቸውና ግርማ የሚያውቁትንና ሲሳይ የጠረጠረችውን ምስጢር ለርሷ ይፋ ማድረግና የሚገጥማትን የሥነ-ልቦናና የሞራል ቁስል ማስታመም እንደሚሻል አረጋገጡ።

ሌሎች ሰዎችን ለሥቃይ ከመጋበዝ ልጃቸውን መጉዳት ይሻላል ብለዋል። እስከዛሬ ተከታተሉ። ሊያቆሟት አልቻሉም። እስከመቼ ተከታትለዋት ከወንዶች ጋር የምትመሠርተውን ግንኙነት ማስቆም ይቻላሉ ?

"ንግሥትዬ፣..." አሉ ቃላቸውን ሀዘን እያደናቀፈው።

ቀና ብላ ከማየት ሌላ ምንም አላለችም።

"ይሄን ያህል አንቺን የት ወጣሽ? የት ገባሽ ? እያልኩ የምከታተልሽ ተቸግሬ እኮ ነው። የማደርገው ጨንቆኝ ነው። አንቺ ብቸኛ ልጄ፣ የምወዳት ባለቤቴ ሰጦታ፣ እንዳትሳቀቂብኝና በሥጋት እንዳታልቅብኝ ብዬ ነው። ወድጄ አይደለም ንግሥቴ። ሁኔታውን ልነግርሽ ተገድጃለሁ። እስካሁን ለአንቺ ስል ደብቄው ቆይቻለሁ። ይህ ሁኔታ ደግሞ ሌሎችን የሚጎዳ ሆና አግኝቼዋለሁ። ሌሎችን ለማዳን ስል፣ አንቺን መጉዳት ይሻላል ብያለሁ። ንግሥቴ፣..." አሉና በተጨነቀ ስሜት ተመለከቷት።



በጉጉት አፍጣ እየቻቸው። ቶሎ አልነገሯትም። ፍራቻ አደረባት። አባቷን አንድ ያስጨነቃቸውና ሊነግሯት ያልፈለጉት ነገር እንዳለ አወቀች። "ምንድን ነው አባዬ ?"

"ንግሥቴ ፣ በደምሽ ውጥ የኤድስ ህዋስ አለ። "ሲሉ ፣ ዕንባ ባቀረሩት ዓይናቸቸው አይዋት። ወደ ህክምና ዓለም ለመግባት ሲመረቁ የገቡትን ቃለ መሀላ ሰብረው ንግሥትን አረዷት።

ሰው 'መሞትህ ነው!'የሚልን መርዶ ሲነገረው ምን ይሰማው ይሆን ?ተወልዶ፣ ድሆ፣ ዳዴ ብሎ፣ አፈር ፈጭቶ፣ ተምሮ ሥራ ይዞ ገና ረጅም ዓመታት በደስታ እኖራለሁ፣ ትዳር መሥርቼ፣ ልጆች ወልጄ፣ ኩዬ ድሬ ኸጅቼ እሞታለሁ ብሎ ሲጓጓ፣ ድንገት ከዚህች ዓለም በሞት ልትለይ ነው' ተብሎ ሲነገረው ምን ይል ይሆን? ለመሆኑ ትሞታለህ የሚልን ዜና ከመስማት ሌላ፣ በዚህች ዓለም ላይ ምን የሚያስደነግጥ ነገር አለ?

ንግሥት መናገር አልቻለችም። አልጋዋ ላይ ቁጭ እንዳለች፣ ሁለት እጆቿን በጉልበቶቿ ላይ አስደግፋ፣ ዓይኖቿን ጎልጉላ እየቻቸው አባቷን። ልቧ ብቻ ሳይሆን፣ በውስጧ የሚዟዟረው ደሟም፣ ቀጥ ያለ ይመስላል። ጠይም ፊቷ የአስከሬን ገጽ መስሏል። እነዛ የፈጠጡት ዓይኖቿ በቅጽበት የደም ዕንባ ቋጥረው፣ አፏን ለመናገር ብላ ከፈት አድርጋው ከአልጋው ላይ በዝግታ ብድግ አለች። አባቷ ደረት ላይ ልጥፍ ብላ፣ "አባባ ! እውነት ነው ወይ ! እውነት መሞቴ ነው ወይ?" ዝርግፍ ብሎ የወጣው ዕንባዋ፣ አላናግር አላት።

ዶክተር ናትናኤል እጆቻቸውን ትከሻዋ ላይ አነባበሩና ጉንጯቸውን ልጃቸው እናት ላይ አስደግፈው፣ ዓይኖቻቸውን ጨመቁ ለአንድ ብቸኛ ልጃቸው፣ እንደባለቤትና እንደ እናት ሆና ለምታማክራቸው ብቸኛ ልጃቸው፣ በህይወት ዘመናቸው ውስጥ አይተውት ወደማያውቁት የሀዘን ማጥ ውስጥ ሰጥመው ምርር ብለው አለቀሱ። ከአንድ ሥጋ፣ ከአንድ አጥንትና ከአንድ ዓይነት ደም የተፈጠሩት አባትና ልጅ፣ ህይወት ስትጨክን ለሰው ልጅ የምታቀምሰውን ሀዘን ተጋርተው፣ ለብዙ ደቂቃዎች ተቃቅፈው ሲላቀሱ ቆዩ።

ወዲያው፣ ንግሥት አየር እንዳስወጣ ፊኛ ዝልፍልፍ ብላ ከአባቷ እቅፍ ውስጥ ሾልካ ወደቀች። ዶክተር ድንጋጤ ጨብጦአቸው የሚያደርጉትን አጡ። የህክምና እውቀታቸው ንፋስ እንዳላቸው ባርኔጣ ከላያቸው በርሮ የሄደ መሰላቸው። ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል

ፍዝዝ ብለው ካዩዋት በኋላ ትኩረታቸው ሲመለስ ከመሬት ላይ አንስተው አልጋዋ ላይ አስተኝዋት። ፊቷ በዕንባና በላብ ታጥቧል። መስኮት ከፈቱ። የመኝታ ቤቱንም በር ከፍተው፣ ወደ ክሊኒካቸው ሮጡ። ህይወቷን ለመመለስ የሚረዱ፣ የህክምና መርጃ መሣሪያዎችን በሙሉ ይዘው ተመለሱ።

## 38

አባቷ ባደረጉላት ዕርዳታ በተከታዩ ቀን ራሷን መግዛት ብትችልም፣ የደረሰባትን የሞራልና የሥነ-ልቦና ጉዳት በአፋጣኝ ልትቋቋመው አልቻለችም። ከአልጋዋ ላይ ሳትነሳና 'እህህ' ስትል ከዛሬ ሌላ ሦስት ቀናት አለፉ። ይሁንና፣ ዶክተር ናትናኤል ባደረጉላት ያላሰለሰ ምክርና ማጽናናት እንደ ገና በዚህ ዓለም ላይ በተስፋ ለመኖር፣ የተቻላትን ያህል እየጣረች ነው። ከአልጋዋ ላይ ባትወርድም፣ የተደራረቡ ትራሶች ድጋፍ አድርጋ ቀና ብላ ከአባቷ ጋር እያወራች ነው።

"ንግሥቴ፣ ለዚህ በሽታ በማጥናት ላይ ያለሁት መድሀኒት፣ እስከዛሬ በአለማችን ላይ በልዩ ልዩ ሳይንቲስቶች ከተሞከሩት የመድሀኒት ዓይነቶች እጅግ ውጤታማ ነው። ደጋግሜ ነግሬሻለሁ። እንቺን ለማጽናናት መዋሸቴ አይደለም። ንግሥቴ ሙች ! እውነቴን ነው። በዚህ መድሀኒት የእንቺን ብቻ ሳይሆን፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የዓለም ህሙማንንም ህይወት ነው የማድነው። ይህ በህይወቴ ሙሉ አግኝቼው የማላውቀውን ደስታ ይሰጠኛል። ከዚህ ሌላ፣ በአለም ህብረተሰብ ዘንድ፣ ታላቅ አክብሮትና ዝና አገኛለሁ። ይህ ለእኔ ብቻ ሳይሆን፣ ለአንዷ ልጄ፣ ለአንቺ፣ እንዲሁም ለወገናቼና ለአገሬም ጭምር ነው። ይህ መድሀኒት ሲፈበረክ የማገኘው በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ፣ የአገሬ ሳይንቲስቶች ለሚያበረክቷቸው ግኝቶች ከዳር ማድረሻና ለአንቺ የወደፊት ኑሮ ማቃኛ ይሆናል። እኔ እርጅቻለሁ ። ሁሉም ያንቺ ይሆናል። ያን ጊዜ ያፈቀርሽውን ታገኝያለሽ። እመኝኝ ልጄ። አይዞሽ! በርቺ! በቅርቡ ያገኘሁትን መድሀኒት አስመልክቶ፣ ለሀገሬና ለውጭ ሀገር ጋዜጠኞች መግለጫ እሰጣለሁ። ያን ጊዜ ሁሉንም ታምኚያለሽ። " አሉ ዶክተር፣ ለስለስ ባለና በሚያሳዝን ድምጽ።"አይዞሽ ትድኛለሽ! ጥቂት ታገሽ!"አሉ በመቀጠል።

"እስከመቼ፣ አባዬ? " አለች፣ ዕንባ እየተናነቃት።



"በጣም ጥቂት ወራት ብቻ ነው የሚያስፈልጉኝ።"

ዶክተር ናትናኤል ይህንን ሁሉ ያሉት፣ ልጃቸውን ለማጽናናት ብለው ሳይሆን፣ በርግጥም የምርምራቸው ሂደት አጥጋቢ ውጤት ስላሳያቸው ነው። መጨረሻው ካማረላቸው፣ እነሳሳቸው ልብ በተስፋ የሚያሞቅ ነው።

"እስከዚያ አልሞትም?" አለች፣ በሚያሳዝንና በተሰበረ ድምፅ።

"ከእንግዲህ ወዲያ ለሚቀጥሉት አራት ወይም አምስት ዓመታት ምንም ሳትሆኚ ትቆያለሽ። እንዳች የሚያሰጋሽ ነገር የለም። እመኚኝ ። ከዚያ በፊት ትፈወሽያለሽ።"

"እሺ ። ግን ምን ያህል ነው የቀረህ ? "

"ቴዎሪውን ጨርሻለሁ ማለት እችላለሁ። ሙከራዎችን በማድረግ ላይ ነኝ። ግን ትንሽ የገንዘብ እጥረት አጋጥሞኛል። ከውጪ ሀገር ግብረ ሠናይ ድርጅቶች የገንዘብ እርዳታ የማገኝበትን ሁኔታ እያመቻቸሁ ነው። በቅርቡ አገኛለሁ።" አሉ ዶክተር።

አባቷ ስለ ገንዘብ ችግር ሲያነሱ አንድ ነገር አስታወሳት። ከሦስት ቀናት ቀደም ባሉ ጊዜያት፣ በየሴኮንዱ ብታስታውሰው የምትወደውና የሚያስደስታት ነገር ብቅ አለ።

ዳንኤል! ባለፉት ቀናት ሥጋት ውስጥ የከተታት የዳንኤል ጅምር ፍቅር ነው።

"ንግሥቴ ፣ ገንዘብ ሊሰጥህ የሚችል ሰው አለ ብለሽኝ አልነበር፣ ከዚህ በፊት?"

"አዎ!"

"ታዲያ ማግኘት እችላለሁ ሰውዬውን?"

ጥቂት አሰበች። ትክዝ ብላ ከፊት ለፊቷ ያለውን ግርግዳ እያስተዋለች፣ "እሞክራለሁ።" አለች።

"ጥሩ። ቶሎ ቢሆን መልካም ነው።"

አንገቷን በማወዛወዝ እሺታዋን ገለፀች።

ዶክተር ትንሽ ሥጋት ያዛቸው። ' የሰው ገንዘብ ተቀብዬ የምርምሬ ውጤት ከንቱ ቢሆን፣ ከየት አምጥቼ እከፍላለሁ ? ' ሲሉ በልባቸው ራሳቸውን ጠየቁ።

በአለማችን ላይ የሰውን ልጅ በመጥቀም ላይ ያሉ አዳዲስ ግኝቶች፣ በአብዛኛው የአንድ ወቅትና የጥቂት ሳይንቲስቶች ውጤቶች

አይደሉም። በአንድ ወቅት ብቅ ያሉ ሳይንቲስቶች፣ ጀምረው ያለፉት ወይም ሞክረው የከሸፈባቸው ጥረቶች መሻሻል ናቸው። በተለያዩ ጊዜያት የተፈጠሩ የብዙ ሳይንቲስቶች የድካም ፍሬዎች ናቸው። እና ፣ ዶክተር ናትናኤል በዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብቻቸውን፣ ለምርምር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችና ገንዘብ እንደልብ በማይገኝበት አጋጣሚ፣ የአለም ህዝብ የጓጓለትን መድሀኒት 'አፈጥራለሁ።' ብለው መነሳታቸው በልባቸው አንድ ፍርሀት ሳያሳድርባቸው አልቀረም። ይሁንና፣ ያለምንም አጋርና ሁኔታዎች መሟላት 'አንቱ' የሚያሰኙ ሥራዎች ሠርተው ያለፉ ጥቂት ሳይንቲስቶች መኖራቸውን ሲያስታውሱ፣ ተጽናኑ።

"እኔ ምለው አባዬ፣ የዚህ ህዋስ ተሸካሚ መሆኔን እንዴት አወቅኸው ?" ስትል እንደዋዛ ጠየቀች።

ከሀሳባቸው ድንገት ቀና አሉና፣ "አንድ ጊዜ ትዝ ይልሻል፣ እጅሽን ስለት ቆርጦት ብዙ ደም አልፈሰሰሽም?"

ንግሥት አስታወሰች። አንገቷን በመነቅነቅ አዎንታዋን ገለፀች።

"ያን ጊዜ ነው፣ ምን እንደገፋፋኝ አላውቅም፣ ደምሽን ወስጄ የመረመርኩት። ያን ካወቅሁ በኋላ ነው፣ ሌሎች ሰዎችን እንዳታበላሺ ክትትል ያደረግሁት።"

መርዶውን ከነገሯት በኋላ፣ ለምን ይከታተሏት እንደነበረ አውቃለች። ግን እስካሁን ያልተመለሰላት አንድ ጥያቄ አለ። ስለዚህም፣ ራሷ እንጂ፣ ዶክተር የሚያውቁት ነገር የለም። በሽታውን ማን ነው ያስያዛት ? በህይወቷ የምታውቃቸው ወንዶች ሁለት ናቸው። አንዱ ለአራት ዓመታት በፍቅረኛነት የያዘችው መላኩ ነው። በእርሱ ነው የግብረ ሥጋ ግንኙነትን ጣዕም ልትረዳ የቻለችው። ከርሱ ጋር ከተለያየች ሁለት ዓመታት አይሞላም። ከዚያ ሌላ ወንድ ያየችው ያንን አረመኔ ብቻ ነው-ሻምበል እርአያን። በበሽታው ያስለከፋት ሰው ከሁለቱ አንዱ መሆኑን አልተጠራጠረችም።

የእርሷ ጥያቄ ድንገት የዶክተር ናትናኤልም ሆኖ ተገኘ። "እኔ ምልሽ ንግሥቴ፣... "ብለው ዝም አሉ።" በዚህ በሽታ ያስያዘሽን ሰው ታውቂዋለሽ ?" ሲሉ ጠየቋት።

ጥቂት ሴኮንዶች ያህል ዝም ብላ፣ በትካዜ ከፊት ለፊቷ ያለውን ግርግዳ ተመለከተች።



" ካወቅሽው፣ ሌሎች ሰዎችን እንዳያበላሽ ቶሎ ለማስቆም ነው።"

" የህዋሱ ተሸካሚ መሆኔን ካወቅኸው ስንት ጊዜ ሆኗል?" ስትል ጠየቀች። ጥቂት አሰቡና ነገሯት።

አሁን ማን እንደሆነ ተረዳች። እዚህ ማጥ ውስጥ የከተታትን ዲያቢሎስ ለየች። መላኩ!" መላኩ ጉታ ነው የለከፈኝ !" አለች ጮክ ብላ።

" የት ነው የሚኖረው?"

የመላኩ መኖሪያ ቤት የሚገኝበትን ቦታ በምልክት ነገረቻቸው።

" ጥሩ። አሁን ትንሽ እረፍት ውሰጂ። እኔም ወደ ጥናት ክፍሌ ልሂድ። በርታ በይ። እሺ የኔ እመቤት ?" አሉና ግንባሯ ላይ ሳሟት። የመኝታ ቤቷን በር ከፍተው ሊወጡ ሲሉ፣ ጠራቻቸው።

" አባዬ!"

" አቤት የእኔ እመቤት።" አሉ፣ የአባትነት ፍቅር ባለው አነጋገር።

"ኪኒን ስጠኝ።"

"የምን?"

"የፅንትልፍ።"

እስካሁን የከረመችው በዚሁ ክኒን ነው። ከእንግዲህ ወዲያ ግን፣ በዚህ ክኒን እንዳትጠቀም ይፈልጋሉ። ይቅርብሽ ለማለት አሰቡና የፈቀደችውን ላድርግላት ብለው፣ አምጥተው ሰጧት። "መጀመሪያ ራት ብይእ።"

"በልቻለሁ። ገበታ ሲነሳ እኮ ነው የመጣኸው።" አለች ንግሥት።

እንደነገሩ ለኮፍ አደረገችው እንጂ አልበላችም። ምግብ በሥርዓት መብላት ካቆመች ቀናት ተቆጥረዋል።

እንደገና ግንባሯን በመሳም ተሰናብተዋት ወጡ።

ንግሥት ክኒኑን ከዋጠች በኋላ፣ ጋደም አለች። እንቅልፍ ግዛት ውስጥ ከመውደቋ በፊት ግን ከእርአያ ጋር ያሳለፈችውን ምሽት አስታወሰች። አረመኔ አድራጎቱ በዓይነ ህሊናዋ ታያት። ጉልበቱን መከታ አድርጎ ያደረሰባት ግፍ፣ ትዝ አላት። ይሁንና፣ ከርሷ ጋር ባደረገው የግብር ሥጋ ግንኙነት ሳቢያ የበሽታው ተለካፊ በመሆኑ፣

ከልቧ አዘነችለት። ለህይወቱ አደጋ ላይ መውደቅ ምክንያት በመሆኗ እርሷነቷን ረገመች። ዓይኖቿ ድንገት እንባ አዘነቡ።

## 39

ከጠዋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ሆኗል። ባለፉት ጥቂት ቀናት እንዳደረጉት ዛሬም በንግሥት መኝታ ቤት ውስጥ ገብተው አይዋት። ዕንቅልፍ የማረከውን ፊቷን በእጃቸው መዳፍ ዳበስ- ዳበስ አደረጉና ግንባሯን ስመው ወጡ። ሸዋዬ ከመኝታዋ ተነስታ ቁርስ ለማዘጋጀት ጣደፍ ጣደፍ ስትል አገኟት።

"ዶክተር፣ ወዴት ነው የሚሄዱት ቁርስ ሳይበሉ?" አለች ሸዋዬ፣ ያለ ወትሮአቸው በጠዋት ለመውጣት ሲዘጋጁ አይታ።

"ጉዳይ አለኝ።"

"ቁርስ ሳይበሉ?"

"ግድየለም። ውጭ እበላለሁ። እናንተ ብሉ። ንግሥቴን እንደተለመደው አጽናኛት። እሺ? አሁን ካለፈው ጊዜ እየተሻላት መጥቷል። በተቻለ መጠን እንድትረሳው ለማድረግ ሞክሪ።"

መኪናቸውን አስነስተው ከግቢው እንደወጡ፣ ሸዋዬ ወደ ንግሥት መኝታ ቤት ገባች። አልጋዋ ላይ በጎን ተቀምጣ ቁልቁል ታያት ጀመር።

ንግሥት ዓይኖቿን ከፈት ዘጋ አደረገች።

"ንግሥትዬ፣ ንግሥት፣ አንቺ!"

ዓይኖቿን ገለጠች። "አቤት!"

"ዶክተር በጠዋት የት እንደሚሄዱ ነግረውሻል?"

"የት ሄደ?"

"እኔ እንጃ ስጠይቃቸው አልነገሩኝም። ተኚ። ቁርስ ላዘጋጅ።" ብላ ወጣች።

ንግሥት ዓይኖቿን ከደን አደረገች። ዕንቅልፏን አልጨረሰችም። ተጫጭኗታል። የአባቷ ቀደም ብሎ መውጣት ሸዋዬን ለምን እንዳስገረማት አላወቀችም። 'ግን የት ይሆን በጠዋት የሚሄደው?'ስትል ራሷን ጠየቀች። 'ማታ ነግሮኝ ነበር?ምንድን ነበር የተጫወትነው?' የነገሯት ነገር ምንም ትዝ አላላትም። ነገር ግን፣ ለዚህ ሁሉ ሥቃይ ዳረገኝ ስለምትለው፣ ስለመላኩ፣ መነጋገራቸውን



አስታወሰች። ነቃ አለች። ዓይኖቿን ሙሉ ለሙሉ ከፍታ ኮርኒሱ ላይ አሳረፈቻቸው። ንዴት፣ አልህና በቀል ስሜቷ ውስጥ ዘልቀው ገቡ። መላኩን እንዴት አድርጋ እንደምትበቀለው ሊገባት አልቻለም። ምን ማድረግ ትችላለች? ልትደበድበው? ልትገድለው? እንዴት አድርጋ?

ከአልጋዋ ላይ ድንገት ብድግ አለችና ቦርሳዋን ወደ አስቀመጠችበት ሳጥን ተጠጋች። የማስታወሻ ደብተሯን አወጣችና ሳሎን ወደተቀመጠው ስልክ አመራች። ቁጥሮች አዞረች። ከወዲያኛው ጫፍ ስልኩ ይጠራል።

ስልኩ ተነሳ። "ሀሎ!"

"የመላኩ መኖሪያ ቤት ነው?"

"አዎ!" አለ ቀጠን ያለ፣ የሴት ድምጽ።

"ላነጋግረው ፈልጌ ነበር!" አለች ፣ ንግሥት ድንገት ሳይታወቃት ጮሃ።

"ትንሽ ይጠብቁ። ወይም ትንሽ ቆይተው ይደውሉ። ማን ልበል ግን?" አለች፣ የመላኩ ባለቤት የደዋይዋ ሁኔታ ግራ አጋብቷት።

"ንግሥት እባላለሁ።"

"መልዕክት ከሆነ ላስቀምጥሎት።"

"ጉዳዩ በቀጥታ ከርሱ ጋር ነው። እሱን ነው የምፈልገው።" አለች ንግሥት።

"ግድየለም፣ ከእኔ የሚደብቀው ነገር ስለሌለ ቢነግሩኝ ያው ነው። ባለቤቱ ነኝ።" አለች የመላኩ ሚስት በማግባባት ዓይነት። በማለዳ በመደወሉ የድንጋጤ ስሜት ቀይ ክብ ፊቷን ጥላሸት አስመስሎታል።

ንግሥት 'ባለቤቱ ነኝ' የሚለውን አረፍተ ነገር ስትሰማ፣ ጠቅ አደረጋት። ማግባቱን ሳትሰማ ቀርታ ሳይሆን እርሱን በማግባቷ የበሽታው ተጠቂ በመሆኗ፣ አዝና ነው። " ለአንቺ የሚነገር አይደለም፣ የእኔ እህት።" አለች ንግሥት፣ በሀዘኔታና ለስለስ ባለ አነጋገር። ሁኔታውን ነግራ በስጋት፣ በንዴትና በሰቀቀን ልታነፍራት አትፈልግም። " ይቅርታ፣ በቀጥታ ከመላኩ ጋር ነው መነጋገር የምፈልገው። " አለች ንግሥት።

የመላኩ ባለቤት ስለሁኔታው ለማወቅ ጉጉት አደረባት። 'በጠዋት፣ የማላውቃት ሴት ከእኔ የተሰወረና ለርሱ የምትነግረው ነገር

ምን ይሆን? እኔን የሚመለከት መርዶ እንዳይሆን ብቻ' አለች በልቧ። "ይመጣል። ትንሽ ጠብ-መጣ እንዳውም... ይጠብቁ።" አለች የመላኩን መምጣት አይታ። "መላኩ፣ ስልክ ይፈልግሀል። " አለች ከጓሮ ሲመለስ አይታ።

የስልኩን መናገሪያ፣ ስልኩ የተቀመጠበት ጠረጴዛ ላይ አስቀምጣ፣ ወንበር ስባ ቁጭ አለች። ባሏ ከሚያደርገው ንግግር፣ ጉዳዩ ምን እንደሆነ ለማወቅ ፈልጋለች። መላኩ እጅግ በጣም እንደሚወዳት ታውቃለች። ከዚህ የተነሳ ምንም ነገር አይሸሽጋትም። ከንግግሩ በኋላ እንደሚነግራት ብታውቅም፣ አላስችል አላት።

መላኩ ስልኩን አነሳና ጆሮው ላይ ለጠፈው። " ሀሎ!"

ንግሥት የምትፈልገውን ሰው አገኘች። ግን ምን እንደምትል አልተዘጋጀችም። ምን ልትነግረው እንደደወለች አላወቀችም። ልቧ ንዴት ቢቋጥርም፣ ወደ በቀል የሚያደርሳትን ዘዴ አላቀደችም።

"ሀሎ !...ማን ልበል?" አለ፣ የደዋይ ድምጽ ሲጠፋበት።

"ንግሥት ነኝ።"

"ንግሥት የቷ ?" አለ፣ ትንሽ ግንባሩን ቋጠር አድርጎ።

"ንግሥት ናትናኤል።"

"አ !ንግሥት! እንደምን አለሽ ? ደህና ነሽ ? " አለ ሞቅ ባለ ፈገግታ። ወዲያው መልስ ባለማግኘቱ ትንሽ ደንገጥ ብሎ " ሀሎ!... " አለ።

" መላኩ!" እንባዋ ቀደማት።

"አቤት! ምንድን ነው ?"

የምትናገረው ጠፋት። ዝም ብላ ታለቅስ ጀመር - ስቅስቅ ብላ።

መላኩ ግራ ተጋባ። "እንዴ? ንግሥት! አንቺ! ኸረ ባክሽ የሆንሽውን ረጋ ብለሽ ንገሪኝ!"

መናገር፣ አልቻለችም።

"ማን ሞተ? ለምን ታለቅሻለሽ? ለምን አትነግሪኝም? "አለ መላኩ፣ በመጨነቅ።

ሁኔታውን ከአጠገቡ ሆና ስትከታተል የነበረችው ባለቤቱም ደነገጠች። እንደገመተችው የሞተ ሰው ያለ ነው የመሰላት። ደዋይዋ መልዕክቱን ለርሷ መንገር ያልፈለገችው፣ መርዶው የእርሷን ዘመዶች



የሚመለከት ስለሆነ መስሎ ተሰማት። የስልኩን መናገሪያ ከመላኩ ጆሮ ነጥቃ ማዳመጥ ጀመረች። ምን ብላ እንደምትጠይቅ ሊገባት አልቻለም። ' ማ ይሆን የሞተው? እናቴ? አባቴ? እህቴ? ወይስ ማን?' ሁሉንም ጥያቄዎች አሰበቻቸው እንጂ አልጠየቀችም። የደዋይዋን ለቅሶና ሳግ፣ ከማዳመጥ ሌላ ያለችው አልነበረም።

ንግሥት፣ መላኩ የሚያዳምጣት ነው የመሰላት። ቁርጡን ነግራው የሚሰማውን ስሜት ለማወቅ ወሰነች። "ኤድስ አስያዝከኝ! ከየትም ለቃቅመህ ባመጣኸው በሽታ በከልከኝ! መላኩ ገደልከኝ! ህይወቴን ቀጨህት!" አለችና አለቀሰች። ከዚህ በኋላ የምትጨምረው ነገር ምን እንደሆነ አላወቀችም። " እግዚአብሄር የሥራህን ይስጥህ! እግዜር ይይልህ" አለችና ስልኩን አላተመችው።

የመላኩ ባለቤት፣ በጆሮዋ ውስጥ ተላልፎ ለአንጎሏ መልዕክት የሰጣት ነገር ትክክል መሆኑን ተጠራጠረች። ስልኩን በዝግታ ከቦታው አስቀመጠችና ባለቤቷ ላይ አፈጠጠች። የደም ሥሮቿ ተግተረተሩ። መናገር አቃታት።

እርሱም በድንጋጤ ፈዝዞ ከማየት ሌላ ያለው አልነበረም።

"ማን ናት እሷ?" ስትል ጮኸችበት።

"ስለእሷ ነግሬሽ የለ! አንቺን ከማግባቴ በፊት የነበረች ፍቅረኛዬ ናት።" አለ፣ በፍርሀት ስሜት ተውጦ።

"እውነት ነዋ ? ነገሩ ሁሉ እውነት ነዋ !" አንገቱን አነቀችው።

ሊያስለቅቃት አልቻለም። ባለ በሌለ ሀይሏ አሽቀንጥራ ወረወረችው። እርሱ ከመታገስና ከማየት ሌላ፣ የዱላ ምላሽ አልሰጠም።

"በኤድስ አስያዝከኝ ! እኔንም ገደልከኝ ! ልጄንና እኔን ገደልከን!" ብላ ጮኸች፣ በቤቱ ውስጥ የምትይዘው የምትጨብጠው ጠፍቷት፣ በመንጎራደድ።

የተናገረችው ቃል እጅግ አስደነገጠው። መሬት ላይ እንዳለ፣ " ምን?" ሲል ዓይኖቹን አጉረጥርጦ ጠየቀ።

"በኤድስ አስያዝከን !"

" ምንድን ነው የምታወሪው?"

" ልጅቷ ያለችውን ነዋ! ልጅቷ፣ ያስያዝካት! እኔንም አስያዝከኝ ! ኡ! ኡ!" በጥርሷ ልትቦጭቀው ስትጠጋው፣ የመኖሪያ ቤቱ በር በድንገት ተንኳኳ!

"ቢቶች! ቢቶች! እንደምን አደራችሁ ?" አለ አንድ ሰውዬ። ከኋላው፣ ዶክተር ናትናኤልን አስከትሏል።

ባልና ሚስቱ ተደናግጠው፣ ቤታቸው የገቡትን ሁለት ሰዎች ተመለከቱ።

ዶክተርን ይዞ የመጣው የጎረቤታቸው ሰው፣ በሁኔታቸው ግራ ተጋብቶ ካያቸው በኋላ፣ " እሳቸው የአንተን ቤት ሲፈለጉ፣ አግኝቼ ይዣቸው መጣሁ።" አለና ዶክተርን አየ።

መላኩ በዓይንም ቢሆን ዶክተርን ያውቃቸዋል። ከንግሥት ጋር በወዳጅነት ሳሉ፣ አንድ ጊዜ በሩቅ አሳይታዋለች።

ዶክተር ናትናኤል እጃቸውን ዘረጉት "ዶክተር ናትናኤል እባላለሁ። " በማለት ራሳቸውን በማስተዋወቅ መላኩንና ባለቤቱን ጨበጡ።

ዶክተርን ይዞ የመጣው ሰው ወጣ። ከዚያ በኋላ ዶክተር ከባልና ሚስቱ ጋር ሳይነጋገሩ፣ ደቂቃዎች አለፉ።

## 40

የሚጮኸውን ስልክ አነሳች - ሸዋዬ። " ሀሎ!...."

ደዋዩ የሚፈልገው ቁጥር መሆኑን ለማረጋገጥ ጠየቀ።

" አዎ ነው።"

" ንግሥትን ፈልጌ ነበር።"

" ንግሥት..." አለችና ንግግሯን ቆረጠች። ላለፉት ጥቂት ቀናት እየደጋገመ በመደወሉ፣ ድምጹን ለይታዋለች። በደወለባቸው ቀናት ሁሉ፣ ንግሥት ዘመድ ለመጠየቅ ወደ ሌላ ክፍለ ሀገር እንደሄደች አድርጋ ነበር፣ የነገረችው። ለከፋት አልነበረም እንዲህ የመለሰችለት። ንግሥት ሰሞኑን ባለችበት ስሜት ውስጥ ሆና፣ ከሰዎች ጋር መነጋገሩ ጥሩ አይሆንም ብላ አስባ ነው። ዛሬ ግን ሁኔታዋ ሻል ያለ ስለሆነ፣ እንድታነጋግረው ለማድረግ አሰበች።

" ዛሬም አልመጣችም?"

" አይ መጥታለች።"



"ላነጋግራት እችላለሁ?"

" ይጠብቁ። " በማለት የስልኩን መናገሪያ አስቀምጣ ወደ ንግሥት መኝታ ቤት ሄደች።" ንግሥትዬ፣ ስልክ ይፈልግሻል።" አለች ሸዋዬ።

" ማነው ?" አለች፣ ዐይኖቿን በድንጋጤ ሸዋዬ ላይ ተክላ።

" እኔ እንጃ። የወንድ ድምጽ ነው።" አለች።

ንግሥት ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል ስታስብ ቆየችና በዝግታ እየተራመደች፣ ወደ ሳሎን ሄደች። ስልኩ አጠገብ ደርሳ ሳታነሳው ጥቂት ሴኮንዶች አሰበች።

" ሀሎ!"

" ንግሥትዬ?"

ወዲያው አወቀችው! ልቧ የጠረጠረው እውነት ሆነ። 'ዳኒ!' ብላ ልትጮህና ናፍቆቷን ልትገልጽ አስባ ተወችው። ዳንኤል ከእንግዲህ ወዲያ የእሷ እንደማይሆን፣ ደሟ ውስጥ ያለው ህዋስ አሳውቋታል። ደህና ሁን ዳኒ! ደህና ሁን የኔ ቆንጆ! ደህና ሁን የኔ ጌታ! እኔ ለአንተ አልሆንም የኔ ፍቅር! የምሆንህ አይደለሁም ዳኒ! እኔን ለትዳር ትሆናለች ብለህ ያሰብከው ተሳስተህ ነው፣ የኔ ጌታ !ዳኒ! ከእንግዲህ አንተያይም! !

እነዚህ ሁሉ ቃላት አእምሮዋ ውስጥ ጮኹ እንጂ፣ ከአፏ ወጥተው ዳንኤል ጆሮ ውስጥ አልገቡም።

"ንግሥት አይደለሽም?" ሲል ጠየቀ ዳንኤል፣ ድምጿ ሲጠፋ ደንግጦ።

"ነኝ ። ዳኒ ደህና ነህ ?" አለች፣ እፎይታ በሌለው ድምጽ።

"ደህና ነኝ። ምን ሆነሻል?"

"ምንም አልሆንኩም።"

"በደህና ነው እንዲህ ድምጽሽ የጠፋው? እኔ እኮ ሳልደውል ያሳለፍኩት ቀን የለም። የት ሄደሽ ነው ?"

"የትም አልሄድኩ።"

"ክፍለ ሀገር ሄድሽ አልተባለም እንዴ ?"

"ኸረ ከቤቴም ወጥቼ አላውቅ። ማነው እንዲህ ያለህ ?"

"ስሟን አላውቀውም። በደወልኩባቸው ቀናት በሙሉ ስልኩን ያነሳችው አንድ ሴት ናት። ለምንድን ነው የምትዋሸው ?"

" ትንሽ አሞኝ ስለነበር፣ እንዳታስብ ሰግታ ይሆናል።"አለች፣ ሳግ በተናነቀው ድምጽ።

"በጣም ባለጌ ናት- ሶርይ ቱ ሴይ ሶ - ብቻ በጣም ነው የሚያናድደው። ለምን ይደበቃል? ንግሥትዬ፣ አንቺስ እንዴት አስቻለሽ? መጥቼ እንድጠይቅሽ አስደውለሽ ብትነግሪኝስ? አንቺም ጥሩ አልሰራሽም። ልክ ነው የሠራሽው?"

መልስ አልሰጠችም።

"ልክ አይደለም። አይደል?"

"አዎ!"

"ምን ያህል እንደናፈቅሽኝ ታውቂያለሽ ? ሰሞኑን ያለሁበት ሁኔታ የጤንነት እኮ አይደለም። ንግሥትዬ፣ አሁን ተሽሎሻል?"

"እየተሻለኝ ነው።" አለች፣ ቅሬታ ባዘለ ድምጽ።

"ዛሬ መገናኘት እንችላለን?"

ድምጿ ጠፋ። ምን ትመልስ? በምን ምክንያት ትሸሸው? ሁለቱን እንደ አንድ ሰው ያስተሳሰራቸውን እውነተኛ የፍቅር ገመድ እንዴት ትቁረጥ? አልቻለችም።

"ከቤት መውጣት ካልቻልሽ እኔ ልመጣ እችላለሁ። ቤታችሁ አካባቢ ነው ያለሁት። እመጣጤ፣ በቀጥታ እቤት ገብቼ ልጠይቅ ነበር። ግን ደፍሬ መግባት ስላልቻልኩ ነው የደወልኩልሽ። ልምጣና ልይሽ ?"

"እሺ። "አለች ረጋ ባለ ድምጽ። ከዚህ ሌላ የምትለው አልነበራትም። የብሶቷ፣ የጭንቀቷና የስሜቷ መግለጫ ሆኖ የሰነበተው ዕንባዋ፣ ዛሬም ከዓይኖቿ ውስጥ ገንፍሎ ወጣ። መኝታ ቤቷ ውስጥ ገባችና አልጋዋ ላይ በደረቷ ተኝታ፣ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች። የተመኘችውን፣ የፈለገችውን ፍቅርና ጥላ ሊሰጣት የሚችል ፍቅረኛ፣ አሳይቶ የነሳትን አምላክ አማረረች። በዚህ በሽታ ተሰቃይታ ህይወቷ እንዲያጥር ያዘጋጃትን ፈጣሪዋን ወቀሰች። ሰው መጀመሪያውኑ በዚህች ዓለም ላይ የሚኖረው ለአጭር ጊዜ ነው። ይህችኑ ጊዜ ይበልጥ ለምን እንዳሳጠረባት ጠየቀች። ይሁንና፣ መልስ አላገኘችም።

በዚህ ሁኔታ፣ ጥቂት ደቂቃዎች እንደቆየች፣ የመኝታ ቤቷ በር ተከፍቶ፣ ሸዋዬ ዳንኤልን አስከትላ ገባች። "ንግሥትዬ፣ እንግዳ ይፈልግሻል፣ ተነሺ። "ብላ ቀና ማለቷን ስታይ፣ ያሰፋችውን እንጀራ ለማውጣት እየሮጠች ሄደች።



ዳንኤል ወደ አልጋዋ ተጠጋ። ዓይኖቿን ለማየት ቸኩሏል። ሸዋዬ ጥላቸው በመሄዷ ደስ ሳይለው አልቀረም። አጠገቡ የሚታዘበው ሰው ሳይኖር፣ የንግሥትን ፊት በናፍቆት ለማየት ጓጉቷል። "ንግሥትዬ !"

መልስ አልሰጠችውም። በማንባት ላይ እያለች ድንገት መድረሱን አልወደደችውም። ቀና ሳትል ፊቷን በአልጋ ልብሱ ጠረገችና ከአልጋው ተነሳች።

በረሀብ ስሜት ተያዩ። አንገቷን አቅፎ፣ ከንፈሮቹን ከንፈሮቿ ላይ አሳረፈ። ባለፉት ጥቂት ቀናት ያደረባቸውን የናፍቆት ስሜት ለመወጣት፣ ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል በዚህ ሁኔታ ቆዩ። ወዲያው፣ ንግሥት ከንፈሮቿን አላቀቀችና ፊቷን አንገቱ ሥር ቀብራ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች። 'አምላኬ! ለምን ታሰቃየኛለህ? መድሀኒት በሌለው በሽታ፣ በማላገኘው ሰው ፍቅር፣ በስንቱ መቀጣት እችላለሁ ? ከፍቅረኛ ጋር ተዋደው እንዲሁ መቆየት አይቻልም? ሁልጊዜ ፍቅር በግብረ ሥጋ ግንኙነት መታሰር አለበት? እንዲሁ ብቻ፣ በመንፈስ አንድ በመሆን፣ አብሮ መኖር አይቻልም? እባክህ አምላኬ ስማኝ! እባክህ አድነኝ! እባክህ ከዳኒ አትለየኝ ! ያለ ዳኒ መኖር አልችልም - ለጥቂት ዓመታትም ቢሆን' አለች ለራሷ።

ዳንኤል ከፋኛ ደንግጦ አንገቷን ቀና አድርጎ አያት። ዓይኖቿ በዕንባ ታጥበዋል። የግንባሯ ሥሮች ተግተርትረዋል። የጉንጮቿ አጥንቶች ገጠዋል። ህይወት የነበረው ፊቷ ገርጥቷል። "ምን ሆነሻል ንግሥትዬ?"

"አሞኛል።" ብላ ትከሻው ላይ ዘፍ አለች።

"ምንሽን?"

ምን ትበል ? ዳንኤልን ማዳኛ ደቂቃ አሁን ነው። የያዛትን የበሽታ ዓይነት ተናግራ ዳንኤልን ብታባርረው ህይወቱን ታድነዋለች። የምትወደውን ሰው በማዳኗ፣ በዚህች ዓለም ከእንግዲህ ወዲያ በምትቆይባቸው ዓመታት፣ የህሊና ደስታ ታገኛለች። ይሁንና፣ የተመኘችውን የህሊና ደስታ ዳንኤልን ከጎኗ በማጣት ለማግኘት አልፈለገችም። ህሊናዋ ከሚሰጣት ጥቅም ይልቅ የርሱ ፍቅር የሚሰጣት ጣፋጭ ደስታ፣ ከፍተኛ ነው ብላ አመነች። እና ዳንኤልን ማባረር እንደሌለባት ወሰነች።

ግን ደግሞ አሁንም የህሊና ጥያቄ ከተፍ አለ። 'አንቺ እንዴ አብቅቶልሻል። ከሞተው በላይ ከነዋሪው በታች ነሽ። ለምን እሱን

እዚህ መከራ ውስጥ ትከቺዋለሽ ? ፍቅር ሲውል ሲያድር የሚረሳ እኮ ነው ! ሀሊና ግን ሲውል ሲያድር ሲቆስል፣ ሲያመረቅዝ ነው የሚኖረው። እባክሽ ለሀሊናሽ ተገዢ።!'

ሌላው አፍራሽ ስሜቷ ብቅ አለ። 'አይሆንም! ፍቅር ይቅደም። አፍቅረሽዋል። አስጨርሽው፣ ያስጨርስሽ። ሰው ሁሉ እኮ የተፈጠረው ሊሞት ነው። ምን አስፈራሽ ?' ለሀሊና የቆመው ስሜቷ በተራው ተነሳ። 'ሰዎች ሁሉ ሟች ቢሆኑም፣ አንድ ላይ፣ እኩል መሞት የለባቸውም። እርሱ መኖር አለበት።' ሌላው እንደገና ከተፍ አለ። 'ሰዎች ሁሉ እኩል እንደማይሞቱማ የታወቀ ነው። ፍቅርሽን ቀጠልሽ ማለት ከዳንኤል ጋር እኩል ትሞታላችሁ ማለት እኮ አይደለም። እርሱ አንቺ ከሞትሽ በኋላ የሚኖርባቸው ረዘም ያሉ ጊዜያት ይኖሩታል። አትስጊ እባክሽ !'

ንግሥት በአእምሮዋ ውስጥ የሚሟገቱትንና የሚፋጩትን፣ የፍቅርና የሀሊና ስሜቶቿን መዳኘት አልቻለችም። ለአንዱ ማድላት እንዳለባት ግን አውቃለች።

ዓይኖቿን ከድና ሳትናገር በመቆየቷ፣ እንደመደንገጥ አለና፣ ፊቷን በመደባበስ፣ "ንግሥዬ ! ንግሥትዬ! "

ዓይኖቿን ከፈተች።

"ምንሽን ነው የሚያምሽ ?"

"የመንፈስ ጭንቀት !መንፈሴ ይረበሻል፣ ዳኒ።"

"አይዞሽ! ትድኛለሽ!ይሄ ቀላል ነገር አይደለም እንዴ! አይዞሽ!" አለና ግንባሯ ላይ ሳማት። ባለፈው፣ ከቤተሰቦቹ ጋር ሊያስተዋውቃት በጉዞ ላይ ሳሉ፣ ድንገት አሞኛል ካለችው ጊዜ አንስቶ ፣ ብዙ ነገሮችን ሲያወጣና ሲያወርድ ነው የከረመው። በዚያ ቀን፣ የንግሥት ፊት ጭንቀት እንዳስነበበው ያስታውሳል። መነሻው ምን እንደሆነ ግን ሊገምት አልቻለም። በጭንቅላቱ ውስጥ ብዙ ነገሮች ሲርመሰመሱ ነው የሰነበቱት። ቅናት ብጤ ኮርኮር አድርጎታል። ከእሱ ሌላ ያፈቀረችው ሰው፣ ድንገት ደርሶባት ከርሱ መለየት ፈልጋ የሰጠችው ምክንያት ነው የመሰለው። ያን ያህል ባለጌ ናት ብሎ ግን፣ ለመደምደም አልቻለም። እርሱን የቀረበችው፣ ለእውነተኛ ፍቅር መሆኑን ከሁኔታዋና ከድርጊቷ ተረድቷል። ግን ማን እንደሚያወራው ሆኖ ይገኛል?



"እኛ ሰዎች ሁል ጊዜ፣ የሚያስጨንቁን ነገሮች አናጣም። ይሄ ሁኔታ፣ በአንቺ ላይ ብቻ የታየ አይደለም። እያንዳንዳችን፣ በህይወት ስንኖር የምንሰማቸው፣ የምናያቸውና የምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ሊያስጨንቁን ይችላሉ። ግን በብልሀት ዘለን የምናመልጣቸው ወይም ጎንበስ ብለን የምናሳልፋቸው፣ ባለን የመታገስ ችሎታና ልምድ ይወሰናሉ። ሁላችንም የመንፈስ ጭንቀት አለብን። ይህ በአንቺ ብቻ የመጣ፣ የሚታይ አይደለም፣ ንግሥትዬ። " አለ። እርሷን ለማጽናናት ብሎ የተናገረው ራሱን ሳያስገርመው አልቀረም። "መቼ ነው የጀመረሽ ?" ሲል ጥያቄውን አስከተለ።

ምንም መልስ አልሰጠችውም።

"የዚያን ቀን ? ያኔ አብረን ያመሸን ቀን ነው የጀመረሽ ?"

"አይደለም። ከዚያ በፊት ነው።" ስትል ዋሸች።

"አይዞሽ ! ቀላል ነገር ነው። ለከፋ የሚሰጥ ነገር አይደለም። እኔ ራሴ በቀላሉ ላድንሽ እችላለሁ። የሥነ-ልቡና አዋቂዎች የጻፏቸው ብዙ መጻሕፍት አሉ። እነሱን አመጣልሽና ታነቢያቸዋለሽ። ብዙ ይረዱሻል። ብዙ ይመክሩሻል። ህይወትን በተስፋና በደስታ እንድትኖሪ የሚያስችል ጥበብ ይሰጡሻል።" አለ መሀረቡን ከኪሱ አውጥቶ ዕንባዋን እየጠረገ።" አይዞሽ የኔ ፍቅር !ብቻሽን ደግሞ አትሁኚ። የሚያጫውትሽ ሰው ከሌለ እንኳ መጻሕፍትን አንብቢ። አንዳንድ ነገሮችን አድርጊ። ራስሽን በሥራ ጥመጂው። ለመንፈስ ጭንቀት በሽታ፣ መድሀኒቱ ራሱ ህመምተኛው ነው። ሙዚቃ አድምጪ። አንዳንድ መዝናኛ ቦታዎች ደግሞ እንሄዳለን። አይዞሽ፣ እኔ እስካለሁ ምንም አትሆኝም። ትድኛለሽ። " አለ።

የዳንኤል ንግግር በልቧ ውስጥ ሰፍኖ የነበረውን ሀዘን እየሸረሸረው ሄደ። ትንሽም ቢሆን የመጽናናት ስሜት አሳደረባታል። የሚላትን ለመስማትና ለማድረግ የተዘጋጀች መሰለች።

"ከነገ ወዲያ ማታ ለምን ሂልተን ሆቴል ፓርቲ አንወጣም? ያዝናናሻል። ጥሩ ዝግጅት አላቸው። ሌሊቱን ሙሉ ስንደንስ ማደር እንችላለን። ጥሩ አይመስልሽም?"

ንግሥት ዝም አለች።

"ተናገሪአ። ምነው?ቤት ውስጥ መተኛቱ ጥሩ አይደለም እኮ ንግሥትዬ። እሺ በይኝ።" አለ በመጎትጎት ስሜት።

"ላስብበት ዳኒ።" አለች ጭንቅ ብሏት፣ በእጇ ጣቶች ፀጉሯን ወደ ኋላ እንደማበጠር እያለች።

"ምን ማሰብ ያስፈልጋል ለዚህ ደሞ ?"

መልስ አልሰጠችውም።

"እሺ እንዳልሽ ይሁን። ነገ ስመጣ ትነግሪኛለሽ ?"

"እዎ!"

## 41

ዶክተር ናትናኤል፣ በግል ክሊኒካቸው ውስጥ በዕለቱ የመጡትን ህሙማን አክመው ጨርሰው የጥናት ክፍላቸው ውስጥ ከገቡ፣ አሥራ አምስት ደቂቃዎች አልፈዋል። ከፊት ለፊታቸው ካለው መጽሐፍ ላይ ዓይኖቻቸውን ቢያሳርፉም ማንበብ አልቻሉም። ዛሬ ሙሉ ቀን ሲያከናውኑ የዋሉትን ተግባራት በክለሳ ያዩ ጀመር።

በማለዳ ሲጨቃጨቁ ካገኟቸው ባልና ሚስት ጋር ራሳቸውን ካስተዋወቁ በኋላ፣ መላኩን ለማነጋገር ጠየቁ። የንግሥትን በህዋሱ መለከፍ አረዱት። በመላኩ ላይ የታየው ስሜት አሳዛኝና አስደንጋጭ ቢሆንም፣ የተቻላቸውን በመጣር ሊያጽናኑትና ማድረግ የሚገባውን ሊመክሩት ሞከሩ። ከብዙ ድካም በኋላ፣ ለመመርመር ፈቃደኛ እንዲሆን አደረጉ። እርሱን ብቻ ሳይሆን ባለቤቱንም ወደ ሆስፒታል ወስደው ደማቸውን አስመረመሩ። በሁለቱም ሰዎች ደም ውስጥ የኤድስ ህዋስ አልተገኘም። ይህ ሁኔታ ዶክተርንና ባልና ሚስቱን አስደስቷል። በባልና ሚስቱ መሀል የነበረው ፍቅር እንደወትሮው ቀጥሏል። ይሁንና፣ ዶክተርን ጥያቄ ውስጥ ከቷቸዋል -ይህ ሁኔታ። ልጃቸው ወሲባዊ ግንኙነት ያደረገችው ከዚህ ሰው ጋር ብቻ እንደሆነ ነግራቸዋለች። ከመላኩ ሌላ ማንንም ወንድ እንዳላየች ከርሷ ተረድተዋል። ይህ ሁኔታ ለጥቂት ጊዜ ሲያስጨንቃቸው ከቆየ በኋላ አንድ ነገር ትውስ ብሏቸው ነበር። ከጥቂት ዓመታት በፊት፣ በ1978 ዓ.ም. ንግሥት በጠና ታምማ ደም አስፈልጓት ከእርሳቸው እንደተቀዳ አስታወሱ። ትውስታው አስደንግጧቸው የራሳቸውን ደም አስመርምረዋል። ዘንግተውት ነው እንጂ የእርሳቸውና የንግሥት ደም ዓይነት አንድ ባለመሆኑ በርሳቸው ደም ልዋጭ ሌላ ነበር የተሰጣት። ይህ ሁሉ ትዝ ያላቸው የርሳቸው የደም ምርመራ ጤናማ መሆናቸውን ከመከሰረ በኋላ ነበር። ሳይመረመር ከልጃቸው ደም ጋር የተቀላቀለው የሌላ ሰው ደም እንደለከፋት አምነዋል። ሁኔታው እጅግ



ሲያሳርራቸውና ሲያስቆጫቸው ነው የዋለው። ነገሩን ሁሉ ለልጃቸው ሊያስረዱ ፈልገው እንደገና ሥቃይ መቀስቀስ ነው ብለው ትተውት ነበር። ነገር ግን መላኩን በማያውቀውና በማይመለከተው ነገር መጥላትና መውቀስ እንደሌለባት ለማስረዳት ወሰኑና ወደ መኝታ ክፍሏ ሄዱ።

ንግሥት ከባድ እንቅልፍ ወስዷታል። ቀስቅሰው ያረፈ መንፈሷን ሊረብሿት አልፈለጉም። ጭራሽ ሀሳባቸውን በመለወጥ የመድሀኒታቸው ግኝት ስኬታማ ሆኖ እስክትድን ድረስ ላለመንገር ወስነው ወደ ጥናት ክፍላቸው ተመለሱ።

## 42

አባቷ ከሥራ ሲመጡ፣ እንደወትሮው ተንሳቄላ አልጋዋ ላይ አላገኟትም። ዛሬ፣ ፊቷ የቀድሞ ውበቱን ይዞ፣ ፀጉሯን ወደ ኋላ አበጥራ ራንግለር ጃኬት ላይ አስተኝታው፣ ጥቁር ሱሪዋን አድርጋ አይዋት። የልጃቸው ሞራል፣ እንደገና እየተገነባ መሆኑን አወቁ። ሁኔታው አስደሰታቸው። የዳነች ያህል ፈነደቁ።

"ንግሥቴ!ደህና ዋልሽ?" አሉ፣ ጥሩ ስሜት ባለው የድምጽ ቃና።

"ደህና ዋልክ አባዬ?"

እቅፍ አድርገው ጉንጮቿንና ግንባሯን ሳሙ።

"ልወጣ ስል እኮ ነው የመጣኸው።" አለች ፈገግ ብላ።

"ወዴት ልትሄጂ?" አሉ፣ ከእቅፋቸው አውጥተው ከእግር እስከራሷ እያዩዋት።

"ፓርቲ ልወጣ ነው። ጥሩ አይመስልህም? ራሴን ላዝናናው አይደል?"

ጥቂት ዝም ብለው ካዩዋት በኋላ፣ ፈገግ ብለው፣ "ጥሩ ነው! በጣም ጥሩ ነው!" አሉ ትከሻዋን በሁለት እጆቻቸው ደግፈው፣ ፊት ፊትዋን እያዩ። "ግን ከማን ጋር ነው የምትሄጂው?" ሲሉ ጠየቁ፣ ፈገግታቸውን ሳይቀንሱ።

"ከሲሳይ ጋር። "ስትል ዋሸች።

"ሲሳይ ?ይህች ጓደኛሽ ?"

"እዎ!"

"ስምታለች እንዴ? " ሲሉ ሳያስቡት ጠየቁ።

"ምኑን ?" አለች።

ዶክተር ጥያቄውን ማንሳት እንዳልነበረባቸው ዘግይተው ነው የገባቸው። " አሁን ከእኔ ምን ትፈልጊያለሽ? ስንት ብር ይበቃሻል ? "

ለጥያቄያቸው መልስ እስክትሰጥ አልጠበቋትም። ከኋላ ኪሳቸው ቦርሳቸውን አውጥተው አንድ የመቶ ብር ኖት ሰጧት።

ገንዘብ እንደማያስፈልጋት ብታውቅም፣ መቀበል ነበረባት። "አመሰግናለሁ።" አለችና ጉንጫቸው ላይ ሳመቻቸው። መንገድ ልትጀምር ስትል ጠሯት።

"ንግሥት፣..." አሉና ጥቂት አሰቡ። 'ፓርቲው ሲያልቅ መጥቼ ልውሰድሽ?' ብለው ሊጠይቋት አሰቡና ተውት።

"አቤት አባዬ!"

"እስከ ስንት ሰዓት ነው የምትቆይው?"

"ሌሊቱን ሙሉ ነው። "

"ጥሩ። ቻዎ! ብቻ ንግሥቴ፣ አደራ! ተጠንቀቂ! እሺ የኔ ንግሥት!" አሉ በምክር ድምፀት።

ምን ማለታቸው እንደሆነ ገብቷታል። ይህ ጥያቄ መነሳቱ እንደማይቀር፣ ከበፊቱም አውቃለች። ግን በዚህ መልኩ ሳይሆን፣ በ'አትሂጂም' ቁጣ ይታጀባል ብላ ነበር የገመተችው።

ከግቢዋ ወጣች። ሜክሲኮ አደባባይ የሚወስዳትን ታክሲ ያዘች። ለጥቂት ቀናት ከቤቷ ሳትወጣ በመቅረቷ፣ በየጎዳናው ያጋጠሟትን ነገሮች በአትኩሮት እያየች፣ መድረሻዋ ቦታ ላይ መኪናው ቆመ። ሂሳቧን ከፍላ ወረደች። እንደወትሮው ቀድሞ ይጠብቃት ነበር። መኪናውን ከፍታ ገባችና ጉንጯን አቀበለችው።

ጉንጭ ለጉንጭ ካነካኩ በኋላ፣ ከንፈሮቻቸውን ለቅጽበት ያህል አገናኙና አለያዩ።

ንግሥት እስከዛሬ ያልገጠማትን ደስታ ሰጧት፣የዳንኤል ከንፈሮች። የተከለከሉት ነገር ይጣፍጣል ለካ !

ፈገግ ብሎ አያት። ነጭ ሙሉ ልብስ፣ ጥቁር ሸሚዝና ነጭ ከረባት አድርጓል። "ዛሬ የህይወትን ሌላ ጥሩ ገጽታ መሰልሽ!"

"እንዴት?"

"ውብ ሆነሻል!"

"የህይወት ሌላው ገጽታ ምንድን ነው?"



"ውበት አልባ መሆን። "አለ፣ ዓይኖቹን ከፊቷ ሳያነሳ።

"አሁንም እንዴት?"

"ሥቃይ፣ ትካዜና መረበሽ ያመጣው ሀዘን ሲኖር፣ ህይወት ታስጠላለች። ያን ጊዜ ውበቷ ይጠፋል። አይደለም እንዴ ?"

"ጠጠረብኝ። "አለች ፈገግ ብላ።

ጉንጯን በቀኝ እጁ ነካ አደረገና፣" የፓርቲው ሰዓት እስኪደርስ የት እናምሽ ?" ሲል ጠየቃት።

"ደስ ያለህ ቦታ። "አለች፣ ስጋትም ደስታም እያናኳት።

ላሊበላ ሬስቶራንት ሲደርስ የመኪና ማቆሚያ ፈልጎ አቆመ። ከመኪናው ወርደው መግባት እንደጀመሩ፣ "ላይ እንውጣና መጀመሪያ መክሰስ ቢጤ እናድርግ።" ሲል ሀሳብ አቀረበ።

"እኔ እንደሁ አሁን በልቻለሁ። ትንሽ መሽት ሲል፣ ራት ብንበላ ይሻላል።"ስትል የራሷን ሀሳብ ሰጠች። "አንተ አስፈልጎሀል?" በማለት፣ በማስከተል ጠየቀች።

"አልፈለኩም።"

ወደ መጠጥ ቤቱ ገቡና ወንበር ያዙ። አሳላፊው መጣና ቢራ ታዞ ሊያመጣ ተመልሶ ሄደ።

"ተጫወቻ ' ማይ ኪዊን '!" ሲል ተነፈሰ። የኔ ንግሥት እያለ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ሲጠራት ደስ ይላታል። ይህንኑ ከዚህ በፊት ነግራዋለች።

"እሺ። "አለች በግማሽ ፈገግታ።

ጥቂት ትኩር ብሎ አያት። የአሁኑና ከጥቂት ቀናት በፊት የነበረው ስሜቷ ትልቅ ልዩነት እንዳለው ተገንዝቧል። ቁጥብ የሆነች መስላ ታየችው።

ቢራው መጣ። አሳላፊው ዋንጫ መሰል ብርጭቆዎች ውስጥ፣ በግማሽ ቀዳላቸውና ሄደ።

ዳንኤል የራሱን አነሳና፣" ቺርስ !"አለ።

ንግሥትም አነሳችና አፀፋውን መለሰች። ተጎነጩና አስቀመጡ።

"ለምን እንደሆነ አላውቅም ቢራ የሚጥመኝ የመጀመሪያው ጠርሙስ ብቻ ነው።" አለች ንግሥት።

"አዎ፣ እኔም የሚጣፍጠኝ የመጀመሪያው ብርጭቆ ብቻ ነው።"

"ለምንድን ነው?"

"ኢኮኖሚስቶች አንድን ነገር ብዙ በተወሰደ ጊዜ 'ማርጅናል ዩቲሊቲይ ዲሚኒሽ ' ያደርጋል ይላሉ። ይህ ማለት ምን ማለት መሰለሽ... ለምሳሌ የመጀመሪያው ጠርሙስ ቢራ የሚሰጠን ርካታና የሁለተኛው እኩል አይደለም። አንዳንድ ጠርሙስ ቢራ ጨምረን በጠጣን ቁጥር የምናገኘው ርካታ እየቀነሰ፣ እየቀነሰ ይሄድና መጨረሻ ላይ እንዳውም ያልተፈለገ ውጤት ያመጣል። ይህንን ነው የገለጹት።" አለ ፈገግ ብሎ።

"ይህንን ነው የገለጽነው ብትል አይሻልም?" አለች ፈገግ ብላ።

"እኔን ከነሱ ተርታ የሚያቆመኝ እውቀት መች ጨበጥኩና።" አለ ፈገግታው ሳይጠፋ።

ዳንኤልን እንድትወደው ኮደርጓት ባህርያት አንዱ፣ ራሱን ከሌላው ከፍ አድርጎ አለማየቱ ነው። ስለራሱ ከመናገር ይቆጠባል። ከሚናገራቸው ቃላት ይልቅ፣ ድርጊቶች ስለራሱ እንዲናገሩ የመረጠ ይመስላል።

"በጣም ቆየን አይደል፣ ከተገናኘን ?"ሲል ጠየቀ።

"አዎ!"

"ያን ቀን አባዬና እማዬን እንግዳ ይዤ እመጣለሁ ብያቸው፣ ብቻዬን ስገባ፣ በጣም ነው ቅር ያላቸው።"

ስላለፈው ሁኔታ መነሳቱን አልወደደችውም።

"ስለ አንቺ ሁኔታ ነግሬአቸው ነበር። አንቺን ለመተዋወቅ እጅግ ጓጉተው ነበር። ነግሬሻለሁ ከዚህ በፊት... ለእናትና አባቴ ልክ እንደ አንቺ ብቸኛ ልጃቸው ነኝ። ሚስት እንዳገባ በጣም ይገፋፉኛል። የልጅ ልጅ ለማየት ትልቅ ጉጉት አላቸው።" አለና ቢራውን ተጎነጨ።

ዳንኤል የተናገራቸው ቃላት በንግሥት ላይ የመከፋት ስሜት አመጡ።

"ጠጪ እንጂ።"

"እሺ። "አለችና ብርጭቆውን አነሳች።

"ዛሬ እንዴት ነው... ጨዋታውንም ቀንሰሻል። ጥቂት ቀናት ተለያይተን ስለተገናኘን እንግዳ ሆንኩብሽ መሰለኝ?"

"እየተጫወትኩ እኮ ነው።"

ዝምታ ሰፈነ።



"በቀደም ዕለት እቤት ያደረስኩሽ ቀን፣ ልክ ከእናንተ ግቢ አለፍ እንዳልኩ፣ አባትሽ በመኪናቸው ሲመጡ አየኋቸው።"

ንግሥት ስሜቷ ትንሽ ቆንጠጥ አለና " ምን አለህ ?"አለች ጓጉታ።

"ምንም አላሉኝም። ትኩር ብለው ሲያዩኝ ሰላም አልኳቸው። አንድ ጊዜ ስላከሙኝ አስታውሰውኝ ነው መሰለኝ፣ አተኩረው አዩኝና አፀፋውን መለሱልኝ።"

ንግሥት እፎይታ ተሰማት።

"የዚያ የምርምራቸው ውጤት ምን ደረሰ?"

"ጥሩ አዝማሚያ እያሳየው ነው። ተስፋ እንዳለው ነው የሚነግረኝ።" አለች።

"የመጨረሻው ውጤት መቼ የሚታወቅ ይመስልሻል?"

"እኔ እንጃ። ብቻ ረጅም ጊዜ እንደሚወስድበት ነግሮኛል። ግን አሁንም ችግር አለበት።"

"የምን ችግር?"

"የገንዘብ።"

"ባለፈው ጊዜ ልረዳቸው እችላለሁ ብዬሽ ነበር። ነገርሻቸው ይሆን?"

"አዎ! በደስታ ነው የተቀበለው።"

"ታዲያ እስካሁን ለምን ሳትነግሪኝ ቆየሽ?"

ምንም አልተናገረችም።

"ምን ያህል ነው የሚፈልጉት?"

"እኔ እንጃ። ጠይቄ እነግርሀለሁ።"

"ነገ ቤት ስትሄጂ ጠይቀሽ፣ ወዲያውኑ ትነግሪኛለሽ። እሺ?"

"ጥሩ።"

## 43

የዳንሱ ሥነ ሥርዓት ከተጀመረ ጥቂት ሰዓታት ተቆጥረዋል። አብዛኛው የዳንሱ ታዳሚዎች፣ ጥንድ እየሆኑ በፈጣኑም፣ በለስላሳውም ሙዚቃ ስልታቸውን እየለዋወጡ ሲደንሱ አምሽተዋል። ከነዚህ መሀከል ዳንኤልና ንግሥት ይገኙበታል።

ምሽቱ ለዳንኤል አስደሳች ቢሆንም ፣ ለንግሥት ግን አልነበረም። ለንግሥት ከዳንኤል ጋር እንደዚህ ያለ ምሽት ማሳለፍ እንደጥርስ ህመም የሚያሰቃይ ሆኗል። እንደሌሎቹ እንስት ነጻ ሆና፣ የምትወደውን ሰው አላጫወተችውም። የተለመደው የጎሊና ወቀሳ ልቧን እያደማው ተቸግራ ነው ያመሸችው። ሌሎች መሰል ጓደኞቿን እያየች 'ምን የታደሉ ናቸው!' በሚል ስሜት ስትቀናና ቅሬታ ሲሰማት ነው፣ ሌሊቱ የተገባደደው። እስካሁን የወሰደችው የአልኮል ዘር ከወትሮው በርከት ቢልም፣ ከዚህ ስቃይ ነፃ ሊያወጣት አልቻለም።

ከሌሊቱ አሥራ አንድ ሰዓት ሲሆን፣ የዳንሱ ዝግጅት አለቀ። ከታዳሚዎቹ ውስጥ አንዳንዶቹ ይዘው በመጡት መኪና፣ ሌሎቹ ደግሞ በእግር መጓዝ ቀጠሉ። ጥቂቶቹ ደግሞ እስኪነጋ ድረስ በሆቴሉ ውስጥ የመረጡትን ቦታ ያዙ።

"ንግሥትዬ ፣ ቤት እንሂድ። "አለ ዳንኤል፣ አንድ እጁን ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጎ።

ምንም አስተያየት አልሰጠችም።

"ነገ የምትሄጂበት ቦታ አለ?"

"እም።"

"በቃ እስኪነጋ ድረስ ወደ ቤት እንሂድ። "አለና መኪናውን ወዳቆመበት ቦታ፣ ፈጥኖ ሄደ።

ተከተለችው። ከውስጥ ሆና በከፈተላት በር ገባች። የዳንሱ ዝግጅት ካለቀ በኋላ፣ በቀጥታ ወደ ቤቴ እሄዳለሁ ብላ ነበር ያሰበችው። እስኪነጋ ይቆያል ብላ ነበር የጠበቀችው። ያሰበችው ሳይሆን ወደ ዳንኤል ቤት ለመሄድ በመገደዷ ሰሞኑን አብሯት የከረመው ሥጋት፣ አሁንም ከጎኗ አልተለየም። ያ የምትፈራው ጊዜ እንደደረሰ ተረዳች።

"እንዴት ነው ፓርቲው?" አለ የመኪናውን ሞተር እያስነሳ።

"ጥሩ ነው።"

መኪናዋ ጉዞዋን ጀመረች። ወደ ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ የሚወስደውን ጎዳና ተያያዘችው። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፣ ወደ ውስጥ በሚያስገባ አንድ መንገድ ዳር፣ ከሚገኘው የዳንኤልና የቤተሰቡ መኖሪያ ቤት ደረሱ።

የመኪና ጥሩንባ ሲነፋ የሰማው ዘበኛ፣ ከአልጋው ላይ ተነስቶ ሮጦ ከፈተ።



መኪናዋ ገባች። በግቢው ውስጥ፣ አንድ ፎቅ ያለው ትልቅ ቤት ጉብ ብሏል። ዳንኤል ጋራዡ ውስጥ መኪናውን ካቆማት በኋላ፣ ወጡ። ከትልቁ ቤት በስተጀርባ፣ አንድ ራሱን የቻለ ትልቅ ቤት አለ።

የንግሥትን ክንድ ደገፍ አድርጎ፣ "የእኔ ቤት ይሄ ነው። ያ የወላጆቼ ቤት ነው።" አለ ዳንኤል፣ በሌላ እጁ እያመለከተ። በሩን ከፈተና የሳሎኑን መብራት አበራ። ክፍሉ የሚያስፈልጉትን ዕቃዎች በሙሉ ይዟል። ሶፋው፣ ኮንትሮ ቡፌው፣ የምግብ ጠረጴዛና ወንበሮች፣ ተራራ የሚያክል ቪዲዩ፣ ምንጣፍና የግርግዳ ጌጦች በሙሉ ለሰፊው ሳሎን ውበት ሆነውታል።

ወደ ግራ የሚወስደውን በር ከፈተና ገቡ። መተላለፊያውን አቋርጠው፣ ወደ መኝታ ክፍሉ ከመግባታቸው በፊት፣ መታጠቢያ ቤቱን እንዲያሳያት ንግሥት ጠየቀችው። አሳያት። በሩን ከፍታ መብራት አበራች። መታጠቢያ ቤቱን የፈለገችው፣ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ብቻዋን ለመሆን ነበር። ከእጅ መታጠቢያው በላይ ያለውን መስታወት ተመለከተች።

ንግሥት ናትናኤልን ተጨንቃ፣ ተከዛ፣የምታደርገውና የምትሆነው ጠፍቷት እየቻት፣ ራስዋ ንግሥት። ጠይም የነበረው ቆዳዋ በርኖስ መስሏል። ለወትሮው ነጭ መደባቸው ጠርተው፣ ውበት የሚረጩት ትላልቅ ዓይኖቿ፣ ዛሬ ሲያለቅሱ እንደዋሉ ሁሉ ቀልተዋል። ፀጉሯ ምስቅልቅሉ ወጥቷል። የራሷ ገጽታ አስፈራትና ዓይኖቿን ከመስታወቱ ላይ ነቅላ ወደ ጣሪያው ላይ ተከለች። 'አምላኬ ሆይ! እባክህ ከዚህ ጭንቅ አውጣኝ! እባክህ የዳኒን ስሜት ያዝልኝ ! አውጣኝ አምላኬ! ብርታቱን ስጠኝ !' አለች በልቧ። ቀበቶዋን አላልታ የውስጥ ሱሪዋን ከፍ አደረገችና የለበሰችውን ሸሚዝ ለቀቀችው። ሱሪዋን ጥርቅም አድርጋ በቀበቶዋ አሰረችው። ጃኬቷን እስከአንገቷ ድረስ ዘጋችው። ከመታጠቢያ ክፍሉ ወጣች። መብራት ያየችበትን ክፍል በር ከፍታ ገባች። ደብዘዝ ያለ ብርሀን በርቷል። አንድ ሰፊ አልጋ፣ ከባህር ማዶ የመጣ ቀይና ነጭ ዥንጉርጉር ቀለም ያለው የአልጋ ልብስ ለብሶ ይታያል። አንድ ቁንጠኛ ቁምሳጥንና ኮሞዲና ሌሎች የክፍሏ ሀብቶች ናቸው። ከአልጋው ጎን አንድ አነስተኛ ጠረጴዛ የውስኪ ጠርሙስ፣ አምቦ ውሀ፣ በረዶ የተቀመጠበት ሳህንና መለኪያዎች ይዞ ይታያል።

ዳንኤል ካፖርት መሰል ቢጃማ ለብሶ፣ በመስኮት ውስጥ፣ ሰማዩ አቅፎ የያዛቸውን ኮከቦች ያያል። የንግሥትን ኮቴ ሲሰማ መስኮቱን ዘጋና ወደ በሩ ተጠጋ። በሩንም ዘጋው።

የንግሥት ልብ መዝለል ጀመረ-በድንጋጤ። ልትጮህ አሰበች። ግን ማን ይሰማታል? ቤቱ ውስጥ ያለነሱ ማንም የለም። የሚሰማትና የሚያስጥላት፣ ዳንኤልን የሚያድነው ሰው ባለመኖሩ ይበልጥ ጭንቅ አላት። ሰሞኑን የርሷ ህይወት በአደጋ ላይ በመሆኑ፣ ስትሰቃይ ከርማለች። ዛሬ ደግሞ፣ የሌላ ሰው ህይወት ከሥቃይ እንዳይገባ የገጠማት ሙግት፣ ይህ ነው የማትለው የሥቃይ ሥቃይ ውስጥ ከቷታል። ግንባሯ ላይ ላብ ቸፈፍ አለ።

"አልጋው ላይ ተቀመጭ እንጂ።" አለ ዳንኤል፣ ውስኪውን በመለኪያ እየቀዳ።

ተቀመጠች።

"በረዶ ላድርግልሽ ?"ሲል ጠየቀ ሳያያት።

አልሰማችውም። የልቧን ትርታ ነበር የምታዳምጠው።

ድምጿ ሲጠፋበት ቀና ብሎ አያት። "ምነው አላበሽ ንግሥትዬ?" ሲል ፍቅር ባዘለ ዜማ ጠየቃት።

ግንባሯን በመዳፏ ጠረገችና፣ "እንዲሁ ነው። "አለች።

"በረዶ ልጨምርልሽ?"

"ተወው!" አለችና ወዲያው ሀሳቧን ለውጣ፣ "ጨምሻበት።" አለች።

አጠገቧ ከተቀመጠ በኋላ፣ መለኪያውን አነሳና፣ "ያገር እንጂ።" አለ ፈገግ ብሎ።

ደረቅ ፈገግታ አሳየችውና መለኪያዋን አንስታ ፉት ካለች በኋላ፣ አስቀመጠች።

"ተጫወች!" አለና በአንድ እጁ ትከሻዋን መታ አደረገው። እጁ ግን አልተመለሰም። እዚያው ቀረ፣ ትከሻዋ ላይ ሙጥኝ። "ንግሥትዬ፣ ምን ሆነሻል?"አለና በሌላው እጁ ግንባሯ ላይ የተቋጠረውን ላብ እንደማድረቅ አደረገ። ይሄኛውም እጁ በቦታው አልተመለሰም። አገጯን ደገፍ አድርጎ ቀና አደረጋት። ንግሥት ዓይኖቿን በፍርሀት ከደነች። ከንፈሮቿ ይንቀጠቀጡ ጀመር። የዳንኤል ከንፈሮች ተቀበሏቸው። ከንፈሮቻቸው ተገናኙ። እዚያው አልረጉም። አንገቷን፣ ጉንጮቿን ሁሉ ዳሰሱ። እጆቹም ሥራ አልፈቱም። አልጋው ላይ በግማሽ ጋደም አሉ። በዚህ ሁኔታ ጥቂት ሴኮንዶች እንዳለፉ፣ ንግሥት ፍንጥር ብላ ከአልጋው ላይ ተነሳች። ግን ርቃ ልትሄድ አልቻለችም። ዳንኤል እጇን ስቦ አስቀራት። ተመልሳ



አልጋው ላይ ጋደም አለች። ደረቷን ተደገፎ እያያት፣ "ወዴት ልትሄጂ ነው።?"

ትኩር ብላ አይታው፣ ዓይኖቿን ከመከደን ሌላ አልተናገረችም። ዳንኤል እንደገና ከንፈሮቹን ከከንፈሮቿ ጋር አቆላለፈ። አልተቃወመችውም። እጁ አላረፈም። የሱሪዋን ቀበቶ ሊፈታ ሲል ያዘችው።

"ተው ዳኒ !" አለች፣ ከንፈሮቿን አላቅቃ።

"ለምን?" አለ፣ እንደመቆጣትም፣ ለስለስ እንደማለትም ብሎ።

"አልፈልግም።"

"ለምን? "አለ፣ ትንሽ ጠንከር ባለ ድምጽ።

መልስ አልሰጠችውም። ዓይኖቿን እንደመከደን ብላ ዝም አለች።

የዳንኤል ስሜት የሚታገስ አልሆነም። ዛሬ ንግሥትን የእርሱ ለማድረግ አቅዷል። ለብዙ ቀናት ሲናፍቀው የነበረውን ቀን፣ ደቂቃና ሴኮንድ ለሌላ ጊዜ ለማሳለፍ አልፈለገም። ዛሬውኑ፣ በማንኛውም መስዋትነት፣ መፈፀም እንዳለበት ወስኗል። ንግሥትን ለማሸነፍ ጥረት ማድረግ እንዳለበት አምኗል።

የንግሥት ስሜት ደግሞ፣ የሚፈታተነውን የዳንኤል ስሜት ታግሎ ለመግደል፣ ወስኗል። ይህንን ጊዜ፣ ለጥቂት ወራት ለማራዘም አቅዶአል። 'የዶክተር ናትናኤል መድሀኒት ካልሰራ ወይ ፍንክች!' የሚል ይመስላል። ግን የዳንኤልን ስሜት አሸንፎ በበላይነት መቆየቱ ያጠራጥራል። መፍረክረክ ጀምሯል። ቢሆንም እስከመጨረሻው ለመታገል ወስኗል።

ዳንኤል፣ ከንፈሮቹን ከንግሥት ከንፈሮች ጋር እንደገና በማገናኘት ፍልሚያውን ጀመረ። ከበፊቱ በበለጠ ጠንክሮ፣ ጥቃቱን በንግሥት ደካማ አካላት ላይ ሰነዘረ። አንገቷን፣ ትከሻዋንና ጡቶቿን እጆቹ መውረር ጀመሩ።

የንግሥት ስሜት ጥቃቱን አልቻለም። ከእንግዲህ ወዲያ በመቃወም፣ አንድ ሴኮንድ ማሳለፍ የሚችል አልመሰለም። መሸነፉን በፀጋ ተቀበለ። እጆቹን ሰጠ። የሚመጣውን ሥቃይ በቅጽበት ለሚገኘው ደስታ ሲል ለመቀበል ተዘጋጀ ።

የዳንኤል እጅ የንግሥትን ቀበቶ መፍታት ጀመረ።

ንግሥት ተቃውሞ አላሰማችም።

ዚፕዋን ከፈተው።

ምንም ተቃውሞ አላሳየችም።

ሱሬዋን ሊያወልቅ ሲታገል፣ የንግሥት ስሜት ብርታት አገኘ። ንግሥትን ከነበረችበት የሽንፈት ገደል ውስጥ መንጥቆ አወጣት። "ተው ዳኒ! አልፈልግም!" ስትል እያነባች ጮኸች።

ዳንኤል ለማሸነፍ ሞከረ። አልቻለም። ለቅሶዋ ከልብ አለመፈለጓን ነገረው። 'ለምን? ምንድን ነው ችግሯ? ለምን ትደብቀኛለች?' ሲል በንዴት ራሱን ጠየቀ። ወዲያው፣ "ለምንድ ነው እምቢ የምትይው ንግሥት?" አለ በንዴት።

"አልፈልግም!"

"ለምን? ምክንያት የለሽም?"

መልስ አልሰጠችውም።

"ምን ያህል እንደምታሰቃይኝ ይገባሻል?"

"ምን ላድርግ ዳኒ?"

"ችግርሽ ምንድን ነው ?ለምን አትነግሪኝም?"

ዝም አለች።

"ፔሬድ ላይ ነሽ ?"

አንገቷን በመነቅነቅ አለመሆኗን ገለፀች።

"ታዲያ ምንድን ነው ችግርሽ ? ለመንገር ትፈሪያለሽ ?"

ዝም አለች። ይሁንና በዝምታ ማለፍ እንደማትችል ተረዳች። ዳንኤል ላነሳቸው ጥያቄዎች መልስ መስጠት አለባት። ዳንኤል ከእንግዲህ ወዲያ የሚታገሳት አልመሰላትም። ነገሩን ሁሉ አፍርጣ ነግራው፣ ዕድል የምትሰጣትን ልትቀበል ወሰነች። ከእንግዲህ ወዲያ፣ ራሷን በማሰቃየት ልትቆይ አልፈለገችም።

ዳንኢል፣ ንግሥት የደበቀችው ነገር እንዳለ ያወቀው ዛሬ ብቻ አይደለም። ባለፈው ጊዜ፣ ቤቱ ሊያመጣትና ራት ሊጋብዛት የነገራት ቀን፣ ድንገት ተነሥታ ወደ ቤቷ ለመሄድ መወሰኗ፣ አንድ ነገር እንዳለ ነግሮታል። 'ግን ምንድን ነው ችግሯ?ለምን አትነግረኝ ም?'አንድ የጠረጠረው ነገር አለ። ግን፣ ይሄ በዚህ ዕድሜዋ ይኖራል ብሎ አልገመተም። ማረጋገጥ እንዳለበት አወቀ።

"ድንግል ነሽ ?"ሲል ጠየቃት።

ለረጅም ሴኮንድ እየችውና፣" አዎ!"ስትል ዋሸች።

"ታዲያ ለመቼ ነው የሚቀመጠው?"

"እስክንጋባ ድረስ። "



በትዝብትና በፈገግታ ከማየት ሌላ፣ በጊዜው የሚናገረው አልነበረውም።

## 44

"ሻምበል ፍቅሩ እባላለሁ።" አለና እጁን ዘረጋላት።

ሲሳይ ከተቀመጠችበት በመነሳት ትኩር ብላ እያየችው ጨበጠችው። ጠይም ፊቱ ማንነቱን ሊነግራት አልቻለም። ከዚህ በፊት አይታው አታውቅም። "ሲሳይ።" ብላ ስሟን ነገረችው።

"አውቃለሁ።" አለና ቢሮዋን ቃኘት፣ ቃኘት አደረገ። "ብቻሽን ላነጋግርሽ ፈልጌያለሁ። እዚሁ እንችላለን?" አለ በመቀጠል።

"አዎ? ምንድን ነው ጉዳዩ? ማን ነው የላከህ?" አለች በማከታተል። አርእያ የላከው ሰው ነው ብላ፣ ጠርጥራለች። 'ግን ለምን ጉዳይ?'

ሻምበል ፍቅሩ ከሲሳይ የጽሕፈት ጠረጴዛ ፊት ለፊት ካለው ወንበር ላይ ተቀመጠ። "መርማሪ ፖሊስ ነኝ- የግድያ ወንጀል መርማሪ ነኝ።" አለ፣ ዓይኖቿ ላይ ዓይኖቹን ሰክቶ።

ሲሳይ ድንጋጤ ቢጤ ቆንጠጥ አደረጋት። ምን መናገር እንዳለባት አላወቀችም።

-- "ላለፉት ጥቂት ጊዜያት ያህል ስከታተለው የነበረ ጉዳይ አለ። ይህንን ጉዳይ ለውጤት ለማብቃት አንዳንድ፣ ጉዳዩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚመለከታቸውን ሰዎች ማነጋገር አለብኝ። ከእነዚህ ሰዎች አንዷ አንቺ ሆነሽ ተገኝተሻል።"

ድንጋጤዋ ጨምሮ ዓይኖቿን ጎልጉላ እየችው።

"አፈወርቅ ምንዳዬን ታውቂዋለሽ?"

የምታውቀው ስም መነሳቱ ደግሞ ይበልጥ አስደነገጣት። ትኩር ብላ እየችውና፣ "አዎ!" አለች።

"የት ነበር የምትተዋወቁት?"

"ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሳለን ነው ያወቅሁት። የአንድ ጓደኛዬ የቅርብ ጓደኛ ስለነበር፣ በርሷ ምክንያት ነው የተዋወቅነው።"

"ጓደኛሽ ማን ናት- ማለቴ የአፈወርቅ ጓደኛ ?"

"ንግሥት ናትናኤል።"

"ጥሩ። የንግሥትና የአፈወረቅ ጓደኝነት በምን መልክ ነበር?"

"በወንድምና በእህትነት መልክ ነበር።"

"ርግጠኛ ነሽ ?"

"አዎ።"

"ንግሥት የአፈወረቅ ፍቅረኛ ነበረች የሚሉ አሉ። ምን አስተያየት አለሽ?"

"ውሸት ነው። ከእኔ የተደበቀ ምንም ነገር የለም። በርግጥ፣ በጣም የሚቀራረቡ ጓደኛሞች ስለነበሩ፣ በብዙ ቦታዎች አይለያዩም። ይህ ሁኔታ፣ በእኛ ህብረተሰብ ዘንድ አዲስ በመሆኑ ነው መሰል፣ ፍቅረኛሞች ናቸው እያሉ ሰዎች ያወሩ ነበር።"

"አፈወርቅ በምን እንደሞተ የምታውቂው ነገር አለ?"

"ተሰቅሎ ነው፣ ሲባል የሰማሁት።"

"ለምን የተሰቀለ ይመስልሻል?"

"እኔ እንጃ። ይሄ እስካሁን መልስ ላገኘለት ያልቻልኩት ጥያቄ ነው።"

"ንግሥት ለአፈወርቅ በጣም የምትቀርበው ከመሆኗ የተነሳ፣ አፈወርቅ ራሱን ሊገድል የወሰነበትን ምክንያት በትክክል ባታውቅም፣ ልትጠረጥር ትችላለች የሚል ግምት አለን። ስለ አፈወርቅ መሞት ምክንያት ያጫወተችሽ ነገር አለ?"

ትንሽ እንደማሰብ አለች። "አዎ። አፈወርቅ እናትና አባት የሉትም። ያሳደጉት ሰው ዘመዱ አይደሉም። ብቸኛ በመሆኑ፣ ብዙ ጊዜ እንደሚበሳጭ ትነግረኝ ነበር። ይሄ ብስጭቱ ሊሆን ይችላል ራሱን እንዲሰቅል ያደረገው የሚል እምነት አላት።" ስትል መለሰችለት።

"መልካም። ወይዘሪት ሲሳይ፣ ጓደኛሽ ንግሥት የኤድስ ህዋስ ተሸካሚ ነች ይባላል። እውነት ነው?"

ሲሳይ ክው ብላ ቀረች። ምንም መልስ አልሰጠችም።

መርማሪው ሁኔታዋን አየና፣ "ገበየሁ ሁሉቃ የሚባሉ ሰው፣ ተሰማ የሚባል ልጃቸውን ገድለው፣ እጃቸውን ለፖሊስ ሰጥተዋል። የአባትና የልጁ አለመግባባት የተፈጠረው፣ ልጁ የኤድስ ቫይረስ ሰለባ ሆኖ በመገኘቱ፣ ከቤት እንዳይወጣና ጉዳዩ ታውቆ የቤተሰቡ ስም እንዳይጎድፍ በሚመክሩት ጊዜ፣ ፈቃደኛ ካለመሆኑ የተነሳ በተፈጠረ ጭቅጭቅ ነው የሚል እምነት ላይ ደርሰናል። ካደረግነው ምርመራ፣ አፈወርቅ የተሰማን የኤድስ ቫይረስ ሰለባ መሆንን የሚያውቅ ብቸኛ



ሰው በመሆኑ፣ አቶ ገበየሁ ወሬ እንዳይዋጣ-የልጃቸው ምስጢር-አፈወርቅን አስገድለው፣ ራሱን የሰቀለ አስመሰሉ የሚል ነገር አግኝ ተናል። ይህንኑ ጉዳይ ለአቶ ገበየሁ ሁሌቃ ገልፀን፣ የእምነት ክህደት ቃላቸውን እንዲሰጡን ጠይቀን ነበር። አፈወርቅ በሰው ሳይሆን የተገደለው፣ የኤድስ ቫይረስ ስለያዘው፣ ራሱን ሰቅሎ ነው የሚል ቃል ሰጥተውናል።

"አቶ ገበየሁ የሰጡንን ቃል እውነትነት ለማረጋገጥ የአፈወርቅ የቅርብ የሴት ጓደኞችን ሁኔታ ማጥናት ነበረብን። አፈወርቅን በጣም ትቀርብ የነበረችው ያንቺው ጓደኛ ንግሥት ናትናኤል፣ በዚሁ በሽታ ተይዛለች የሚል ፍንጭ ከአንዳንድ ሰዎች አግኝተናል። ይህንኑ ለማጣራት ነው ወደ አንቺ የመጣሁት። ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ የአፈወርቅና የንግሥት ግንኙነት አንቺ እንዳልሽው በወንድምና በእህትነት አልነበረም።"

"በዚህ በኩል እንኳ አትጠራጠር። ንግሥትና አፈወርቅ የፍቅር ግንኙነት አልነበራቸውም።"

"ጥሩ። የኤድስ ቫይረስ ሰላባ ነች የሚባለውስ?"

"ምንም የማውቀው ጉዳይ የለም።"

"ርግጠኛ ነሽ ?"

"አዎ!" አለች።

መርማሪው ፖሊስ አመስግኗት ወጣ።

ሲሳይ ፍዝዝ ብላ ቀረች። ከመርማሪው ጋር ያደረገቻቸው ቃለ-ምልልሶች፣ እረፍት አልሰጧትም። የሰማችው የአፈወረቅ ታሪክ፣ በመጽሐፍ ላይ ያነበበችው ልብ ወለድ ነው የመሰላት። የንግሥትና የአፈወርቅ ጓደኝነት ፍጹም በሆነ ወንድምነትና እህትነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ብታውቅም፣ በልቧ ውስጥ ጥርጣሬ ነገሠ። ግርማ የነገራት-በርሱና በንግሥት መሀል የነበረው ግንኙነት የተቋረጠበትን ምክንያት-አስታወሰች።'አፈወርቅ በትክክል ራሱን ሰቅሎ ከሆነ፣ እውነት ነው ማለት ነው። ንግሥት ኤድስ ይዟታል ማለት ነው። አባቷ፣ ዶክተር ናትናኤል ንግሥት በአፈወርቅ ለቅሶና ቀብር ላይ እንዳትገኝ ያደረጉት፣ አፈወርቅ በትክክል የሞተው፣ እርሷ ባስያዘችው በሽታ ቢሆን ነው።' ስትል ደመደመች። ዳንኤል ከንግሥት ጋር ወሲባዊ ግንኙነት አድርጎ ይሆን? እንደዚያ ከሆነ ዋጋ የለውም።' አለች አሁንም በሀሳቧ።

በርግጥም የዳንኤልና የንግሥት ፍቅር ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ የምታውቀው ነገር የለም። አንድ ጊዜ ከንግሥት ጋር ኃይለ ቃላት ከተለዋወጡ በኋላ፣ ተገናኝተው ተነጋግረው አያውቁም።

## 45

በብዙ ድካምና መከራ ያገኘችውን የዳንኤልን መኖሪያ ቤት የስልክ ቁጥር ከጻፈችበት ብጣሽ ወረቀት ላይ እያነበበች፣ የስልኩን ቁጥሮች አዞረች። ዳንኤልን ለማዳን ያላት ብቸኛ መንገድ የንግሥትን በህዋሱ መለከፍ ፍርጥርጥ አድርጋ ለርሱ በመንገር፣ መሆኑን አምናለች። የንግሥት በበሽታው መለከፍ-አለመለከፍ፣ በትክክል እስኪታወቅ ድረስ፣ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ጉዳዩን ለዳንኤል ለመንገር ወስናለች።

"ሀሎ !"አለ ስልኩን ያነሳው ሰው።

"ዳንኤልን ፈልጌ ነበር እባክዎ። "

"ዳንኤል አልገባም።"

"የት ላገኘው እችላለሁ? በጣም ፈልጌዋለሁ። ይህ አራተኛዬ ነው ስደውል። ይመጣል፣ ትንሽ ቆይቼ ልደውል?" ስትል ጠየቀች፣ የእጅ ሰዓቷን እያየች። ከምሽቱ አራት ሰዓት ሆኗል።

"አይመጣም ዛሬ።"

"እሺ ጠዋት ይኖራል፣ ልደውል?"

"አይመስለኝም ። ሶደሬ ነው የሄደው።"

"ከማን ጋር?" ስትል ሳይታወቃት ጮኸች።

የዳንኤል አባት በሁኔታዋ ግራ ገብቷቸው፣"ማን ነሽ አንቺ?" ሲሉ ጠየቁ።

"እኔን አያውቁኝም።" አለችና ንግግሯን አቋረጠች። ልቧ ተሰቅሏል። "ከንግሥት ጋር ነው የሄደው?"

"መሰለኝ። ንግሥት ናት የምትባል ፍቅረኛው ?"ሲሉ ጠየቁ።

ሲሳይ ጨነቃት። የምታደርገው ጠፋት። ዘግይታ መደወሏን ተረዳች። ይሁንና ተስፋ አልቆረጠችም። "አሁን እንዴት ልንረዳው እንችላለን? ህይወቱን ማዳን አለብን !"ስትል ጮኸች።

"እንዴት? ምንድን ነው? ምን ተፈጠረ?" ሲሉ አባትየው



በተጨነቀና በድንጋጤ ስሜት ሆነው ጠየቋት።

ሲሳይ ሁሉንም ነገር ዘክዝካ ነገረቻቸው....

## 46

ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት ተኩል ሆኗል። የበረሀ ገነት በምትባለዋ የሶደሬ መዝናኛ ቦታ፣ በመካሄድ ላይ ያለው የዲስኮ ዳንስ ከተጀመረ ጥቂት ሰዓታት ተቆጥረዋል። ዳንኤልና ንግሥት ዳንሱ ከተጀመረበት ደቂቃ አንስቶ፣ እንዳሁኑ ለረጅም ደቂቃዎች አላረፉም። በዳንሱ ብቻ ሳይሆን፣ ቀን ሲዋኙና የሶደሬን ውስጥና አካባቢ በእግሮቻቸው እየተዘዋወሩ በመዋላቸው ድካም እያጠቃቸው ነው።

ዳንኤል ወንበሩን በጀርባው ደገፍ ብሎ፣ አንድ እጁን ከጎኑ ባለ ወንበር ላይ የተቀመጠችው ንግሥት ትከሻ ላይ ጣል አድርጎ፣ በመደነስ ላይ ያሉትን ሰዎች ፣ያያል ። ፊቱ በላብ ርሷል። ንግሥት ጭንቅላቷን ዳንኤል አንገት ውስጥ ሸጉጣ በመደነስ ላይ ያሉትን ሰዎች፣ በአግድሞሽ ታያለች። ከፍተኛ ድካም ተሰምቷታል። በተከራዩት የመኝታ ክፍል ውስጥ ገብታ ብትተኛ ደስታውን አትችለውም ነበር። ይሁንና፣ ሶደሬ እንሂድ የሚለው የዳንኤል ግብዣ ከአፉ ከወጣ ጀምሮ፣ በውስጧ ሲላወስ የሰነበተው ፍራቻ የተመኘችውን እንድታደርግ አልፈቀደላትም። ሲያኝካት የዋለው ሥጋት፣ ቀኑ ለመምሸት ደቂቃ በጨመረ ቁጥር፣ ሥቃይዋን እያበረታባት ነው የሄደው።

ፈጣኑ ሙዚቃ አለቀና ለስላሳው ሙዚቃ ቀጠለ።

"ንግሥትዬ፣ ተነሽ እንጫወት።" አለ ጎንበስ ብሎ እያያት።

"ውይ ዳኒ! ደክሞኛል። "

"እኔም ደክሞኛል። ለመጨረሻ ጊዜ በዚህች ሙዚቃ እንጫወት።"

ተነሳች።

ወደ ዳንሱ ክልል ገቡ። ደረቱ ላይ ልጥፍ አደረጋትና ፊቱን አንገቷ ሥር ሸጉጦ፣ ደብዛዛውን ብርሀን እየዘለቀ በሚንቆረቆረው ለስላሳ የእንግሊዝኛ ሙዚቃ፣ መወዛወዝ ጀመሩ። ሁለቱም፣ አትኩሮታቸውን በዚያች ደቂቃ በፈጠሯት የፍቅር አለም ውስጥ አድርገው፣ ተቃቅፈው ሲደንሱ፣ አንድ አካል ይመስሉ ነበር። መሳ ለመሳ የገጠሙ ደረቶቻቸውን ሰንጥቀው፣ ልቦቻቸው የእውነተኛ ፍቅር

መልዕክት ሲለዋወጡ፣ ከንፈሮቻቸው አንዱ ለሌላው የያዙትን የፍቅር ወለላ ለማበርከት፣ አንዴ ሲተሳሰሩ፣ ሌላ ጊዜ ሲለያዩ፣ አጭሯ ለስላሳ ሙዚቃ ድንገት እልቅ አለች።

'የሚጣፍጥ ነገር መቼም አይበረክትም።' የሚል አረፍተ ነገር በሁለቱም ግንባሮች ላይ ተነበበ።

"ይብቃን። አይደል?" ሲል ጠየቃት፣ ዳንኤል ንግሥትን እያያት።

ጥያቄውን ቶሎ አልመለሰችም። ዳንሱን ፈልጋ ሳይሆን 'በቃን' ካለች ቀሪውን ሌሊት ለማሳለፍ ወደ ክፍላቸው መሄዳቸው አይቀርም። ይህ ደግሞ የምትጠላው ነገር ነው።

ዳንኤል መልሷን አልጠበቀም። ወገቧን አቅፎ ወደ መኝታ ክፍላቸው የሚወስደውን መንገድ ይዞ መራመድ ጀመረ። መኝታ ክፍላቸው ገቡ። መብራቱን አበራ። ከአልጋው ጎን ካለ ወንበር ላይ ቁጭ አለ። ንግሥት ዝም ብላ ቆመች። ውስጧ መረበሹን ጠይም ፊቷ አሳየው። ብድግ ብሎ እጆቹን ትከሻዋ ላይ አድርጎ፣ አይኖቿን ሊያያቸው ሲሞክር አቀረቀረች። እንደዚህ የምትጠላቸውን ደቂቃና ቦታ ከእንግዲህ ወዲያ መታገስ እንደማትችል አመነች። ከእንግዲህ ወዲያ፣ ራሷን፣ ልቧ ላመቀው ፍቅር ብላ፣ ማሰቃየት እንደሌለባት ወሰነች። የምትወደውን ሰው፣ እርሷ በተዘፈቀችበት የሥቃይ ውቅያኖስ ውስጥ መንከሩ፣ ህሊና የማይችለው ግፍና የፍቅር አምላክ የማይሽረው ሀጢአት ሆኖ አገኘችው። ሁሉንም ነገር ግልጽልጽ አድርጋ መናገሩ ተገቢ መሰላት። ግን እንዴት አድርጋ የመጀመሪያውን ቃል እንደምታወጣ ጨነቃት። በምትነግረው ዜና የምትወደውና የሚወዳት ዳንኤል ሲሳቀቅ ማየቱ፣ ቫይረሱ ካደረሰባት የሥነ-ልቦና ጭንቀት የበለጠ አስፈራት። ግን፣ የሚመጣውን ሁሉ ለመቻልና ዜናውን ለመንገር ወሰነች።

"ሴክስ ማድረጉ ነው አይደል ያስጨነቀሽ?"

"አዎ!" አለች ቀና ሳትል።

"አይዞሽ አትስጊ። አንቺ ካልፈለግሽ ምንም ነገር አይደረግም። መቼም ቢሆን፣ አንቺ ካልፈለግሽ፣ አላስገድድሽም። እሺ?"

ቀና ብላ አየችውና በእፎይታ አንገቱ ላይ ጥምጥም አለች። ዕንባ ተናነቃት። ግን አላለቀሰችም። ከንፈሮቹን በከንፈሮቿ ዳሰስ አደረገችና ከአጠገቡ ፈንጠር አለች። ከአልጋው ላይ ተቀመጠች።



"መጣሁ የሚጠጣ አዝዤ። "አለና ከመኝታ ክፍሉ ወጣ።

ንግሥት በአንገት እንቅስቀሴ እሺታዋን ገልፃ ጫማዋን ካወለቀች በኋላ፣ አልጋው ላይ ጋደም አለች። ኮርኒሱ ላይ፣ ትላልቅ ዓይኖቿን አነጣጥራ ስለ ዳንኤል ማሰብ ጀመረች። በየጊዜው የሚያሳያቸው ድርጊቶች፣ ይበልጥ እንድትወደው፣ እንድታከብረው፣ እንድታመልከው እያደረጓት እንጂ ፣ እንድትርቀው አላደረጓትም። 'ምን አይነት የዋህና ፍጹም የሆነ ሰው ነው? ዓለማችን እንደዚህ ያለ እውነተኛ ሰው በውን ይዛለች?' ሁሉም ነገር እውነት አልመስል አላት። እንደ ዳንኤል ያለ ፍቅረኛ፣ በምኞት ዓለም እንጂ በውን ያለ አልመሰላትም። በራሷ ላይ የደረሰው አደጋ-በኤድስ ህዋስ መያዝ-ራሱ እውነት አልመሰላትም። ሌሊት የሚታይ፣ መጥፎ ህልም ሆኖ ነው ያገኘችው።' ሁሉም ነገር እውን ባይሆን ምናለ?" ስትል ራሷን ጠየቀችና እንደገና ደግሞ፣ ሁኔታው እውነት ባይሆን፣ ዳንኤልን እንደምታጣ ስትገነዘብ፣ ቅር አላት። 'ጌታዬ! አምላኬ! ሰማይና ምድርን የፈጠርክ አምላክ ! ምንም የማይሳንህ አምላክ! እባክህ አድነኝ! እባክህ ፈውሰኝ! የምወደውንና ለወደፊት ህይወቴ መሠረት የሆነን ሰው፣ ሰጥተህ አትንሳኝ! እባክህ ስማኝ ጌታዬ!' ስትል ተማፀነች-በልቧ።

ጠርሙስ ውስኪ፣ ብርጭቆዎችና የአምቦውሀ ጠርሙስ ይዞ ገባ ዳንኤል። በሩን ቆልፎ አልጋው ላይ ተቀመጠ።

"እንዴ !ጠርሙስ ሙሉ ውስኪ! ምን ያደርጋል?"

"ለክብርሽ ስል ያወረድኩት ነው!"

"አመሰግናለሁ። "አለች ፈገግ ብላ። "ግን ይህን ሁሉ ማን ይጠጣዋል?" ስትል ጠየቀች።

"የሚበቃንን ያህል ጠጥተን የተረፈውን እንተወዋለን።" አለና ውስኪውን ከቀዳ በኋላ አቀበላት። የግራ እጇን ኮንዶ፣ አልጋው ላይ አስመርኩዛ፣ በመዳፏ ጭንቅላቷን ደገፍ አድርጋ፣ በቀኝ እጇ ተቀበለችው።

"ደክሞሻል። አይደለም?"

"በጣም እንጂ።" ብላ ፉት አለች። "ለምን ሞላኸው እንዲህ ?"

"እንድትጠጪ።"

"ዛሬ በጣም ነው የጠጣሁት።"

"በዳንሱ ምክንያት በላብ ወጥቷል።"

ዝምታ ሰፈነ።

"አልደከመህም?"

"ደክሞኛል። "

"ና ጋደም በል።"

ጫማውን አውልቆ፣ ከጎኗ በጀርባው ጋደም አለ።

አሁንም ፀጥታ ሰፈነ።

ሁለቱም በየግል ሀሳባቸው ሰመጡ።

ወሲባዊ ግንኙነት እንደማያደርጉ ዳንኤል ቃል ቢገባላትም፣ ንግሥት ልታምን አልቻለችም። ዳንኤልን ሳይሆን ያላመነችው፣ በሁለታቸው ውስጥ የመሳሳብ ሀይል ያላቸውን ስሜቶች ነው። ወንድና ሴት- ያውም በፍቅር ብስል ያሉ -አንድ አልጋ ላይ አድረው፣ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ሳያደርጉ ማለፍ ያስችላቸዋልን? ይህ ሁኔታ፣ እንደገና ሥጋት ላይ ጣላት። የዳንኤል ህይወት፣ እንደገና አደጋ ላይ መሆኑን አወቀች።

ዳንኤል ሊያነሳሳት ያቀደውን ጉዳይ አሁን ለመጀመር አሰበ። ግን ወኔ አላገኘም። ፈራ። ተወው። ጉዳዩን በቀጥታ ከማንሳት በፊት፣ ድርጊት መቅደም አለበት ብሏል። ይሁንና፣ አንድ ጥያቄ ማንሳት ፈለገ። "የሚያስጨንቅሽ ነገር እንዳለ ይሰማኛል። "አለ፣ በጥያቄ ሳይሆን፣ የመሰለውን አስተያየት እንደመስጠት ብሎ።

ንግሥት ምንም አልተናገረችም።

"አይደለም?"

አሁንም ዝም አለች።

"ንግሥትዬ አትደብቂኝ። ከእኔ የሚደበቅ ነገር ያለሽ አይመስለኝም። ንገሪኝ?"

"ምኑን?"

"አንድ የሚያስጨንቅሽ ነገር አለ።"

"እም። "አለች፣ ዝቅ ባለ ድምጽ።

"ንገሪኝ። ልስማውና እንወያይበት።"

'ከልብ የሚወዱትን ፍቅረኛን እስከመጨረሻው የሚያባርር ነገር እንዴት ይነገራል? እውነተኛ ፍቅር በታጣበት ዘመን፣ ፍቅር ተቀብሎ ፍቅር በመስጠት የህይወት ጥላ የሆነን ሰው እንዴት እንዲሸሽ ይደረጋል? ቢሆንም እውነቱ ሊነገረው ይገባል። ከልብ የሚወደድ ሰው ሥቃይ ውስጥ መግባት የለበትም። ቢርቅም፣ ደህንነቱን ከሩቅ



ሆኖ መስማት፣ ከማንኛቸውም ነገሮች የበለጠ ያስደስታል። እነግረዋለሁ። ግን አሁን መሆን የለበትም። መርዶ በጨለማ አይነገርም። ይንጋ።' አለች ንግሥት ለራሷ። "ዳኒ ሁሉንም ነገር ጠዋት እነግርሀለሁ። አሁን ተወኝ ።ታገሥ። "አለች፣ እርሷም በጀርባዋ ተንጋላ ጣራ ጣራውን እያየች።

በማግሥቱ የምትነግረው አትመስልም። ዳንኤልን በምንም መንገድ ለማጣት እንደማትፈልግ ልቧ ያውቀዋል። ፍቅር ማለት ስግብግብነት ማለት ይሆን?

ዳንኤል በእሺታ ዝም ከማለት ሌላ፣ አልተናገራትም። ይሁንና፣ በውስጧ ያለው ሌላው እሷነቷ አላሳረፋትም። ጭቅጭቁን ቀጠለ። 'ለምን አትነግሪውም? እስከ ጥዋትስ ለምን ታቆይዋለሽ? አሁኑኑ ንገሪው። እስኪነጋ የሚፈጠረውን ማን ያውቃል? ነገር ከሆነ በኋላ ከመፀፀት፣ አሁኑኑ ፍርጥ አድርጊው!አሁኑኑ ንገሪው!....ንገሪው!!!'ሲል ጮኸባት። ለዳንኤል ነግራ ልታሳርፈው አልቻለችም። 'ዳንኤል ቢያንስ ይቺን ሌሊት፣ያለ ሀዘን ማሳለፍ አለበት' ብላ ወሰነች። የዳንኤልን ልብ የሚሰብር ነገር፣ በውድቅት ጨለማ መናገር እንደሌለባት አመነች። እየጮኸ የሚያስቸግራትን እርሷነቷን ለመግደል፣ ዓይኖቿን ጨፍና በብርጭቆ የተቀዳውን ውስኪ፣ ጅው አደረገችና ከጠርሙሱ ውስጥ ሌላ ቀዳች። ውሀ እንደጠማው ሰው -እንደቀደቀችው።

ዳንኤል ትኩር ብሎ ከማየት ሌላ፣ ለጊዜው የሚያደርገው ጠፋው። እንደገና ከጠርሙሱ ውስጥ ልትቀዳ ስትል፣ እጇን ያዘው። "ንግሥትዬ በቃሽ ! ከዚህ በላይ ከጠጣሽ ልብሽ ፈንድቶ ትሞቻለሽ።" አለ፣ በማባባል ዓይነት።

'የምፈልገውም ይህንኑ ነው!ተወኝ!' ልትል ፈልጋ ተወችው።

"ደክሞሻል። ተኚ። " አለ ብርድ ልብሱን እየገለጠላት።

ቀሚሷን ሳታወልቅ፣ እንሶላዎቹ ውስጥ ገባች። የገዛ ጭንቅላቷ ይከብዳት ጀመር። ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል፣ በአንድ እርሷነቷ ውስጥ የተፈጠሩት ሙግቶች ለጊዜው እረፍት ቢያሳጧትም የጠጣችው ውስኪና ድካም ጥቃት ስላደረሱባቸው፣ ዕንቅልፍ ቀረባት። ይዞአት ጭልጥ አለ።

በንግሥት ላይ ያደረው ስሜት በርሱ ላይ ሰፍሮ ቢያዝንም፣ ይህ ሁኔታ ከዛሬ ወዲያ እንደማይደገም በመገመት፣ የተሰማው ጥልቅ ሀዘን እየሟሸሸ ነው። ዛሬ ሁሉንም ነገር አድርጎ በርሱና በንግሥት

ፍቅር መሀል የቆመውን ችግር ለማጥፋት ወስና ነበር። ሶደሬን የመረጠው ይህንኑ ዕቅድ ለማሳካት ነው። ንግሥትን የማስከር ዕቅድ ቢኖረውም፣ እንዴት አድርጎ እንደሚያደርገው ጨንቆት ነበር። ይሁንና፣ በራሷ አነሳሽነት የጨለጠችው ውስኪ ራሷን አሳልፋ ለዳንኤል እንድትሰጥ አደረጋት። አተኩሮ አያት። ረጅም ጥቁር ፀጉሯ ትራሱ ላይ እንደ ቄጠማ ተነስንሷል። የአንፖሉ ብርሀን፣ ጠይም ፊቷ ላይ የሚነበበውን ውበቷን አፍክቶታል። እንጆሪ የሚመስሉ ከንፈሮቿን አልገጠመቻቸውም። የሚጋብዙት መሰለው። የወሲብ ፍላጎቱ ተቀሰቀሰ። ከአልጋው ላይ በጥንቃቄ ተነሳ። ወደ መታጠቢያ ክፍሉ አመራና ከሴኮንዶች ቆይታ በኋላ ተመለሰ። አሁንም አተኩሮ አያት። ውበቷ ከደቂቃ ወደ ደቂቃ እየጨመረ የመጣ መሰለው። ጃኬቱን፣ ሸሚዙንና ሱሪውን አውልቆ አልጋው ውስጥ ገባ። የልቡ ትርታ ጨመረ። የድንጋጤ ስሜት ግንባሩን አወረዛው። እጁን ንግሥት ጡቶች ውስጥ ላካቸው።

ንግሥት ምንም እንቅስቃሴ አላሳየችም።

ከንፈሮቿን በከንፈሮቹ ዳሰሳቸው።

ምንም እንቅስቃሴ አላሰየችም።

ብርድ ልብሱን ገለጠው። ቀሚሷንም ገለጠው። ነጭ የውስጥ ሱሪ አድርጋለች። የልቡ ትርታ ፍጥነት አደነቆረው። የውስጥ ሱሪዋን አወለቀው።

ንግሥት ንቃት የሌለው እንቅስቃሴ አሳየች እንጂ ከዕንቅልፍ አለም አልወጣችም።

ዳንኤል በትዕግስት ትንሽ አደፈጠ። የሞተች ትመስላለች። ነፍሷን አታውቅም። ከጥቂት ሴኮንዶች በኋላ ተከታይ ርምጃውን ቀጠለ። በመጨረሻ ያሰበው ተሳካለት....

ንግሥት በሰመመን ነቃ ብላ እንደገና ጠፋች.....

## 47

ስካሩና ድካሙ እንደገና ለዕንቅልፍ አሳልፎ ቢሰጣትም፣ እስከዛሬ ስትሸሸው የነበረው ጊዜ ደርሶ፣ የተፈጠረው ነገር፣ በሰመመን ውስጥ ሆና ቆረብሻት ነበር። የህሊና ወቀሳው፣ ከአልኮልና ድካም ሀይል ጋር ግብግብ ፈጥሮ፣ ሲነጋጋ ገደማ ሙሉ ድል በመቀዳጀት የንግሥትን አእምሮ ወሯል። አሁን ንግሥት ሙሉ ለሙሉ ነቅታ፣ ከጥቂት ሰዓታት በፊት የተፈጠረውን በክለሳ መልክ ማየት ጀመረች። ራሷን መውቀስ፣ ራሷን መጥላት ፣ ራሷን መስደብ



ጀመረች–በልቧ። ይህ ሁሉ ለሰራችው በደል ካሣ ሆኖ አልተገኘም። ዳንኤልን ወደ ሞት መንደር ውስጥ በማስገባቷ፣ ራሷን ከፋኛ ኮነነች። ሳታስበው እንባች የደም ዕንባ። ከዚህች ዓለም ለመሰወር አቀደች። መቼ? ቶሎ እንዲሆን ተመኘች። ከእንግዲህ ወዲያ ህሊናዋን በማቁሰል፣ በማድማት፣ ለአንዲት ሴኮንድ ያህል እንኳ በትዕግሥት መቆየት አልፈለገችም። ቶሎ ለመጥፋት ጓጉታለች–ሞት የሚያጓጓ ሆኖ።

ፊቷ በዕንባ መራሱን ዳንኤል እንዳያውቅባት ብላ፣ ለመታጠብ ከአልጋው ላይ በጥንቃቄ ተነሳችና ወደ መፀዳጃ ክፍሉ አመራች። መብራቱን አብርታ፣ ፊቷን በመስታወት አየችው። ዓይኖቿ ቀልተው፣ ውሀ ሳይሆን ደም የሚያነቡ ነው የመሰሉት። መስታወቱን ማየት ትታ፣ በመፀዳጃ ቤቱ ውስጥ ያሉትን ዕቃዎች ቃኘች። ራስን መግደል የሚያስችሉ ነገሮች የሉም። ተበሳጨች። የምታደርገው ጠፋት። ሽንቷ የመጣ መሰላት። የተጨማደደ ቀሚሷን ከፍ፣ የውስጥ ሱሪዋን ዝቅ አድርጋ፣ የመፀዳጃው ሳህን ላይ ቁጭ አለች። ምንም የወጣት ነገር አልነበረም። ተነሳች። ድንገት አንድ ነገር ትውስ እንዳላት ነገር፣ ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ፍዝዝ አለች። ሴትነቷን ጎንበስ ብላ አየችው። ከወንድ ጋር ግንኙነት ማድረጓን የሚያሳይ ምልክት አላየችም። በእጇ ዳበሰችው። ምንም ነገር አልነገራትም። 'ራሴ የፈጠርኩት ሥጋት ይሆን? ነገሩ ሁሉ በህልሜ ያየሁት ነገር ይሆን? መሆን አለበት። ዳኒ አላደርግም ያለውን ነገር፣ ቃሉን ሰብሮ አይፈጽምም። በህልሜ ነው' አለች ለራሷ። ህይወት እጥቶ የነበረው ፊቷ እንደገና ለመለመ። የዕንባ ጎርፍ ነግሶባቸው የነበሩት ጉንጮቿ በደስታ ፈገግ ማለት ጀመሩ። ከት ብላ ልትስቅ ፈለገች። ግን አልቻለችም። በውስጧ ሳቀች። ለጥቂት ሴኮንድ ያህል በዚህ ሁኔታ ከቆየች በኋላ፣ የውስጥ ሱሪዋን ከፍ ማድረግ ጀመረች። ድንገት አንድ ትክክል ያልሆነ ነገር አየች። ተገልብጧል።' ገልብጬ ነበር እንዴ የለበስኩት? ሊሆን አይችልም።' ነገሩ ሁሉ የተደረገው በህልሟ ይሁን በውኗ መለየት አስቸገራት። በተጨነቀ ስሜት ውስጥ ሆና ወደ መኝታ ክፍሉ ገባች።

ዳንኤል እንደ ግንድ ተጋድሟል።

መኝታ ክፍሉ ገባች እንጂ ምን ማድረግ እንዳለባት ማወቅ አልቻለችም። ከአልጋው ጎን ካለ ወንበር ላይ ተቀመጠች። ኮምዲኖውን ከፈተች። የተረፈ ውስኪ በጠርሙስ ውስጥ አገኘች። አንስታ ጨለጠችው።

ድንገት ዳንኤል ነቃ። ዓይኖቹን ጨፈን ከፈት አድርጎ አተኩሮ አያት። ግራ ገባው። ጠርሙሱን ሊነጥቃት አልቻለም። ጠጥታ ጨርሳዋለች።

"ምነው ንግሥት?" አለ። ማለት የሚችለው ይህንን ብቻ ነበር።

"ምነው?" ብላ ጮኸችበት።

ደንግጦ ዝም አለ። የእጅ ሰዓቱን አየ። ከጠዋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ከሀምሳ ደቂቃ ሆኗል።

"አሁን ተነስና ወደ ቤቴ መልሰኝ።"

"እሺ።" አለ በዝግታ። አልጋው ላይ ተንጋሎ ጥቂት በማሰብ ቆየ። ስቅስቅ ብላ አለቀሰች።

ከአልጋው ላይ ተነስቶ ተጠጋት። የተቀመጠችበት ወንበር ላይ በጫፉ ተቀምጦ፣ እጁን ትከሻዋ ላይ ጣል በማድረግ፣ ሊያባብላት ሞከረ።

"ንግሥትዬ? አይዞሽ! ምንም የሚያስጨንቅሽ ነገር የለም። ሁሉም ነገር አንቺ እንደሰጋሽው አይደለም። አይሆንምም። ምንም ሆንሽ ምንም እወድሻለሁ። አትጨነቂ። ልለባብስና ቁርስ በልተን ቀስ ብለን እንሄዳለን።" አለና ልብሶቹን ለባብሶ ወደ መፀዳጃ ክፍሉ አመራ።

ዳንኤል፣ የተጨነቀችበትን ነገር የተረዳላት አልመሰላትም። ድንግል ነኝ ብላው በማታለሏ፣ ተፀፅታ ያዘነች ሆና የታየው ነው የመሰላት።

ፊቱን ታጥቦ ከመጣ በኋላ፣ የጉዞ ሻንጣውን የጎን ኪስ ከፍቶ ማበጠሪያ አወጣ። ፀጉሩን አበጠረና አያት። "ፊትሽን ታጠቢውና ፀጉርሽን አበጣጥሪ።"

ዝም አለች።

ጎንበስ ብሎ ፊቷን አየው። "ንግሥቴ፣ አንቺ፣ ተነሽ ታጠቢ። ምንም የሚያስጨንቅ ነገር የለም። ከዚህ ወጥተን ናዝሬት እንገባና ቁርስ እንበላለን። የዛሬውን ቀን እዚያ አሳልፈን ሲመሽ ወደ አዲስ አበባ እንሄዳለን። እሺ?"

"ቀጥታ ወደ ቤቴ ነው መሄድ የምፈልገው! አልችልም!" ስትል፣ ሳይታወቃት ጮኸች። ጋብ ብሎ የነበረው ዕንባዋን እንደገና አዘነበችው።

ዳንኤል ጨነቀው። ንግሥትን ካባበለ በኋላ፣ ረፈድ ሲል፣ ሊነግራት ያሰበውን መንገር የሚችል አልመሰለውም። እዚሁ ለመንገር ተገደደ። ግን እንዴት ብሎ እንደሚጀምር አላወቀም።



ንግሥት ስታለቅስ፣ እሱ በዝምታ ሆኖ ጥቂት ሴኮንዶች አለፉ።

"ንግሥትዬ፣ አንድ ነገር ልጠይቅሽ ?"

አልሰማችውም። አጠገቧ ሄዶ እንደ ቅድሙ ተቀመጠ። ቀና ብላ ሳታየው ማልቀሷን ቀጠለች። ከእንግዲህ ወዲያ ዳንኤልን በሙሉ ዓይኖቿ ማየት የምትችል አይመስልም።

አንድ ጊዜ፣ ሊያደርግላቸው ስላሰበው የገንዘብ እርዳታ ለመነጋገር በንግሥት ቀጠሮ አዘጋጅነት ከዶክተር ናትናኤል ጋር ባደረጓቸው ቃለ-ምልልሶች ውስጥ ልቡን እንደ ሸክላ እንክት ያደረጉት ቃላት ትውስ አሉት።

"በእውነቱ፣ የዚህን በሽታ መድሀኒት ለማግኘት በማደርገው ሙከራ በገንዘብ ድጋፍ ከእኔ ጎን በመቆምህ እጅግ አመሰግንሀለሁ። በህሙማኑ ስም ሆኜ በጣም አመሰግናለሁ።" አሉ ዶክተሩ ፊታቸው እየበራ።

"ኧረ ምንም አይደለም። ለአለም ህዝብ የሚጠቅም ነገር ለመፍጠር የሚዘጋጅን ሰው መርዳት ደስታ ይሰጠኛል። ይህንን እድል ስለሰጡኝ ላመሰግኖት የሚገባኝ እኔ ነኝ።" አለ ዳንኤል ፈገግ ብሎ። ከዚያ በኋላ ሁለቱም የቀረበላቸውን ቡና እየጠጡ ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ዝም አሉ።

"ዳንኤል፣..."አሉ የቡና ስኒያቸውን ከፊት ለፊታቸው ካለው ጠረጴዛ ላይ እያስቀመጡ።

ንግግራቸው ስለተቋረጠ ቀና ብሎ አያቸው።

"ንግሥትን ምን ያህል ትወዳታለህ?"

ግራ የሚያጋባ ጥያቄ ሆነበት።

"እሷ በጣም እንደምትወድህ አውቃለሁ።"

"እኔም በጣም እወዳታለሁ።" አለ ዳንኤል።

ዶክተሩ ሀሳብ ገብቷቸው ዝም አሉ–ለሴኮንዶች ያህል። "ከአንተ ጋር በቀጠሮ ለመገናኘት የፈለኩበት ዋና ምክንያት፣ ስለምታደርግልኝ የገንዘብ እርዳታ ለመነጋገር አይደለም። ሌላ ጉዳይ አለኝ።" ብለው ዝም አሉ። "የሩካቤ ሥጋ አድርጋችሁ ታውቃላችሁ?"

አስደንጋጭና አሁንም ግራ የሚያጋባ ጥያቄ ሆነበት።

ዶክተር ናትናኤል፣ ንግሥትና ዳንኤል የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት አድርገው ከሆነ፣ ስለንግሥት የኤድስ ህዋስ ተሸካሚ መሆን ላለመናገር ወስነዋል–ዳንኤል ሥጋት እንዳያድርበት ብለው። እስካሁን

ካላደረጉ ግን፣ እውነቱን ነግረው ግንኙነቱን እንዲያቋርጥ ለማድረግ አስበዋል።

"እይዞህ፣ ንገረኝ።"

"አድርገን አናውቅም።"አለ፣ ለስለስ ባለ አነጋገር።

"እውነቱን ንገረኝ፣ ዳንኤል። ግልጽ ሰው እንደሆንክ ንግሥት ነግራኛለች።

"አይጠራጠሩኝ። እውነቴን ነው።"

"ስንት ጊዜ ሆናችሁ እስካሁን?" ሲሉ ያልተሟላ የጥርጣሬ ጥያቄ አቀረቡ።

"አጋጣሚ አጥተን ሳይሆን፣ ንግሥት ማድረግ የማትፈልግበትን ምክንያት ስላመንኩበት ነው።"

ነቃ ብለው በመጓጓት አይነት እያዩት፣ "ምንድ ነው ይሄ ምክንያት?" ሲሉ ጠየቁ።

"ድንግል ነኝ ብላ ስለነገረችኝና ከጋብቻ በፊት ማድረግ እንደማትፈልግ ስላወቅሁ ነው።" አለ ዳንኤል።

ዶክተር ናትናኤል በእፎይታ አየር ካስወጡ በኋላ፣ ዝም አሉ። ልጃቸው የሰጠችው ምክንያት ፣ ዳንኤልን ከወሲብ ግንኙነት ሊገድበው የሚችል መስሎ ቢታያቸውም፣ ዘላቂ መፍትሄ መሆኑን አላመኑም። ወንድ፣ ድንግል ናት የተባለች ሴት ስታጋጥመው፣ ክብረ ንጽህናዋን ወስዶ የራሱ ለማድረግ የሚጣደፍ መስሎ ይታያቸዋል። ስለዚህ ፣ ለዳንኤል ሊነግሩት የፈለጉትን ዜና ከመንገር ወደ ኋላ ማለት አልፈለጉም።

"ዳንኤል፣ እውነቱ እሷ የነገረችህ አይደለም። እርሷ ለአንተ የምትሆንህ ልጅ አይደለችም።"

"እንዴት?" አለ ዳንኤል፣ ደንግጦ።

"ባለጌ ናት ወይም መጥፎ ፀባይ አላት ማለቴ አይደለም። ልጄ ፍጹም ጨዋ መሆኗን አውቃለሁ። በዚህም መቶ በመቶ እተማመናለሁ።" ብለው እንደማሰብ ዝም አሉ።

ዳንኤል በጉጉት አያቸው።

"አንድ ጊዜ በጠና ታምማ ነበር። ደም አስፈልጓት እኔ ሰጠሁኝ። እኔ የሰጠሁት ከእርሷ ደም ጋር ባለመመሳሰሉ ለርሷ የሚሆን ሌላ ደም ከሆስፒታል ተፈልጎ ተሰጣት። በዚያን ጊዜ ስለ ኤች አይ ቪ ቫይረስ የሚታወቅ ነገር ባለመኖሩ፣ ሳይመረመር ከልጄ ደም ውስጥ ተቀላቀለ። "ብለው ንግግራቸውን አቋረጡ።



ዳንኤል በድንጋጤ፣ ሀውልት ሆኖ አያቸው። በጆሮዎቹ ውስጥ የገቡት የዶክተሩ ቃላት እንደ እንጨት አደረቁት። ከፊቱ ላይ ይነበብ የነበረው የድሎት ወዝ እስፖንጅ ላይ ጠብ እንዳለ ውሀ ተመጠጠ።

"ከወንዶች ጋር በመግባባት ያገኘችው አደጋ አይደለም። ከዚህ በፊት ያየችው ወንድ መላኩ የሚባል አንድ ሰው ብቻ ነው። ምርመራ አድርገንለት ቫይረሱ በእርሱ ደም ውስጥ እንደሌለ አረጋግጠናል። ከእሱ ከተለየች፣ አንድ ዓመት ከምናምን ወራት አልፈዋል። በዚህ ጊዜ ውስጥ፣ ግርማ ከሚባል ልጅ ጋር ፍቅር ጀምራ ነበር። ሆኖም፣ ብዙ ሳይቆዩ የንግሥትን መለከፍ ስለተረዳሁ፣ አድኘዋለሁ። አሁን አንተም ይህ ችግር ሳይደርስብህ ግንኙነታችሁን ማቋረጥ አለብህ።" አሉ ሀኪሙ።

ዳንኤል ለአንድ ደቂቃ ያህል የሚናገረው ጠፍቶት ከቆየ በኋላ፣ ከመቀመጫው ተነሳ–ለመሄድ።

"አዝናለሁ፣ እንዲህ ያለ መጥፎ ዜና ስለነገርኩህ።"

ዳንኤል አሁንም አልተናገረም።

"አንድ የምለምንህ ነገር አለ። ቶሎ አትራቃት። ቀስ በቀስ፣ እያላመድክ አድርገው። ምክንያቱም፣ በጣም ትወድሀለች። አሁን ለገጠማት ችግር ጥሩ ማጽናኛ ሆነህ እንደነበር አምናለሁ። አንተን ስታጣ፣ ሥቃይዋ እጥፍ ሊሆን ስለሚችል፣ ከዚህ አደጋ ውስጥ እንዳትገባ የተቻለህን አድርግላት።"

ከአፉ የወጡ ቃላት አልነበሩም። ሳይሰናበታቸው ከክሊኒካቸው ወጣና እያለቀሰ፣ መኪናው ውስጥ ገባ።

ከዚያ በኋላ፣ ለአንድ ሁለት ቀናት ያህል የገጠመው የመንፈስ ችግር እንዲህ ነው ተብሎ የሚገመት አልነበረም። በህይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የወደዳትን ሴት የሚያሳጣ አስደንጋጭ ዜና በመስማቱ የባዶነት ስሜት አድሮበታል። ይህን ባዶነት ለመጋፈጥ የሚያስችል ወኔ አላገኘም። በምኑም፣ በምኑም ንግሥት ትዝ እያለችው ከፊቱ ድቅን እያለች ታሰቃየዋለች። እንባዋን እንደሾላ እያረገፈች ስትማፀነው፣ ስታስጨንቀው ትታየዋለች።

'ዳኒ፣ ህይወቴ፣ አምላኬ ነህ ብዬ ስመካብህ ፣ ሸሸኸኝ? ዳኒ፣ የኔ ጌታ፣ እረ ተው አትጨክን። ስለፍቅር አምላክ ብለህ ዳኒ፣ በባዶ ሜዳ ላይ አትጣለኝ። በዚህች ዓለም ላይ ከአባቴ ቀጥሎ የማምነውና የምመካበት ሰው አንተ ብቻ እንደሆንክ አልነገርኩህም? ታዲያ ምነው፣ ህይወት ስትከዳኝ፣ ህይወት ስትቀጣኝ የምትከዳኝ? ወድጄ

ያመጣሁት ነገር እኮ አይደለም? ዳኒ፣ እንደሰው ማግጨ ወይም ቀብጨ ያገኘሁት አደጋ እኮ አይደለም። ዳኒ እያወቅኸው? በስንቱ ልቀጣ? ዳኒ በስንቱ!'

አልፎ አልፎ ልቡ በሀዘን ቢሸረሸርም፣ ከእርሷ ጋር ያለውን የፍቅር ግንኙነት ሊገፋበት አልደፈረም። የሚያስፈራራው የራሱ የሆነ ስሜት ብቅ ይልበታል።

'ዳንኤል ራስህን አትወድም? እናትህንና አባትህን አትወድም? አንድ አንተ ብቻ እኮ ነህ ያለህቸው። አንተ የምትሆንህን መርጠህ አግብተህ፣ የልጅ ልጅ እንድታሳያቸው ሲመኙ፣ ጭራሽ አንተ አንድ ልጃቸውን፣ የዓይናቸቸው ብቸኛ ማረፊያን፣ ልትቀጨው ነው? አስብ እስኪ። ፍቅር አያሸንፍህ። ንግሥትን ብታጣ፣ ሌላ ሴት መተካት ይቻላል እኮ። በአለም ላይ ስንት ውብ የሆኑ፣ በማንኛውም ረገድ ከእሷ የሚበልጡ ሴቶች አሉ። ተው አትሳሳት። ተምረህ እንዳልተማረ አትሁን።'

'ተምረህ እንዳልተማረ የምትሆነው፣ ባለብኝ ችግር ሸሽተህ ሌላ ሴት ስትይዝ ብቻ ነው። አትሳሳት። ባዶ ሜዳ ላይ ጥለኸኝ ከሄድክ ትዝብት ውስጥ ትገባለህ። እስቲ አስብ፣ ዳኒ። በዚህች ዓለም ላይ ያለኸኝ ተስፋ እኮ አንተ ብቻ ነህ። አንተ ፊት ከነሳኸኝ እኮ አንድም ቀን በዚህች ምድር ላይ አላድርም። የእኔ መሞት ለህሊናህም ጥሩ አይደለም እኮ ዳኒ። አስብ ዳኒ። ራራልኝ ዳኒ። ዳኒ!'

እነዚህ የርሱ አእምሮ የፈጠራቸው ሙግቶች ካደረሱበት የሥነልቡና ችግር ለመውጣት ያላገላበጣቸው መጻሕፍት የሉም። ብዙ የህክምና አዋቂዎችንም አነጋግሯል። መፍትሄ የሚሉትን ነግረውታል። ከዚያ በኋላ ነው እዚህ ውሳኔ ላይ የደረሰው።

"አንድ የሰማሁት ነገር አለ። እውነት ይሁን አይሁን ግን፣ ማወቅ አልቻልኩም። አንቺንም መጠየቅ ፈርቼ ቆይቻለሁ። ነገር ግን፣ አንዳንድ የምታሳይአቸው ድርጊቶች የሰማሁት ነገር እውነት መሆኑን እያሳወቁኝ መጥተዋል። ሰው የነገረኝ እንድሸሽ ነበር። ግን አልቻልኩም። ለጥቂት ቀናት ከአንቺ ለመለየት ሞከርኩ። ከንቱ ድካም ሆኖ አገኘሁት። በጣም እወድሻለሁ። ያለ አንቺ መኖር እንደማልችል አመንኩኝ። ብዙ ጊዜ ከራሴ ጋር ሙግት ፈጥሬ ነበር፣ ነገሩን ከሰማሁ በኋላ። ግን የተረዳሁት ከአንቺ ተለይቶ መኖር እንደማይቻል ነው። የደረሰብሽ ችግር የመጣው ፈልገሽው ሳይሆን፣ በአጋጣሚ መሆኑን ተገንዝቤአለሁ። ስለዚህ እንዴት ልሸሽ? ብቻ ፈጽሞ አልቻልኩም።



ነገሩን አንቺ እንስተሽው እንድንወያይ ፈልጌ ነበር። ነገር ግን ልትነግሪኝ አልቻልሽም። እኔም አንስቼ እንድንነጋገርበት የሚያስችል ወኔ አላገኘሁም። ጉዳዩን ማወቄን ከተረዳሽ ትሸሽኛለሽ ብዬ አፍኜ አቆየሁት። ንግሥትዬ፣ በጣም እንደምትወጂኝ አውቃለሁ። በደረሰብሽ ችግር ልርቅሽ አልፈለኩም። እኔ ጤነኛ አንቺ ደግሞ ህመምተኛ – መድሀኒቱ እስኪገኝ ድረስ – ሆነሽ ፍቅራችንን የምንቀጥልበትን መንገድ የህክምና አዋቂዎችንና የሥነልቦና ምሁራንን ጠይቄ በነገሩኝ ዘዴ ከአንቺ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደረግሁ። ያስፈቃድሽ በማድረጌ ይቅርታ።" ብሎ ፊቱ ላይ በድንጋጤ ያሳረፈቻቸውን ዓይኖቿን አተኩሮ አየ።

ዲዳ መስላ ቆመች።

"የሠጋሽው ነገር አልተፈጠረም። በኮንዶም ነው የተጠቀምኩት። እንዲህ እያደረግን ፍቅራችንን እንቀጥላለን ለማለት ነው።"

ንግሥት ፍጹም የሆነ፣ እስካሁን በህይወት ዘመኗ ያላየችው ደስታ፣ በእርሷነቷ ውስጥ ሲወራጭ ተሰማት። ዕንባ እንቅ አደረጋት የደስታ። ዳንኤል አንገት ላይ ተጠመጠመችበት - በፍቅር። ከዚያም ከንፈሮቹን....

## 48

ሻምበል አርአያ የቀይ ዳማ ፊቱ በንዴትና በቁጭት ዳምኖ፣ አለቃው ቢሮ ውስጥ ለመግባት ተራውን እየተጠባበቀ ነው። በወታደር ዲሲፕሊን፣ ካለቃ ጋር አፍ መካፈት ከረር ያለ ቅጣት የሚያስከትል መሆኑን ቢያውቅም፣ ደንታው አልሆነም። እኚህ አለቃው ከዚህ ቀደም 'ጋጠወጥ ነው። በሥራው ምስጉን አይደለም።' ብለው ሁለት ጊዜ የማዕረግ ዕድገት እንዲታለፈው አድርገዋል። የዚህ ብስጭት ቁስል ሳይሽር፣ እጁ የገባውን የውጭ ሀገር የትምህርት ዕድል ያጨናገፉበት መስሎ ታይቶታል። ይህንን ጥቃት ግን በዝምታ ሊያልፈው አልፈለገም። ጓደኞቹ ሲሾሙ እርሱ በመታለፉ፣ተራርቀዋል። ይህንን ሁኔታ በትዕግስት ማሳለፍ አልቻለም።

ከጥቂት ሴኮንዶች በኋላ ከአለቃው ቢሮ ውስጥ ገባ። ጠይም፣ ግርማቸው የሚያስፈራ ሰው የመኮንን ልብስ ለብሰው ጉብ ብለዋል።

አርአያ በወጉ ሰላምታ አላቀረበላቸውም። በቀጥታ ወደ መጣበት ጉዳይ ገባ። "ጌታዬ ከዚህ በፊት፣ ለእርሶ በመስልዎ ልዩ ልዩ ጉዳዮች፣ ማግኘት የሚገቡኝን የማዕረግ ዕድገቶች አጥቼአለሁ። አሁን

ደግሞ፣ ለብዙ ዓመታት በናፍቆት ሲጠብቀው የነበረውን የውጭ ሀገር ትምህርት ዕድል እንዴት ይነፈገኛል?" ሲል ጮኸ።

አለቃው ትኩር ብለው አዩት። አነጋገሩ ክብራቸውን ያጎደፈባቸው ያህል ቆጣ አሉ። "ምን ይፈጠር ነው የምትለው?" አሉ። ከንዴታቸው የተነሳ ለመናገር የፈለጉትትን በወጉ ያወቁ አይመስሉም።

"ተበድያለሁ ነው ያልኩት።" አለ፣ ረጋ ባለ አነጋገር።

"ባለፉት ጊዜያት የማዕረግ ዕድገት እንዲታለፍህ የተደረገው፣ መልካም ሥነ ምግባርና የሥራ ብቃት ስለሌለህ ነው። ይህንን ራስህም ታውቀዋለህ። ጋጠ ወጥ ነህ። አሁን ያሳየኸው ተግባር ራሱ ለህግ የሚያድር መኮንን ቀርቶ፣ አንድ ተራ ወሮበላ የማያደርገው ነው! ውጣልኝ አሁን! ከአንተ ጋር ምንም ዓይነት ንግግር የለኝም!" አሉ። ቁጣቸው ቃላት በጨመሩ ቁጥር እየናረ የሚሄድ ይመስላል።

እርሱም ግልፍ አለው። "እስከመቼ እበደላለሁ? እኔ ለዚህች ሀገር የእንጀራ ልጅ ነኝ? ለሀገሬ እኔም እየደከምኩ ነው? እሺ ዕድገቶቼ ፀባይ የለህም ተብዬ ታለፉኝ። የአሁኑን ዕድል ለምን አጣለሁ? ይሄን ብቻ መልሱልኝ?"

"አላውቅም!"

"እንዴት አያውቁም?" ሲል ጮኸ። 'እጅግ ቢከፋ ለሰው ልጅ አስቸጋሪ የሆነ ቦታ ቢወረውሩኝ ነው፣ ከዚህ የባሰ ሊመጣ አይችልም' የሚል ስሜት ከግንባሩ ላይ ይነበባል።

"ሰውዬ ውጣ! እንዳላስጠፍርህ!"

"ግድ የለኝም። ለመብቴ ስል የተሰጠኝን እቀበላለሁ። ግን በዘመድ አዝማድ መሥራት ይቅር! የሆነ ያልሆነ ምክንያት ፈጥረው መበደሉ..."

"ሰውዬ የትም ስትልከሰከስ ባመጣኸው ችግር ነው ልትቀር የቻልከው! የህክምና ምርመራ ውጤትህን ሰምተሀል?" አሉና አፈጠጡበት። ንዴት ፊታቸው ላይ መንተግተግ ጀምሯል። ትክክለኛና ኀበዝ ከፍተኛ መኮንን የመሆናቸውን ያህል ሲናደዱ የሚመልሳቸው ኃይል ያለ አይመስልም። ግልፍተኛ በመሆናቸው ያናደዳቸውን ሰው፣ ባመቻቸው መንገድ የመበቀል ባህርይ እንዳላቸው ይነገርላቸዋል። ብዙ ዘመን የሚያውቋቸው ሰዎች ግን፣ እልም ያለ በርሀ ውስጥ ብዙ ዘመናት በመሥራታቸው፣ ተለክፈው ነው በማለት ያዝኑላቸዋል። "ስማ



የትም ስትልከሰከስ ባመጣኸው ችግር ነው የትምህርት ዕድሉ ያልተሰጠህ!" ሲሉ ጮኹበት።

ሻምበል አርአያ በንዴት ዓይኖቹን አጉረጥርጦ፣ "ምንድን ነው መልከስከስ? ምን ሳደርግ ታይቼ ነው እንዲህ የሚሉኝ?" ሲል ከጣሪያ በላይ አለቃው ላይ ጮኸ።

"የኤድስ ቫይረስ ተሸካሚ መሆንህ ተረጋግጧል! ይህ ነው ከሀገር እንዳትወጣ ያደረገህ!" ሲሉ በቁጣ አረዱት።

ሻምበል አርአያ የግንባሩ ሥሮች ተግተርትረው፣ ዓይኖቹ ከጉርጓዶቻቸው ለመውጣት ያህል ተጎልጉለው፣ ጆሮዎቹ እንደ ቀንድ ቆመው አለቃውን አያቸው።

በሻምበል አርአያ ፊት ላይ የታየው የድንጋጤ ስሜት አለቃውን ረገብ አደረጋቸው። ሳይታወቃቸው የተናገሩት ነገር መልሶ ርሳቸውኑ ፀፀታቸው።

## 49

እሁድ ጠዋትን ናዝሬት፣ ከሰዓት በኋላንና ሌሊቱን ደግሞ ፣ በደብረዘይት ከተማ በሆራ ራስ ሆቴል አሳልፈው፣ ሰኞ ረፋዱ ላይ አዲስ አበባ ገቡ። ንግሥትን ቤቷ ድረስ ከመሸኘቱ በፊት፣ ወደ መኖሪያ ቤቱ ደርሶ ትንሽ እረፍት ለማድረግ በመፈለጉ፣ ጉዞውን ቀጠለ–ወደ ቦሌ።

"ወዴት ነው የምንሄደው?" ስትል ጠየቀች፣ንግሥት።

"ቤቴ እንድንደርስ ፈልጌ ነው። ትንሽ እረፍ እንበልና አደርስሻለሁ።"

"አባዬ ሊሰጋ ይችላል። እሁድ ማታ እመለሳለሁ ብዬ ስጠፋ መጨነቁ አይቀርም።"

"ከቤት ትደውይላቸዋለሽ።"

ተስማሙ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፣ መኖሪያ ቤቱ በር ሲደርሱ መኪናዋ ቆመች። ዳንኤል ጥሩንባ አሰማ።

የዳንኤል መምጣት በመኪናዋ ድምጽ ሲሰማ፣ እናቱ፣ አባቱና አንድ የእኅቱ ልጅ፣ ከዋናው ቤት በችኮላ ወጡ። ዳንኤል መኪናውን ግቢው ውስጥ አስገብቶ እስኪቆምና ከመኪናው ንግሥትና እሱ ወርደው ወደ እነሱ እስኪመጡ ድረስ፣ ዓይኖቻቸውን

እንዴ በንግሥት ላይ ሌላ ጊዜ ደግሞ በዳንኤል ላይ እያፈራረቁ ከሌላ ዓለም እንደመጡ ልዩ ፍጡሮች አዩአቸው።

ዳንኤል የቤተሰቡ ያልተጠበቀ ሁኔታ ለጊዜው ቢያስደነግጠውም፣ ምን እንደተፈጠረ ከመጠየቁ በፊት ተገቢ ሰላምታውን አቀረበላቸው። "ተዋወቂያቸው።" አለ፣ በእጁ እየጠቆማት።

ንግሥትና የዳንኤል ቤተሰቦች ተዋወቁ–በመጨባበጥና ስሞቻቸውን በመናገር።

"ፍቅረኛዬ ብዬ ያሚወትኳችሁ እሷን ነው።" አለ ዳንኤል፣ ፍዝዝ ብለው የቀሩትን የቤተሰቡን አባላት አይቶ።

ምንም መልስ አልሰጡትም። ለርሷም ግቢም ውጭም አላሏትም። የሚናገሩት የጠፋቸው ይመስል አቀርቅረው ዝም አሉ።

"ንግሥቴ፣ ነይ ወደ ቤቴ እንሂድ።" ብሎ እጇን ይዞ እየመራ፣ በግቢው ውስጥ ወደሚገኘው መኖሪያ ቤቱ መራመድ ጀመረ። ጥቂት ርምጃዎች እንደተራመዱ ስሙ ሲጠራ ተሰማው።

"ዳንኤል!" ሲሉ በድጋሚ ጠሩት አባቱ።

በዝግታ ዞር ብሎ አያቸውና፣ "አቤት!" አለ። አንድ እንግዳ ነገር እንደተፈጠረ ሳይገባው አልቀረም።

"ለጥብቅ ጉዳይ፣ በአስቸኳይ ላነጋግርህ እፈልጋለሁ።" አሉ፣ አባትየው ፍጹም የሆነ ሀዘን በፊታቸው ላይ እየታየ።

ጥቂት ዝም ብሎ ካያቸው በኋላ፣ "እሺ መጣሁ። "አለና ንግሥትን ይዞ ወደቤቱ ገባ። "ንግሥቴ መታጠብ እፈልጋለሁ ስትይ ነበር። እነ አባባን እስካነጋግራቸው ድረስ ታጠቢ። ወደ ቤትሽ ስልክ እደውላለሁም ብለሽ ነበር። መኝታ ቤት ገብተሽ መደወል ትችያለሽ። መጣሁ።" ብሎ ወላጆቹና የእኅቱ ልጅ ወደ ነበሩበት ቦታ ተመለሰ። "ለደህና ነው የተፈለኩት?"

አባትና እናቱ ወደ መኖሪያ ቤታቸው ሲገቡ፣ ዳንኤል የእኅቱን ልጅ በጥያቄ ዓይነት እያየው ተከተላቸው። ሳሎኑ ሰፊ ነው። ወለሉ እጅግ በሚያምር ምንጣፍ ተሸፍኗል። በሳሎኑ ቅርጽ የተሰራው ባለአበባ ሶፋ ለዓይን ትልቅ ደስታ ይሰጣል። የምግብ ጠረጴዛው የለበሰው ኽርንጉርጉር ጨርቅ ለሳሎኑ ተጨማሪ ውበት ሆኖታል። ከሶፋ ወንበሮቹ ፊት ለፊት የዳንኤል አባትንና እናትን ፎቶግራፎች የተሸከሙ ግዙፍ ቴሌቪዥንና ዴክ ተቀምጠዋል። ቅርንጫፎች ያሏቸው አራቱ ትላልቅ አምፖሎች አልበሩም። በየግድግዳዎቹ ላይ የተሰኩት ጌጠኛ መብራቶች ግን ደብዘዝ ያለ ብርሃን እየረጩ ነው።



"ይህን ሰሞን የት ከረምክ?" ሲሉ ጥያቄአቸውን ጀመሩ፣ አባትየው። ጠይም ፊታቸው በሀዘን ዳምኗል።

"ነግሬህ አልነበር እንዴ? ሶደሬ ነበርኩ።"

"ትናንት እዚያ መጥተን ስናስስ አላጣንህም?"

"ከሶደሬ የወጣነው ጠዋት ነው። ትናንት የዋልኩትና ያደርኩት ናዝሬትና ደብረዘይት ነው።" አለ ዳንኤል።

ለምን ጉዳይ ሶደሬ ድረስ መጥተው እንደፈለጉት ሊገባው አልቻለም። እጅግ አስቸኳይ ችግር እንደተፈጠረ አወቀ። ምንነቱን ለማወቅ ጓጓ፣ ደነገጠም።

"ጥሩ። እሱን ተወው። አሁን የሚፈለገው ጉዳይ እሱ አይደለም። ከዚህች ልጅ ጋር..." አሉና እንዴት አድርገው ጥያቄያቸውን መፍጠር እንደሚችሉ ቸግሯቸው። ንግግራቸውን አቋረጡ።

ዳንኤል በመጨነቅ አባቱን አየና ዓይኖቹን ወደ እናቱ ፊት ወረወረ። የእናቱ ዓይኖች እንባ አቅርረዋል። ቀይ ፊታቸው ገርጥቷል። ተስፋ በመቁረጥ ስሜት ከማየት ሌላ ፣ የተናገሩት ቃል አልነበረም።

"ከዚህች ልጅ ጋር ነው ሶስቱንም ቀን የከረምከው?" አሉ፣ የዳንኤል አባት።

"አዎ።" አለ፣ ግራ በመጋባት ስሜት ውስጥ ሆኖ።

"እና አንድ አልጋ ላይ አብራችሁ አደራችኋል?" ሲሉ ልባቸው በተሰቀለ ስሜት ጠየቁት። ይህ ጥያቄ የአባትየው ብቻ ሳይሆን፣ የእናቱም ነበር።

ዳንኤል አንድ ፍንጭ አገኘ። ቤተሰቡ የተጨነቀበት ነገር ገባው። ግን እንዴት እንደሰሙ ሊረዳ አልቻለም። ሊጠይቃቸው አልደፈረም። ላነሱት ጥያቄ መልስ ሰጥቶ ቤተሰቡን ሊያረጋጋ ፈለገ። "አዎ።" አለ ዳንኤል፣ ረጋ ብሎ ጥፋቱን እንደሚናዘዝ ሰው።

አባትየው ግልጽ ሳያደርጉ ላነሱት ጥያቄ፣ ግልጽ የሆነ መልስ ባለማግኘታቸው፣ ጥያቄውን በሌሎች ቃላት ደገሙት። "የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት አድርጋችኋል?"

"አላደረግንም። እስከዛሬ አላደረግንም።" አለ፣ ቤተሰቡን ለማረጋጋት።

እናትየው መሬት ሳሙ። አባትየው ደግሞ ጣራ ጣራውን እየተመለከቱ፣ "ተመስገን አምላኬ! ተመስገን አንዱን ልጃችንን ከሞት ባህር ጠልቀህ በጥበብህ ያወጣህልን አምላክ ፣ ተመስገን! ምስጋና

ይድረስህ!" አሉና እሳቸውም መሬት ሳሙ:: ከዚያ በኋላ፣ ሚስታቸውን ሳሙ:: "ተመስጌን አምላኬ! አሁን ላንተ ምን ይሳንሀል?" አሉ፣ ወደ ሰማይ አንጋጠው::" የኔ አምላክ የት ሄዶ? መጸሚ፣ መፀለዬ፣ እሱን ለማገልገል አይደል? እንዴት አድርጎ ያሳፍረኛ?" አሉ በደስታ እየተፍነከነኩ::

"ምንድነው ነገሩ አባባ?" ሲል ጠየቀ፣ ጉዳዩ ያልገባው በመምሰል::

ሶፋው ላይ ቁጭ አሉ:: "እስኪ መጀመሪያ ተቀመጥ:: ግድየለም ትደርስበታለህ:: መጀመሪያ ተቀመጥ::"

ዳንኤል ተቀመጠ::

"ዳንኤል፣ የዚህችን ልጅ ውስጠ ምስጢር የሚያውቅ ሰው ነግሮናል:: ልጅቷ ለአንተ የምትሆን አይደለችም:: እርሷ አግድም አደግ በመሆኗ፣ ከማንም ጋር ስትማግጥ የኖረች ናት::" አሉ አባት::

"ማን ነው እንዲህ ያለው?" አለ፣ ትንሽ ግንባሩን ቋጥሮ::

"የሰውየው ማንነት ምን ያደርግልሀል? ልጅቷ ለእንደ አንተ ዓይነቱ፣ በሥርዓት አድጎ ለተማረ ሰው፣ የምትሆን አይደለችም:: ባለጌ ናት::" አሉ ሽማግሊው::

"ፍጹም ውሸት ነው:: ልጅቷን የማያውቅ ሰው ነው የነገረህ:: እርሷ በዚህ ወራዳ ተግባር የምትሰለፍ ልጅ አይደለችም:: ከጥሩ ቤተሰብ፣ በደንብ ከተማረ ቤተሰብ የወጣች ልጅ ናት:: ለዚህ ጥሩ ምስክር የሆነኝ ከተዋወቅንበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ያየሁት ፀባዩዋ ነው::"

"ተው አይደለም:: ልክ አይደለህም፣ አንተ ልጅ:: እሷን በደንብ ከሚያውቃት ሰው ነው የተነገረኝ::" አሉ አባት::

"ሀሰት ነው:: ከእኔ የበለጠ ሊያውቃት የሚችል ሰው አይኖርም:: እኔና እሷን ለማጣላት ያቀደ ሰው ነው የነገራችሁ::" አለ ዳንኤል::

"አንተና እሷን ለማጣላት ሰው ለምን ይፈልጋል?" አሉ እናት::

"ተንኮለኛ ሰው ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩት ይችላል::"

"አይመስለኝም:: የነገረኝ ሰው ባንተ ተመቅኝቶ ሳይሆን፣ ለአንተ አዝኖ፣ በአንተ ላይ አደጋ እንዳይደርስ ተጨንቆ ነው:: የአንተ ህይወት አደጋ ላይ መሆኑን አይቶ እንድትጠነቀቅ ያሰበልህ ሰው ነው::" አሉ አባትየው::



"ትክክል አይደለም:: ደግሞ እኔና እርሷ ከተግባባንና ከተዋወቅን ማንም የፈለገውን ቢል አልቀበልም:: ዋናው የእኔና የእሷ መግባባትና መዋደድ ነው:: ሌላው ትርፍ ነው::"

"ተው ልጄ የሚወራው ሌላ ነገር ነው:: እንዲህ ቀላል ነገር አይምሰልህ::" አሉ አቶ ፈጠነ::

"ምንድነው የሚወራው?"

"ለመናገርም የሚቀፍ ነው ልጄ::" አሉ አባትየው::

"ምንም የሚቀፍ ነገር አይደለም:: በሽታዋ በቅርብ [illegible] መድሀኒት የሚገኝለት ዓይነት ነው::"

"እ?... ሰምተሀዋል ማለት ነው?" አሉ፣ ነቃ በማለት::

"አዎ፣ ሰምቼዋለሁ::" አለ ዳንኤል፣ ነገሩን በማቃለል ዓይነት::

"ታዲያ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ለመቅጣት ያመጣው በሽታ ነው መድሀኒት የሚገኝለት? ይሄ እኮ ለእኩዩች የወረደ መቅሰፍት ነው:: እንዴት ብለህ ነው ከእንደዚህ ዓይነት ሰው ጋር የምትጎዳኘው?"

"አባባ፣ የተሳሳትክ መሰለኝ:: በዓለማችን ለጥቂት ዓመታት ሰውን ሲያሰቃዩ ከቆዩ በኋላ፣ መድሀኒት የተገኘላቸው ብዙ የበሽታ ዓይነቶች ታይተዋል:: ይህንንም ከእነዚህ የሚለየው ነገር የለም:: የጊዜ ጉዳይ ነው:: እንዳልከው እግዚአብሔር ያመጣብን ቅጣት አይደለም::" አለ ዳንኤል::

"እኔን አስተምራ! መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ልትክደው ነው?" አሉ በመገሰጽ ዓይነት::

"አሁን ሌላውን ዘርዝርና ሙግት ተውትና ዳንኤል የምትባለውን ስማ:: ባልጠፋ ሴት ምነው እርሷ ላይ ሙጭጭ አልክ? ስንት የሚሆኑህ ጨዋ ሴቶች እሉ::" አሉ እናትየው በማባበል ዓይነት::

"እማማ፣ ከዚህች የበለጠ ጨዋ ላገኝ አልችልም::"

"ድንቂም ጨዋ! ጨዋ በመሆኗ ነዋ በሽታው የያዛት!" አሉ አባት በመሳለቅ::

"አባባ፣ ንግሥት እኮ ከብዙ ወንዶች ጋር ስትንዘላዘል አይደለም አደጋ ላይ የወደቀችው:: ሆስፒታል ውስጥ በተሠራ ስህተት ነው::" አለና ዶክተር ናትናኤል አንድ ጊዜ የነገሩትን ታሪክ ነገራቸው::

"ብቻ፣ ያም ሆነ ይህ ፣ እርሷ ከእንግዲህ ወዲያ ሶስት አራት ዓመታት ብትኖር ነው። ሞታለች እንጂ፣ በህይወት አለች አይባልም።"

"ለእኔ በህይወት አለች፣ አባባ። ልክዳት ወይም ልሸሻት አልችልም። በህይወት እስካለች ድረስ፣ የሥቃይዋ ተካፋይ ሆኘ እቆያለሁ። ይህ ሁኔታ ደግሞ፣ በእኔ ህይወት ላይ የሚያደርሰው እንዳችም ጉዳት የለም።"

"ምን ማለቱ ነው ይሄ? ምን ታደርግልኛለች ነው የምትለው? ጊፄ ለገና መድሀኒት ይገኛል ብለህ ነው፣ ያለ እሷ ሞቼ እገኛለሁ የምትለው?" አሉ እናት።

"ባይገኝም፣ በህይወት እስካለች ድረስ ልለያት አልችልም።"

"ታመሀል ልበል? ወትሮ ብልህ፣ አርቆ አሳቢ አልነበርክ? ምን ነካህ ?" አሉ አባት።

"ምንም አልነካኝም።"

"ታዲያስ ከማይሆንህ ሰው ጋር ምን አንገታገተህ? በከተማው ስንት ሴት ሞልታ፣ ነገ ቅጥፍ በምትል ልጅ ላይ ምንድን ነው ችክ የሚያደርግህ ?" አሉ አባትየው።

"ለእኔ ከባድ ነው። ሌላ ሴት በእጮኛነት የምይዘው የእርሷን መጨረሻ አይቼ ነው።" አለ ዳንኤል።

"እስከዚያው ቆመህ ልትኖር ነዋ! እኛ የአንተን ልጆች ለማየት ስንቸኩል፣ ምንድን ነው እንዲህ የሚያደርግህ ?" አሉ እናት ቆጣ ብለው።

"እማማ፣ ማድረግ የማልችለውን ነገር ማድረግ አልችልም።" አለ ፍርጥም ብሎ።

"አንተ ልጅ ምን ነክቶሀል ? እሷን ስታስታምም ጊዜ ጥሎህ እንደሚሄድ አታውቅም? ዛሬ ዕድሜህ ስንት እንደሆነ ታውቃለህ?" አሉ አባት።

"አዎ።"

"ታዲያስ! የልጅ ልጅ ለማየት ምን ይቀርህ ነበር! ምን የጎደለህ ነገር አለ? ትምህርትህን ጨርሰሀል። እንፈላሶ የሚያኖርህን ድርጅቴን ሰጠሁህ። መኖሪያ ቤት አለህ። መኪና ገዝተሀል። ከዚህ ወዲያ ምን ትፈልጋለህ?" አሉ አባት።

"ጥቂት ዓመታት።" አለ ዳንኤል።

"ለምን?" ሲሉ አባትና እናት በአንድ ጊዜ ጠየቁ።



"የንግሥትን ሁኔታ እስካውቅ።"

"ጅል! ከረፈፍ! ልብህን ሰለበችው መሰል!" ሲሉ ተቆጡ አባት።

ዳንኤል ተነስቶ ለመውጣት ተዘጋጀ።

"እኔ ነግሬሀለሁ! አስብበት! እንቢ ያልክ እንደሆነ፣ እኔም አባትህ አይደለሁ፣ እሷም እናትህ አትሆንም! አዎ! ያ ብቻ አይደለም። ይሄ የገዛሁልህና የሰጠሁህን ንብረትና መተዳደሪያ ንግድህን ሁሉ መልሼ እወስደዋለሁ!" አሉ አባት በቁጣ።

ዳንኤል፣ 'እውቀቴን ሽጬ መኖር እምችል ሰው ነኝ!' ለማለት ፈልጎ ተወው። ዝም ብሎ ወጥቶ ወደ ግል መኖሪያ ቤቱ ሄደ።

## 50

ሲሳይ ያለችበት ቢሮ ውስጥ ያለው ስልክ ጮኸ። አነሳችው። በጆሮዋ ውስጥ የተላለፈውን ድምጽ ወዲያው ለየችው። ዛሬ ብቻ አራት ጊዜ ደውሎላት ነበር። አራቱንም ጥሪዎች ሳታነጋግረው በጆሮው ላይ ዘግታበታለች።

"ሲሳይ ነሽ ?" አለ ደዋዩ።

"አዎ።"

"አርአያ ነኝ።"

"እኔ የምለው አይገባህም? ከአንተ ጋር መነጋገርም ሆነ አንተን ማየት አልፈልግም! ስንት ጊዜ ልንገርህ? ለምን እየደወልክ ታስለቸኛለህ?" አለች፣ ረገብ ባለ ቁጣ።

"እባክሽ ሲሳይ። ለምን ጨካኝ ትሆኛለሽ? ያለፈውን ነገር እያስታወሽ ለምን እንዲህ ትሆኛለሽ? አጥፍቻለሁ። በዚያ በመፀፀት ይቅርታ ልጠይቅሽ እፈልጋለሁ። ሰው ያጠፋል። ሰው በመሆኔ ተሳስቻለሁ። ያስከፋሁትንና የበደልኩትን ሰው ይቅርታ መጠየቅ እፈልጋለሁ።" አለ ሻምበል አርአያ።

የሲሳይ ልብ መለስ ማለት ጀመረ። "ይቅርታውን ተቀብዬዋለሁ። በቃ። መገናኘቱ ግን አልታየኝም። የሚያስፈልግ አይመስለኝም።"

"ተይ እንጂ ሲሱ:: መገናኘት ያስፈልገናል:: ሰላም መባባል አለብን እኮ::"

"የአሁኑ መገናኘት አያስፈልግም:: ስንገናኝ ሰላም እልሀለሁ:: በቃ:: ከዚህ በላይ መታረቅ አለ?"

"ሲሳይ፣ በድቄሻለሁ:: የሰራሁት ጥፋት ይቅርታ የሚበቃው አይመስለኝም:: ልክስሽ እፈልጋለሁ::"

"ምንም ዓይነት ካሣ አልፈልግም:: አስፈላጊ አይደለም::"

"ተይ እንጂ:: ተገናኝተን ሻይ ቡና ማለት የለብንም? ብዙ አላቆይሽም እኮ:: ግፋ ቢል ሰላሳ ደቂቃ ያህል አብረን ብንቆይ ነው:: ከዚያ ወዲያ በተገናኘን ጊዜ ሰላም እንባባላለን:: እንደአስፈላጊነቱም እንገናኛለን::"

"እኔ ምለው ይቅር ብያለሁ ማለቴን አላመንከም ማለት ነው?"

"አሱማ አምኛለሁ:: ግን አእምሮዬ ይበልጥ ደስ እንዲለው... ብንገናኝ:: በሌላ በኩል ደግሞ መገናኘት አለመፈለግሽ ከልብሽ ይቅር እንዳላልሽኝ ይናገራል::" አለ አርአያ::

ግራ ገባት::

እረ ባክሽ ተለመኚኝ እረ ተይ አትጨክኚ::

"እሺ በቃ::" አለች፣ ትንሽ ካሰበች በኋላ::

"ዛሬ አሥር ሰዓት ላይ መሥሪያ ቤትሽ መጥቼ ልውሰድሽ?"

"ኖኖ! መሥሪያ ቤት አትምጣ:: ሌላ ቦታ ጠብቀኝ:: "አለች ፍቅረኛዋ እንደነበረ የሚያውቁ ሰዎች እንዲያዩዋትአትፈልግም::

"እቤት ልጠብቅሽ ወይስ ኖሮማረስ ምግብ ቤት ውስጥ?"

"እቤት አልመጣም:: ኖሮማረስ ጠብቀኝ:: አሥር ተኩል ላይ እመጣለሁ::"

"እሺ እጠብቅሻለሁ::" ስልኩን ዘጋው::

የበቀል እርምጃ ለመውሰድ ከያዘው ዕቅድ፣ የመጀመሪያው ደረጃ በመሳካቱ ደስ አለው:: ፊቱ ላይ ፈገግታ ነገሠ:: አልጋው ላይ ጋደም አለና እንዴት አድርጎ ተከታዩን እርምጃ መውሰድ እንደሚችል አሰበ::

አርአያ፣ አለቃው በሻይረሱ መጠቃቱን ከነገሩት ጊዜ አንስቶ ለዚህ የዳረገችው ሴት ማን እንደሆነች በአእምሮው ውስጥ ሲመረምር ቆይቷል:: አብረውት የወጡትን ሴቶች ሁሉ ማስታወስ አለመቻሉ ችግር ሆኖበታል:: የጥቂት ሴቶችን አድራሻ ነው የሚያውቀው::



ከአብዛኛው ጋር ኩርፍ ነው:: ሁሉንም ደውሎ በተወሰነ ሰዓት ቀጥሮ በጥይት ቢቆላቸው፣ በጣም ደስ ባለው ነበር:: ይሁንና፣ ይህ እንደማይሆን ልቡ ያውቀዋል:: ሌላው ቀርቶ አብረውት የወጡትን ሴቶች ሁሉ ሰብስቦ ልቡ ያሰበውን ማድረግ አልቻለም:: የደወለላቸው ሁሉ ሙልጭ አድርገው ሰድበው፣ በጆሮው ላይ ስልኩን ዘግተዋል:: ሲሳይ ብትቆጣም፣ የእርሷ የተሻለ ሆኖ አግኝቶታል:: ለዚህም ነው እርሷን አግባብቶ ቤቱ በመውሰድ፣ መላው የሂዋንን ዘር ወክላ ቅጣት እንድትቀበል የበየነባት::

ኮሞዲኖውን ከፈተና ጂን የያዘ ጠርሙስ አወጣ:: ጥም ለማብርድ ይመስል፣ እንደቀደቀው:: ጉሮሮውንና ደረቱን እየሰነጠቀ ወረደ አልኮሉ:: ሲጋራ ለኩሶ እየሳበ፣ ቤቱ ውስጥ ባለች ቦታ መረማመድ ጀመረ:: ወለሉ፣ የሲጋራ ቁራጮች እንደቄጤማ ተርከፍክፎበታል:: በላይ በላዩ ሲያጨስ ነው የዋለው:: በዚህ ሁኔታ ጥቂት ደቂቃዎች ካሳለፈ በኋላ፣ ሽጉጡን ከጎኑ ሽጉጦ፣ ከሚከሲኮ አደባባይ በታች፣ ከርቸሌ በላይ ከሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ወጣ::

ከቀኑ አሥር ሰዓት ሆኗል:: ከሲሳይ ጋር ሊገናኙ የወሰኑበት ቦታ፣ ከቤቱ አምስት ደቂቃ ነው የሚያስኬደው:: ቀደም ብሎ የወጣው፣ ሲሳይ ካፌቴሪያ ውስጥ ሳትገባ ለማግኘትና ወደ ቤቱ እንድትሄድ ለማድረግ ነው:: እቤት ላለመግባት ከወሰነች ግን፣ ሽጉጡን አውጥቶ እዚያው ለመበቀልና አንድ ጥይት እስኪቀረው ድረስ፣ ባካባቢው ያገኛቸውን ሴቶች በሙሉ ፈጅቶ፣ ለመሞት አቅዷል::

በአካባቢው ሲንጎራደድ ጥቂት ደቂቃዎች አለፉ:: አሥር ሰዓት ከሀያ አምስት ላይ፣ ሲሳይ ብቅ አለች:: ሙሉ ነጭ ቀሚስና ኮት ለብሳለች:: ተረከዘ-ረጅም ጫማ አድርጋለች:: የቆዳ ቦርሳዋን አንግታ ቀይ ፊቷን ክስክስ አድርጋ ተጠጋችው-አርአያን::

ጉንጭ ለጉንጭ ተሳሳሙ:: ቃላት ሳይለዋወጡ ጥቂት ቆዩ::

"በካፌቴሪያ ውስጥ ያሉት መቀመጫዎች በሙሉ ተይዘዋል:: ለምን እቤት አንሄድም?"ሲል አለሳልሶ ጠየቃት::

"እሺ::" አለች ዓይኖቹን ሳታይ::

ከካፌቴሪያው ደጃፍ እንስተው ቤት እስኪገቡ ድረስ፣ ምንም ቃላት ሳይለዋወጡ አሳለፉ::

አርአያ ሲሳይ ቤት ለመግባት ባለማንገራገሯ ቢደሰትም፣ ርምጃውን ለመውሰድ ላለመቸኮል ወሰነ:: እያጫወተ፣ እያሳሳቀ፣ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የወሲብ ፍላጎቱን ካረካ በላ፣ አሰቃይቶ

ሊገላት ፈልጓል። "ቁጭ በይ።"አለ፣ ጠባቧ ሳሎን ውስጥ ያሉትን የሶፋ ወንበሮች እያሳያት።

ተቀመጠች። "ና ቁጭ በላ። " አለች ወደ መኝታ ቤት የሚያስገባውን በር ለመክፈት ሲዘጋጅ።

"መጣሁ። የሚጠጣ ነገር ላምጣ።"

"እሱ ይደርሳል። ና መጀመሪያ ቁጭ በል።" አለችና ከቦርሳዋ ውስጥ፣ በወረቀት የተጠቀለለ ነገር አወጣች።

ከፊት ለፊት ካለው ወንበር ላይ ተቀመጠ።

"ሀሳብህ በጣም ነው ያስደሰተኝ። ሰዎች የሠሩትን መጥፎ ሥራ አምነው፣ ይቅርታ ሲጠይቁ እወዳቸዋለሁ። አከብራቸዋለሁ። ትልቅ አድናቆት አለኝ። አንተም ተፀፅተህ ይቅርታ ስለጠየቅኸኝ ከልብ ተደስቻለሁ።" አለችና ከወንበሯ ብድግ ብላ፣ ጎኑ ሄዳ ተቀመጠች። "ይህቺን መጽሐፍ በማስታወሻ መልክ ሰጥቼሀለሁ።" አለችና ዓይኖቹን አተኩራ አየች።

ሻምበል አርአያ ፍዝዝ ብሎ አያት። ዓይኖቹ እሷን ሳይሆን፣ ራቅ ያለ አካባቢን በተመስጦ የሚያዩ መሰሉ። ወዲያው እንባ አቀረሩ። እንዳቀረሩ አልቀሩም። አዘነቡ። ልቡም አብሮ አለቀሰ። አንገቷ ላይ ጥምጥም አለ። እሷም ሙሉ አካልዋን እላዩ ላይ ጥላ እቅፉ ውስጥ ቀረች።

በዚህ ሁኔታ ጥቂት ደቂቃዎች አለፉ። አርአያ ሲሳይን ከማግኘቱ በፊት እንዳቀደው አልተመራም። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ጨክኖ የነበረው ልቡ ተፍረከረኪል። ሲሳይን የሄዋኖች ሁሉ ወኪል አድርጎ ለቅጣት ያሰበውን ልቡን እንደመርገም አለ።

" ምነው ፊትህ ጠቋቆረ?" አለች ድንገት ሳይታወቃት።

" ኢ.ድስ ይዞኛል።"

"እ?"አለች ከወንበሯ ቀና ብላ። "ምንድን ነው የምታወራው?" ስትል በድንጋጤ ጠየቀች።

" እውነት።"

" እውነት?" አለች ድንጋጤዋ ሳይጠፋ።

" አዎ!" አለ ከረር ባለ ድምጽ።

ሲሳይ በድንጋጤ ድምጽዋን አጠፋች- ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል።

እሱም ሳይናገር በመተከዝ ቆየ።



" ከማን ነው የያዘህ?"

"ሳውቀው አልቻልኩም።"

ሲሳይ ድንጋጤዋ እየጨመረ ሄደ። የልቧ ትርታ ሳታውቀው እየናረ ሄደ። "ያወጣሀቸውን ሴቶች..." አለችና የምትናገረው ጠፋት።

"በሙሉ ጤነኛ ናቸው። ከአንቺ ሌላ ያፈቀርኳቸው ሴቶች በሙሉ ጤነኛ ናቸው።" ሲል ዋሸ። በርሷ በኩል ያለውን የጤንነት ሁኔታ ለማወቅ ፈልጓል።

ሲሳይ ፍጹም ደነገጠች። ልቧ ሳይቆም አይቀርም- በጭንቀት። "እንዴት? ኸረ እኔ ጤነኛ ነኝ። በፍጹም። እኔ ጤነኛ ነኝ።"

ረጅም ዝምታ ተፈጠረ።

ሲሳይ በድንጋጤ ስሜት ውስጥ ሆና ንግሥት ትዝ አለቻት። እሷ እንደሆነች ተረዳች ያስያዘችው።

"እንግዲህ፣ ከአንቺ ሌላ ምንም ሴት የለችም፣ ከእኔ ጋር የመጣች። ከአንቺ ሌላ ማንም ልትሆን አትችልም።" ሲል ረገጥ አድርጎ ተናገረ።

ይህ ሁኔታ በሲሳይ ላይ ፍራቻ አሳደረ። እንዲገናኙ የቀጠራት ይቅርታ ለመጠየቅ ይሁን ለሌላ ሊገባት አልቻለም። ጥርጣሬ አደረባት። "እኔ አይደለሁም፣ አርአያ። እኔ አይደለሁም። ሌላ ሴት ናት። ሌላ ሴት ናት ያስያዘችህ። "

"ነገርኩሽ። ከአንቺ ሌላ ያስያዘችኝ ሴት የለችም። አንቺ ነሽ !" ሲል ጮኸ። ሳይታወቀው ውስጣዊ ስሜቱ በሀዘንና በንዴት ተንተገተገ። እፍጦ አያት። ከመቀመጫው ፍንጥር ብሎ ተነስቶ ቆመ።

ሲሳይ በድንጋጤ ጭብጥ ብላ አየችው። መውጫ ቀዳዳ እንዳጣችና በወጥመድ እንደተያዘች አይጥ፣ ዓይኖቿን ቁልጭ ቁልጭ ከማድረግ ሌላ የተናገረችው አልነበረም።

በዓይኖቹ የሚገላት ይመስል አነጣጠረባት። የግንባሩ ሥሮች ተግተረተሩ። ፊቱ በላብ ሰመጠ።

ሲሳይ ሁኔታው እጅግ አስፈራት። ልትታገሰው የማትችለው ሆነ። ቀጣይ ርምጃ ምን እንደሚሆን ሊገባት አልቻለም። ሮጣ ማምለጥ ፈለገች። ግን እንደማይሆንላት ተረዳች። ነገሩን ማበላሸት ይሆናል ብላ ተወችው። ለረጅም ደቂቃዎች ያረፉባትን የአርአያን ዓይኖች ልትታገሥ አልቻለችም። ማምለጫ መንገድ ፈለገች።

"ንግሥትን አነጋግረሀት ነበር?" አለች ረጋ ባለ አነጋገር።

መልስ አልሰጣትም።

ይህ ሁኔታ ደግሞ ይበልጥ አስፈራት። "በኢድስ ተለክፋለች። ከርሷ ጋር አንድ ሌሊት ማሳለፋችሁን ታስታውሳለህ?" አለች።

"የቷ ናት ትዕግሥት?" አለ ወደ ርሷ እየቀረበ።

"ትግሥት አይደለም ያልኩህ። ንግሥት ነው ያልኩህ። ያቺ የእኔ ጓደኛ።"

አርአያ ልጅቷን አልረሳትም። ከሲሳይ ጋር የተጋጩበት ምክንያት እርሷ በመሆኗ ገጽታዋን ባይረሳውም፣ ስሟን አያስታውሰውም ነበር። ጭንቅላቱን በሁለት እጆቹ ይዞ ሶፋው ላይ ቁጭ አለ።

ሲሳይ ለንግሥት ደግሞ ፈራች። አርአያ ጥቃት እንዳይሰነዝርባት ሰጋች። "በዚህ በሽታ መለከፏን አታውቅም። ብታውቅ ኖሮ፣ ታድንህ ነበር።" አለች።

አርአያ አልተናገረም።

"አባትየው ናቸው ያጠፏት። በሽተኛ መሆኗን እያወቁ ሳይነግሯት በመቆየታቸው ነው ሰዎችን ልትበክል የቻለችው። እርሷ ሳትሆን፣ አባትየው፣ ዶክተር ናትናኤል ዘለቀ፣ ናቸው የዚህ ሁሉ ተጠያቂ።" አለች። ከድንጋጤዋ የተነሳ የምትናገረውን የለየች አትመስልም። ማጅራቱን የሶፋ ወንበሩ ላይ አስደግፎ ጣራ ጣራውን ያይ ጀመር። ምንም ሳይናገር ከራሱ ጋር ሙግት ሲፈጥር ቆየ። በአእምሮው ውስጥ ሁለት የተለያዩ ሀሳቦች መጥተው ተፋጬ። 'ሲሳይን ልቅጣት ወይስ ልተዋት?'

'ለምን? እርሷ ምን አጠፋች? እርሷ ንጹህ ሰው ናት።'

'ማን ያውቃል የነገረችህ ነገር ሁሉ እውነት መሆኑን? ማምለጫ ብላ የፈጠረችው ዘዴ ይሆናል።'

'የለም እውነቷን ነው። ያስያዘችህን ሰው በትክክል ነግራሀለች። እርሷን ትተህ ተገቢውን ሰው ተበቀል።'

'ማን ነው ተገቢው ሰው? ንግሥት ወይስ አባቷ?'

'ሁሉም። ሲሳይ፣ ንግሥትና አባቷ።'

ጥቂት ደቂቃዎች ተቆጠሩ። ሲሳይ የአርአያ ዝምታ ሊያሳብዳት ደርሷል። ሰውነቷ ሁሉ በላብ ርሷል። ሸንቷን በውስጥ ሱሪዋ ላይ የለቀቀችው መሰላት።

"ማነው ያልሽኝ የአባቷን ስም?"



ነገረችው።

"የት ነው የሚሠሩት?"

ነገረችው።

አሁንም ዝምታ ሰፈነ።

ከመቀመጫው ላይ ተነሳ። በፊቱ ላይ መረበሽ ይነበባል። ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል በተመስጦ ቆየና ወደ መኝታ ቤቱ ገባ። ሲሳይ ዘላ ወጣች። የቤቱን በር ከውጭ ዘግታ ሮጠች....

## 51

ሻምበል አርአያ ዛሬ ፀጉሩን እንኳ አላበጠረም። አለባበሱም እስከዚህ አይደለም። ከውስጥ የወታደር ልብስ ለብሶ ከላይ የሲቪል ጃኬት ደርቧል። የሚፈልጋቸው ሰው ይገኙበታል የተባለበትን ቢሮ ከፈተ። አንድ ወፍራም ቀይ ሴትዮ ተቀምጣለች። ተጠጋት። "ይቅርታ የኔ እህት። ዶክተር ናትናኤል ዘለቀ እዚህ ይገኛሉ?"

"አይገኙም።"

"የት ነው ቢሮአቸው?"

"ቢሮአቸው ይሄ ነው።"

"ይመለሳሉ?"

"አይመስለኝም። ሥራ ስለሚበዛባቸው አታገኛቸውም ዛሬ።"

አርአያ ብስጭት ብሎ መሬት መሬት እያየ ቆየ።

ፀሐፊዋ ሁኔታውን አይታ፣"ምነው?በደህና ነው?"ስትል ጠየቀች። ምን እንደሚመልስላት አላወቀም።

"በጣም አስቸኳይ ጉዳይ ነው ?" ስትል ሌላ ጥያቄ አቀረበች።

"አዎ ።"አለ፣ አርአያ ከዚህ በላይ ምንም አስቸኳይ ነገር የለም ብሎ።

"ታዲያ እንዴት አድረጌ ልርዳህ ? እሳቸው ዛሬ፣ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ጋዜጠኞች መግለጫ ለመስጠት ወደ ጤና ጥበቃ አዳራሽ ሄደዋል። ልታገኛቸው የምትችል አይመስለኝም። ቆይ እስኪ፣ ካልሄዱ አንድ የሚገኙበት ቦታ አለ። ልሞክርልህ።" ብላ የስልክ መናገሪያውን አንስታ የውስጥ መስመር ዘረጋች።" ግን ለምን ጉዳይ ነው የምትፈልጋቸው?" ስትል ጠየቀችው የስልኩን መናገሪያ ጆሮዋ ላይ ለጥፋ። መልስ ከማግኘቷ በፊት ስልኩ አናገራት። "ሀሎ!

እንደምን አደርሽ ? .... አዎ ነኝ:.... ዶክተር ናትናኤል እናንተ ዘንድ አሉ? ..... ወዴት ነው የሄዱት?... እሺ::" ስልኩን ዘጋችውና ቀና ብላ እየችው::" አሁን ወጡ ተባለ::" አለች።

"ወዴት ነው የሄዱት? እደርስባቸዋለሁ?"

" አይመስለኝም፣ በመኪና ነው የሄዱት::"

"መኪና ይዣለሁ::" አለና ወዲያው ሀሳቡን ለወጠ። ዶክተር ናትናኤልን አያውቃቸውም። መከተል አይችልም::" የት አገኛቸዋለሁ?"

"ወደ ጤና ጥበቃ አዳራሽ ነው የሄዱት:: ሦስት ሰዓት ላይ ጉራስ ኮንፈረስ አለባቸው:: አሁን ለሦስት አሥር ጉዳይ ነው::" አለች ሰዓቷን እያየች። " አዳራሹ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት ከደረስክባቸው ሞክር::"

" አዳራሹ የት ነው የሚገኘው?" ሲል ጠየቀ።

ነገረችው::

እየተጣደፈ ወጣ::

ናትናኤል፣ ለልጃቸው ምስጢሯን ሳይነግሯት በመቅረታቸው እርሱን ወደ ሞት አፋፍ አቅርበዋል። በዚህ ቁጭት እርሳቸውን አስቀድሞ በሞት ሊቀጣቸው ተዘጋጅቷል። ይህንን ውሳኔውን በአፋጣኝ ተግባራዊ ለማድረግ ችኩሏል። የገቡበት ገብቶ ሊያጠፋቸው ፈልጓል።

መኪናውን አቆመና አንድ ትልቅ ግቢ ውስጥ ገባ። በግቢው ውስጥ በርከት ያሉ፣ ሙሉ ልብስ ከነክራቫቱ የለበሱ፣ ሰዎች ቆመዋል። የሚጠባበቁት ነገር ያለ ይመስላል። አርአያ ወደ አንድ ሰውዬ ጠጋ አለና፣ "ዶክተር ናትናኤል ዘለቀን የት አገኛቸዋለሁ?" ሲል ጠየቀ።

"አዳራሽ ውስጥ ናቸው::" ብሎ አዳራሹን በእጁ ጠቆመው።

"ላነጋግራቸው አልችልም?" አለ አርአያ።

"አይመስለኝም፣ ከስብሰባው በኋላ ካልሆነ። ይህ ሁሉ ሰው የሚጠብቀው እርሳቸውን ነው። እሳቸው የሚሰጡትን መግለጫ ነው፣ እነዚህ ሁሉ ጋዜጠኞችና ሌሎች ባለሞያዎች፣ የሚጠብቁት። አሁን ጊዜ ያላቸው አይመስለኝም::"

አርአያ ተናደደ። ከስብሰባ በኋላ እንደሚያገኛቸው ቢያውቅም፣ የአንድ ደቂቃ የህይወት ጊዜ እንኳ ሊሰጣቸው አልፈለገም።

ወዲያው፣ በአካባቢው ያሉ ሰዎች፣ ወደ አዳራሹ እንዲገቡ፣ የዝግጅቱ አስተባባሪ አሳወቀ። ሰዎቹ ሁሉ ገቡ። አርአያ ብቻውን ቆመ።



ጥቂት አሰበ። 'ለምን እዚሁ አልደፋቸውም? እንዳውም ጥሩ አጋጣሚ ይሆናል። ለበደሉኝ የምሰጣቸውን ቅጣት ለሌላው ሰው የሚነግሩ ጋዜጠኞች ባሉበት ቦታ መሆኑ ጥሩ ነው። የዶክተሩን ኃጢአት ሁሉም ማወቅ አለበት። ዶክተሩን ካጋደምኩ በኋላ፣ ለተሰበሰበው ሁሉ ጥፋታቸውን ነግሬ፣ ራሴን እገላለሁ' አለ በልቡ።

አዳራሹ ውስጥ ገባ። መጠነኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች አዳራሹን ይዘዋል። የሬዲዮና የቴሌቪዥን ጋዜጠኞች መሣሪያዎቻቸውን፣ ሙሉ ቡላማ ሱፍ ልብስና ቡላማ ክራቫት አድርገው፣ መድረኩ ላይ ጉብ ያሉት ዶክተር ላይ አነጣጥረዋል። አዳራሹ ውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ ጉጉት ያደረ ይመስላል። የነጭና የጥቁር ዘር የተቀላቀለበት የጋዜጠኞች ስብስብም ለአንባቢው፣ ለተመልካቹና ለአድማጩ ተሽቀዳድሞ የሚያቀርበውን ዜና በጉጉት እየጠበቀ ነው።

አርአያ፣ ገንጠል ብሎ አንድ ሰውዬ ወደ ተቀመጠበት አጠገብ ተጠጋና ቆሞ አለ። "ዶክተር ናትናኤል የትኛው ናቸው?" ሲል ጠየቀ አርአያ።

ሰውዬው ቀና ብሎ እየውና፣ "እኛ መድረኩ ላይ ያሉት ናቸዋ::" አለ። እስካሁን ሳያውቃቸው በመቅረቱ የተገረመ ይመስላል።

የአርአያ ቀኝ እጅ ወገቡ ላይ የታሰረውን ሽጉጥ ደገፍ አደረገ። ርምጃውን ለመውሰድ ተጣድፏል። በህይወት ተደስቶ የመኖር እትዱን ያጨናገፉበትን ሀኪም፣ ብዙ ሰዎች በተሰበሰቡበት መድረክ ላይ፣ እንደ ግንድ ሊያጋድማቸው ችኩሏል።

ወዲያው፣ ጥቁር ሙሉ ሱፍ የለበሰና ቀይ ክራቫት ያደረገ፣ ረጅም ቀይ ሰውዬ፣የአዳራሹን የድምጽ ማጉሊያ መሣሪያ ይዞ፣ ከዶክተር ናትናኤል አጠገብ ቆመ። ንግግሩን በእንግሊዝኛ ቋንቋ ጀመረ።

"ክቡራትና ክቡራን! ኢትዮጵያዊው ሳይንቲስት ዶክተር ናትናኤል ዘለቀ በዓለማችን እስከፊ ጥፋት በማድረስ ላይ ስላለው የኤድስ በሽታ ሲያደርጉት የነበረውን ምርምርና ውጤት ምን እንደደረሰ ገለፃ ሊያደርጉላችሁ ከፊታችሁ ይገኛሉ። ስለዚህ በሽታ መከላከያና ማጥፊያ እስከዛሬ በዓለማችን ያሉ ሳይንቲስቶች ብዙ ቢሞክሩም፣ የዶክተር ናትናኤል የአሁኑ የምርምር ውጤት እስካሁን ከተመዘገበው እጅግ ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል። ይህንን ግኝታቸውን እንዲረዳላቸው የተቋቋመው ኮሚቴ የእስካሁኑ ውጤታቸውን መርምሮ ጥሩ ተስፋ እንዳለው በመረዳት፣ ይህንኑ ጉዳይ በዓለማችን ላሉ

ህብረተሰቦች ለማሳወቅ፣ ይህንን የጋዜጣዊ መግለጫ ፕሮግራም አዘጋጅተናል። ይህም መግለጫቸው በዓለማችን ያለውን ሥጋት ጋብ እንደሚያደርገውና የኤድስ ቫይረስ ተጠቂ ለሆኑ ሰዎች ደግሞ፣ የመኖር ተስፋ እንደሚሰጣቸው እርግጠኞች ነን። ለእኝህ ኢትዮጵያዊ ሳይንቲስት፣ ይህ የመጀመሪያ ሥራቸው አይደለም። ሌሎች በርካታ ምርምሮች አካሂደው በሥራ ላይ አውለዋል። በምርምር ክፍላቸው ውስጥ በወረቀት ላይ ብቻ ሰፍረው ያሉም አሉ። አሁን ደግሞ የመላው አለምን ህዝብ ስጋት የሚያጠፋ ግኝት ይዘው ብቅ ብለዋል። ስለግኝታቸው የሚሰጡንን መግለጫ ለመስማትና ለሌሎች ወገኖቻችን ለማዳረስ ባህር ተሻግራችሁ፣ አገር አቋርጣችሁና ከሀገር ውስጥ የመጣችሁት ጋዜጠኞችና ሌሎች ባለሙያዎችን ሁሉ፣ በዶክተር ናትናኤል ዘለቀ ስም አመሰግናለሁ። አሁን መድረኩን ለጋዜጠኞች ጥያቄዎችና ለርሳቸው መልሶች እለቃለሁ። አመሰግናለሁ።"

አርአያ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተደረገውን ንግግር በሙሉ ንቃት ሰምቶታል። ስሜቱ ላይ ከፍተኛ ለውጥ አመጣ። እርምጃ ለመውሰድ አቆብቁቦ የነበረው ስሜቱን ረገብ አደረገ። ይሁንና፣ ጆሮዎቹን ሊያምን አልቻለም። ተከታዩን ማብራሪያ ለመስማት ጉጉት አደረበት። በግራ ጎኑ የያዘውን ሽጉጥ ጨብጦ የነበረው እጁን አወጣና አፉን ያዙ-በመገረም።

አንድ ረዘም ያለች ፈረንጅ ተነስታ የድምጽ ማጉያውን ወደአፏ አስጠግታ፣ "ዶክተር ዘለቀ፣ የመጀመሪያ ጠያቂ ልሁንና፣ የምርምሮ ትኩረት ያረፈው ለኤድስ ቫይረስ ማጥፊያ ወይስ ይህ በሽታ ከአንዱ ሰው ወደሌላ እንዳይዛመት የሚከላከል መድሀኒት በመፍጠር ላይ ነው?" ስትል ጠየቀችና ወደ ወንበሯ ተመለሰች።

ዶክተር ናትናኤል ጉሮሮአቸውን ጠራረጉ። "የእኔ ምርምር ያተኮረው፣ ቫይረሱ ከአንዱ ወደ ሌላ እንዳይዛመት መከላከል የሚችል መድሀኒት በመፍጠር አይደለም። ምርምሬ ያተኮረው፣ ቫይረሱን እስከ እነጭራሹ የሚያጠፋ መድሀኒት በማግኘት ላይ ነው። "አሉና ሌላ ጥያቄ በመጠበቅ ዓይነት ታዳሚውን ቃኙ።

አንድ ሌላ የውጭ ሀገር ጋዜጠኛ ተነሳ። ነጭ ቆዳ አለው። አጭርና ደማም ነው። "ዶክተር ,ምርምሮ ምን ያህል ተሳክቶሎታል? እስካሁን ድረስ መድሀኒቱን ለማግኘት በሌላው የዓለም ክፍል ባሉ ሳይንቲስቶች ከተደረጉት ምርምሮች የእርሶ በምን ይለያል?" አለና ተቀመጠ።



"መጀመሪያ ለሁለተኛው ጥያቄ መልስ ልስጥ። እስከዛሬ ድረስ በጥቅም ላይ የዋሉም ሆነ በምርመር ላይ ያሉ መድሀኒቶች ቫይረሱን ሙሉ ለሙሉ ማስወገድ የሚችሉ አልሆኑም። የሚያደርጉት ነገር ቢኖር ቫይረሱ እንዳይባዛ ማገድ ወይም የማባዣውን ፍጥነት ማዘገም ነው። ለምሳሌ፣ አዚዶታይሞዳይን ፣ ብቸኛ ፍቃድ ያገኘና በጥቅም ላይ የዋለውን ፀረ ሬትሮቫይራል ብናይ፣ የቫይረሱን የመራባት ሂደት ያደናቅፋል። ግን አኒሚያ፣ በተለምዶ አነጋገር የደም ማነስ፣ በሽታ ያስከትላል። በብዙ ሲጠቀሙት ደግሞ ወደ ቫይራል ሪስታንስ ይመራል። ይሁንና የሚያመጣው ያልተፈለገ ውጤት፣ ሳይድ ኤፌክት ገና አልታወቀም። ዲዲሲ እና ዲዲ አይ በሙከራ ላይ ያሉ የኤድስ መድሀኒቶች ናቸው። በኤድስ ህሙማን ላይ የሚያስከትሉት ያልተፈለጉ ውጤቶች ምን እንደሆኑ ገና አልተጠናም። ዲዲ አይ ከአዚዶታይሞዳይን የበለጠ ውጤት ያለውና የሚያስከትለው ጉዳት መጠነኛ የሆነ ይመስላል። እነዚህ ሁለቱ የሚረዱት ለቫይረሱ መራባት ምክንያት የሆነውን ኢንዛይም እንዳይኖር በማገድ ነው። ይሁንና፣ አንዳንድ መረጃዎች እንደሚያሳዩን ዲዲ አይ በጣፊያ ላይና በአንዳንድ ነርቮቹ ላይ መለብለብ ያመጣል። እንደዚሁም ዲዲሲ በአንዳንድ ነርቮች ለይ የመለብለብ ወይም የመቃጠል ጉዳት ያመጣል። ሌሎች ገና በምርምር ደረጃ ላይ ያሉ መድሀኒቶች አሉ። ይሁንና፣ እስካሁን የተነጋገርንባቸውና ሌሎች/ኮምፓውንድ ኪው፣ ጃ ኤል ኪው ቱ ሀንድረድ ቴዌንትይ ስሪ፣ ሪቦዘምስ፣ አልፋና የመሳሰሉት የኤድስ ኤች አይ ቪ ቫይረስ በሽታ መድሀኒቶች ሊሆኑ አልቻሉም።

"ወደ እኔ ምርምር የተመለስን እንደሆነ፣ የኤድስ ቫይረስ በሰውነት ውስጥ እንዳይበራከቱ የሚያግድ ሳይሆን፣ ቫይረሱ ከአንድ ዓይነት ወደ ሌሎች ባህሪዎች ወይም ዓይነቶች ራሱን ከለወጠ በኋላ በመጨረሻ የሚታይበት ደረጃ ሲደርስ የሚያጠፋው ነው። በሌላ አነጋገር የእስካሁኑ የምርምር ውጤቶች ቫይረሱን ሙሉ ለሙሉ የሚያጠፉ ሳይሆኑ፣ ዕድገቱን የሚያዘግሙና የሚያደክሙ ናቸው። የእኔ ደግሞ ቫይረሱ አንድ የተወሰነ የዕድገት ደረጃ ላይ ሲደርስ፣ የሚያጠፋ ነው።

"ወደ ሁለተኛው ጥያቄ እንመለስ። ለአንድ የምርምር ሰው የሚያጠናበት ጉዳይ የሚያመጣውን ችግር መረዳት፣ ማስተዋልና መገንዘብ፣ የችግሩን መነሻና መፍትሄ መላ ምት ማቅረብና መተንበይ፣ መሞከር፣ ውጤቱን ማጤንና መደምደሚያ ላይ መድረስ የሚያጋጥሙት ሂደቶች ናቸው። እኔ ያለሁት ምርምሬ ፍሬ የሚያፈራበት ደረጃ ላይ ነው። ያገኘሁት መድሀኒት የኤድስ

ህመምተኛን በትክክል ይፈውሳል። ይሁንና መድሀኒቱ የሚያመጣውን ያልተፈለገ ውጤት ገና አላወቅሁም። ይህንን ጋዜጣዊ መግለጫ ከመስጠቴ በፊት፣ ይህንን ውጤት አያለሁ ብዬ ገምቼ ነበር።ግን አልቻልኩም። ይሁንና በታካሚዎች ላይ መድሀኒቴ ምንም ዓይነት ሌላ ጉዳት እንደማያመጣ የሚያሳውቀውን መግለጫዬን በቅርቡ እንደማቀርብ እርግጠኛ ነኝ።"

"ዶክተር፣ "አለ አንድ ኢትዮጵያዊ ጋዜጠኛ። "የእርሶ መድሀኒት ሙሉ ለሙሉ የኤድስ/ ኤች አይ ቪ ቫይረስን እንደሚያጠፋ ገልፀዋል። አሁን ባሉበት የምርምር ደረጃ መድሀኒቱ ህሙማንን ካዳን በኋላ፣ የሚያመጣውን ጉዳት /ሳይድ ኢፌክት/ አላወቁም። መድሀኒቱ የሚያመጣው ጉዳት ቢኖር፣ ምን ሊሆን ይችላል ብለው ይገምታሉ ?"

"መጠነኛ የጉበት በሽታ ሊያመጣ ይችላል የሚል ግምት አለኝ። ሄፒታይተስ ቫይረስ ሊፈጠር ይችላል። ብቻ ርግጠኛ መሆን አይቻልም። አሁን የጠቀስኳቸው ጉዳቶች ላይፈጠሩም ይችላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ መድሀኒቱን እንደወሰደ ታማሚው ሊሞት ይችል ይሆናል።"

"ለዚህ በሽታ ማጥፊያ መድሀኒት ለመፈልሰፍ ምን አነሳሳዎ? ለመድሀኒትነት ያገለግላል ብለው ለያዙት ቁስ ፍንጭ የሆኖት ምንድን ነው?" አለ አረብ የሚመስል ጋዜጠኛ።

"ይህንን መድሀኒት ለመፍጠር የተነሳሁበት ምክንያት ግልጽ ይመስለኛል። አሁን በአለንበት ወቅት የሰው ዘርን በሚያስፈራ ፍጥነት በማጥቃት ላይ ላለ በሽታ ማጥፊያ ማንኛውም የህክምና ሰው ፈጣን ምላሽ መስጠት እንዳለበት እውቅ ነው። እኔንም ያነሳሳኝ ይኸው ጉዳይ ነው።" ብለው የተናገሩት ዕውነት መሆኑንና አለመሆኑን ለማወቅ ዝም አሉ። አነስተኛ ፍርሀትና ጥርጣሬ አደረባቸው። ልጃቸውን ለማዳን ሲሉ፣ ይህንን ምርምር መጀመራቸውን በሰው የታወቀባቸው ነው የመሰላቸው። ተከታዩን ጥያቄ መመለስ ጀመሩ። ከባህል ሀኪሙ፣ ከአቶ ምስጋናው ጋር ያስተዋወቃቸውን አጋጣሚ አነሱ። የባህል ሀኪሙ በግሩም ላይ የታዩትን ምልክቶች ያጠፉበትን መድሀኒት እንዲፈተሹላቸው ከመስጠታቸው በፊት ባደረጉት መላ ምት፣ ካገኟቸው ዕፅዋት ውስጥ አንዱ ለመድሀኒትነት እንደሚያገለግል ፍንጭ ማግኘታቸውንና፣ አሁን ያለበት ደረጃ እንዳደረሳቸው አስረዱ።

አንድ ኢትዮጵያዊት ጋዜጠኛ ተነሳች። "ዶክተር ናትናኤል፣ የኤድስ ቫይረስ መቼና የት ታወቀ?የሚሉት ጥያቄዎች ብዙዎቹን



እያጨቃጨቀ እንደመጣ ታወቋል። አንዳንዶቹ የሚሰጡት ገለጻ እንዳንድ አህጉራትን ሲያስኮርፍ ቆይቷል። ለእነዚህ ጥያቄዎች የእርሶ መልሶች ምን ምን ናቸው?"

"የኤድስ ቫይረስ መጀመሪያ የተገኘው - እኔ ባገኘሁት መረጃ መሠረት- በአሜሪካ በሎስአንጀለስ ክፍለ ሀገር፣ በአንድ ግብረ ሰዶም ፈጻሚ ወንድ ላይ ነው። ጊዜው እ.አ.አ 1981 ዓ.ም ነው።" ሲሉ ለተነሱት ጥያቄዎች አጭጭር መልሶች ሰጡ። በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ ብዙ ጊዜ መፍጀት የፈለጉ አይመስሉም።

ሌላ ጋዜጠኛ ተነሳ። ጥቁር ነው። ከአነጋገሩ ዜማ አፍሪካዊ መሆኑ ይታወቃል። "እንደሚታወቀው፣ የሰው ዘር በዚህች ምድር ላይ መኖር ከጀመረ በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ ዓመታት አልፈዋል። ይሁንና፣ እስካለፉት የቅርብ ዓመታት ድረስ፣ የዚህ በሽታ ምንነት አይታወቅም ነበር። ማለት፣ የኤች አይ ቪ ቫይረስ መኖር አይታወቅም ወይም አልነበረም። ታዲያ ይህ ሁኔታ አንዳንድ ሰዎች፣ የዚህ ቫይረስ መነሻ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት ነው እንዲሉ እያደረጋቸው ነው። በሌላ አነጋገር፣ የሰው ልጅ በህይወት ላይ የገጠመውን ችግር ለማቃለል ሲል በፈጠረው ዘዴ ምክንያት ነው፣ ይህ ቫይረስ ሊፈጠር የቻለው ይባላል። በዚህ ላይ ምን አስተያየት አሎት?"

ዶክተር ናትናኤል፣ ሰውዬው መናገር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ፣ ሊጠይቃቸው ያሰበው ምን እንደሆነ አውቀዋል። ጥያቄው ቀጥተኛ ባይሆንም፣ ናትናኤል ምን ለማለት እንደፈለገ ተረድተዋል። "ስለ ኤድስ ኤች አይ ቪ ቫይረስ መነሻ ብዙ መላ ምቶች ተሰጥተዋል። የትኛው ወይም ያኛው ትክክል ስለመሆኑ የምሰጠው መልስ የለኝም"። አሉና ዘጉት።

አንድ የቻይና ጋዜጠኛ ተነሳች። "በአሁኑ ወቅት ለኤድስ/ ኤች አይ ቪ ቫይረስ ሰለባዎች ምን ይመክራሉ?"

"ለመኖር ጉጉትና ተስፋ እንዲኖራቸው ትዕግሥትን መሣሪያ ማድረግ እንዳለባቸው እመክራለሁ። በዚህ በሽታ በመለከፋቸው፣ ከሌላው የህብረተሰብ አባላት ዝቅ ብለው የሚታዩ አለመሆናቸውን ማወቅ አለባቸው። የኤድስ ቫይረስ በሰው ልጅ ታሪክ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የደረሰ መከራ አይደለም። ከእኛ ቀደም ባሉት ትውልዶች ውስጥ የነበሩ ሰዎች በጊዜው መድሀኒት ያልተገኘላቸው አሰቃቂ በሽታዎች ገጥሞአቸው ነበር። ይሁንና፣ ሰው በመታገሉና ጥረት በመደረጉ መድሀኒቶቹን ሊያገኝ ችሏል። የዘመናችን በሽታም ከዚህ የሚለይ

አይደለም። እንዳውም በአሁኑ ወቅት፣ ያለፉት ዘመናት ያላፈሯቸው ሳይንቲስቶችና የምርምር መሣሪያዎች አሉ። ስለዚህ፣ በቅርቡ መድሀኒቱ መፈብረኩ አይቀርም። ትዕግስት ያስፈልጋል። ራስንና ሌላውን በመጥላት ወደጥፋት የሚያደርጉትን ጉዞ መግታት አለባቸው። ከመቼውም የበለጠ ለሰው ልጅ ርህራሄና ቅንነት ማሳየት አለባቸው። ከአካላዊ ደስታቸው ይልቅ ለህሊና ደስታቸው መጣር አለባቸው። ይህ በሽታ እስከዛሬ ከታዩት በሽታዎች ለየት የሚልበት ሁለት ባህሪያት አሉት። አንደኛው፣ በቫይረሱ የተለከፉ ሰዎችን ቶሎ አለመግደሉና የዓመታት ጊዜ መስጠቱ ነው። ይህ ሁኔታ ህሙማንን የሚያጽናና መሆን አለበት። በሽታው እነሱን ለሞት ከመዳረጉ በፊት፣ መድሀኒቱ ሊገኝ ስለሚችል ተስፋ እንዲኖራቸው ያደርጋል። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ቫይረሱ በደም ውስጥ መኖሩ ከመታወቁ በፊት፣ አያሌ ወንድሞችንና እህቶችን ሊበክል ስለሚችል፣ ጉዳቱ ፈጣንም ከባድም ነው። ህሙማን ይህን በመረዳት የሌሎች ሰዎችን ጤንነት በመጠበቅ ለህሊናቸው ማደር አለባቸው። ሌላው ትልቁ መሣሪያ ነው ብዬ የምገምተው፣ ፀሎት ነው። ህሙማን ሳያሰልሱ በፀሎት ከአምላካቸው ጋር መገናኘት አለባቸው።"

ዶክተር ለዚህ ጥያቄ የሰጡት መልስ ለአርአያ ጥሩ አስታማሚ ሆኖአል። ጨልሞ ለነበረው የመኖር ተስፋው፣ የብርሀን ብልጭታ ፈንጥቆለታል። ልቡ በደስታ ተሞልቷል ። አዳራሹ ውስጥ ይዞት የገባውን የበቀል ስሜት አሽቀንጥሮ ጣለው።' እንደገና መኖር!' አለ በልቡ።

አንድ ኢትዮጵያዊ ጋዜጠኛ ተነሳ። "ዶክተር፣ ለዚህ በሽታ መገኘት የባህል ሀኪሞች በተለይ፣ የሀገራችን፣ ምን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለው ይገምታሉ?"

"የዚህን በሽታ መድሀኒት በማግኘት በኩል የባህል ህክምና ከፍተኛ ሚና ሊጫወት ይችላል። እስካሁን በዓለማችን ላሉ ብዙ በሽታዎች መድሀኒት መገኘት ምክንያት የሆነው፣ የባህል ህክምና ነው። ስለዚህ፣ ከባህል ሀኪሞች ብዙ ይጠበቃል። ግን ጥበባቸውን በሳይንሳዊ ዘዴ ምርምር እንዲደረግበት ፈቃደኛ ሆነው መገኘት አለባቸው። እኔ ካገኘሁት መድሀኒት የተሻለና ውጤታማ የሆነ መፈወሻ ሊያፈልቁ ይችላሉ።

"ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደሞከርኩት፣ ለዚህ ምርምሬ መነሻ ፍንጭ የሰጠኝ የሀገራችን የባህል ህክምና ነው። በዚህ ረገድ አቶ ምስጋናው የሚባሉ የባህል ሀኪም የሚደነቅ ተአምር ከመሥራታቸው



ጎን ለዚህ ምርምሬ ምክንያት ስለሆኑኝ ላመስግናቸው እወዳለሁ። በዚህ አጋጣሚ የአቶ ምስጋናው የባህል መድሀኒት ቫይረሱን ማጥፋት ባይችልም፣ የአንድ የኤድስ ህሙምን ዕድሜ መቀጠሉን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ። ይህ ቀላል አይደለም። ይህንን በመረዳት፣ የባህል ሀኪሙን የባለቤትነት መብት በመጠበቅ ውጤት ያሳየውን መድሀኒታቸውን የሚመለከተው ክፍል ምርመር እያደረገበት ነው። አሁን በአለንበት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ግስጋሴ ከዘመናዊ ህክምና ምንም ጠብ ሳይል፣ ከባህል ህክምና ይህ መገኘቱ፣ እንደ አቶ ምስጋናው ያሉ ባለሙያዎች ምን ያህል ጠቃሚ መሆናቸውን የሚናገር ይመስለኛል።" አሉ።

አንድ ሴት ጋዜጠኛ ተነሳች። ነጭ ናት። "ዶክተር ዘለቀ፣ ይህን መርምር ለማካሄድ ከፍተኛ የገንዘብና የማቴሪያል አቅም የሚጠይቅ ይመስለኛል። ይህንን ችግር እንዴት ሊወጡት ቻሉ?

"እንደተባለው ምርምሩ ከፍተኛ ገንዘብ ጠይቋል። በተለይ ደግሞ በግሌ ብቻ ያደረግሁት ምርምር ስለሆነ የገንዘብ አቅም አልነበረኝም። ይሁንና አለምፈቀፍ ግብረሰናይ ድርጅቶችና በሀገር ውስጥ አንዳንድ ግለሰቦች ስለረዱኝ ምርምሩን አሁን ያለበት ደረጃ አድርሻለሁ። ውጤቱንም ካዩ በኋላ በተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ሊያደርጉልኝ የሚፈልጉ ተቋማት አሉ።" ሲሉ ገለጡ ዶክተር።

ጋዜጣዊ መግለጫው እንዳበቃ የፕሮግራሙ አስተናባሪ እንግዶቹ ሻይ እንዲጋበዙ ጠየቀ። እንግዶቹ ሁሉ ወደ ሻይ ሲወጡ፣ አርአያ ብቻ ቀረ። እስካሁን ድረስ ያለውን ነገር መስማቱ በቂ መስሎ ታየው። ከእንግዲህ መቆየት አልፈለገም። ይሁንና የዶክተር ናትናኤልንና የባህል ሀኪሙን፣ የአቶ ምስጋናውን፣ አድራሻ ፈልጓል። ይህንኑ ሊነግሩት የሚችሉት ዶክተር ናትናኤል ብቻ መሆናቸውን ተረዳ። በዚህ አጋጣሚ ሊያናግራቸው ፈልጎ፣ ወደ እርሳቸው ተጠጋ።

## 52

ሲሳይ ከሻምበል አርአያ ቤት አምልጣ ከወጣችበት ደቂቃ ጀምሮ የተሰማት እፎይታ ለረጅም ጊዜ አልቆየም። ራሷን ለማዳን ስትል የፈጠረችው ዘዴ ሳታውቀው የሌሎች ሰዎችን ህይወት አደጋ ላይ ጥሏል - የዶክተር ናትናኤልንና የንግሥትን። እነሱን ለማዳን ማድረግ የሚገባት ምን እንደሆነ ስታስብ ነው የከረመችው።

የተፈጠረውን ሁኔታ ለንግሥት ግልጽ አድርጋ ልትነግራት ወስና በኋላ ላይ ትታዋለች። አንድ ጊዜ የሰደበቻት የሚረሳ

አልሆነባትም። እርስዋን ከማናገር ይልቅ ለአባትየው መንገሩ ጥሩ ዘዴ ሆኖ አግኝታው ነው ዛሬ፣ የሚሰሩበት ሆስፒታል ድረስ የሄደችው። ይሁንና ጠዋት ልታገኛቸው አልቻለችም። ስብሰባ እንዳለባቸው ነበር የተነገራት። ከሥራዋ ቀርታ ዶክተሩን ባለማግኘቷ፣ ብስጭት ብትልም፣ ከሰዓት በኋላ ከቢሮአቸው መኖራቸውን ስታውቅ ደስ አላት።

"እንደምን ዋሉ ዶክተር?" አለች ሲሳይ፣ ልትጨብጣቸው እየተጠጋች።

ቀና ብለው በመነጽራቸው ውስጥ አዩዋት። "አ! ሲሳይ! እንዴ፣ አለሽ እንዴ አንቺ?" ሲሉ በመጠየቅ ጨበጧት።

"አለሁ። ደህና ኖት?" አለች፣ ከቢታቸው በመቅረቷ አፍራ።

"ደህና ነኝ። ደህና ነሽ ?"

"ደህና ነኝ።"

"ምነው ጠፋሽ ? ካየሁሽ እኮ ቆየሁ።"

"አለሁ።" አለች አቀርቅራ።

"መቼ ዕለት ነው? ንግሥቴን ስለ አንቺ ጠይቂያት፣ ደህና እንደሆንሽ ነገረችኝ። ግን በደህና ነው የጠፋሽው ?"ሲሉ ጠየቁ። በንግሥት ላይ የደረሰውን አደጋ ሰምታ የራቀቻት አድርገው ነው ያሰቡት።

"አዎ ደህና ነኝ።"

"ታዲያ ምነው አልጠየቅሽንም? ንግሥቴ እንደ አንቺ ያለ ጓደኛ በምትፈልግበት ጊዜ ከቤት መጥፋትሽ ተገቢ ነው?" ሲሉ ለስለስ ባለ ሁኔታ ጠየቋት።

ሲሳይ አልተናገረችም።

"ከንግሥት ጋር ተጣልታችኋል እንዴ?"

"አይ ደህና ነን። አልተጣላንም።" ስትል ዋሸች። የመጣችበትን ጉዳይ ቶሎ ተናግራ መውጣት ፈለገች። ይሁንና ልትገልጽላቸው ያሰበችውን ነገር ማንሳት ቀላል ሆኖ አልታያትም። ከምን ጀምራ በምን እንደምትቋጭ መለየት አቃታት።

"ሻይ ወይስ ቡና? ምን ይምጣልሽ?" አሉ የውስጥ መስመር ማገናኛ ስልኩን አንስተው።

"ምንም አልፈልግም። እቸኩላለሁ። ቶሎ መሄድ አለብኝ።" አለች ሲሳይ።



ዶክተር አላግደረደሯትም። ጊዜ የላቸውም። "ታዲያ ዛሬ እንዴት ብቅ አልሽ?" አሉ ጥቂት ዝምታ ከተፈጠረ በኋላ።

"አንድ ነገር ተፈጥሮ እርሱን ላሳውቆት ነው የመጣሁት።" ብላ ዝም አለች።

"ምን?" አሉ ትንሽ ኮስተር ብለው ። ልጃቸውን የሚመለከት ጉዳይ መሆኑን አላጡትም።

"ሻምበል አርአያ የሚባል መኮንን አለ።" አለችና እንዴት እንደምትቀጥል ማሰብ ያዘች።

ይሄ ስም በዶክተር አእምሮ ውስጥ አቃጨለ። ከአሁን በፊት እንደሰሙት ርግጠኛ ናቸው። ግን የትና መቼ እንደሆነ ለማረጋገጥ የማሰቢያ ጊዜ ሳያገኙ ሲሳይ ንግግሯን ቀጠለች።

"ኤድስ የያዘው ሰው ነው። 'ያስያዘችኝ ንግሥት ናትና ገድያት እሞታለሁ። 'እያለ ሲፎክር ሰምቼዋለሁ።"

ዶክተር ክፉኛ ደነገጡ። አንገታቸውን ወደ ፊት ሰገግ አድርገው፣ የንባብ መነጽራቸውን አውልቀው አዩዋት፣ ሲሳይን። "ምንድን ነው የምታወሪው ሲሳይ?"

ሲሳይም ሳትደነግጥ አልቀረችም። ስለንግሥት መታመም ርግጠኛ ሆና የምታውቀው ነገር የለም። "እኔ እንጃ ብቻ፣ ንግሥት የቫይረሱ ተጠቂ ሆና ሰውዬውን ማስያዝዋን አላውቅም። ሊገላት እንደሚፈልግ ግን ርግጠኛ ነኝ። ስለዚህ ጉዳይ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለማሳወቅ ነው የመጣሁት።"

ዶክተሩ በፀጥታ ሲያዳምጡ ከቆዩ በኋላ በሀሳብ ሰጥመው ሲሳይን አዩዋት።"ምን ይመስላል ሰውየው?"

ሲሳይ የሻምበል አርአያን አካላዊ ሁኔታ ገለፀችላቸው።

"የት ነው የሚሠራው?"

ነገረቻቸው።

በወረቀት ላይ አሰፈሩት።

"ለእርሶም ህይወት ጥንቃቄ ቢያደርጉ መልካም ነው። እርሶንም ለመበቀል ይፈልጋል።" አለች እንደዋዛ።

ናትናኤል ከፍ ያለ ድንጋጤ መላ ሰውነታቸው ውስጥ ሲሰራጭ ተሰማቸው። "እኔ ደግሞ ምን አጠፋሁ?"

"እኔ ምን አውቃለሁ?" አለች። ወዲያው በመቀጠል፣ "በበሽታው መለከፉን ተረድታ ሰዎችን እንዳትበክል በቅድሚያ እንድትጠነቀቅ ስላላደረጉ ነው መሰለኝ።" አለች።

ዶክተር ናትናኤል ግንባራቸውን ጠረጴዛውን ከተሞረከዘው እጃቸው ላይ ወርወር ከማድረግ ሌላ፣ ምንም አልተነፈሱም። ለሲሳይ የሚነግሯት መከላከያ አልነበራቸውም። ጥፋታቸውን ያውቁታል።

ሲሳይ ከጥቂት ቆይታ በኋላ የጓደኛዋን አባት ተሰናብታ ወጣች። የዶክተር ድንጋጤ አሳስቧታል።ያ ህመምተኛ ልባቸው ሥራውን ያቆማል ብላ ሰጋች። ምንም አማራጭ አልነበራትም። 'ግን ለምን ለንግሥት አልነገርኳትም? ምን አስፈራኝ? ከቶ ለሠራብህ ደግ ሥራ ተብሏል። ብቻ ያው ነው። አባቷ ሰሙ ማለት እርሷ ሰማች ማለት ነው።' ስትል ደመደመች። ይሁንና በዚህ አልፀናችም። የአባትና ልጅ ህይወት አደጋ ላይ መሆኑን የተናገረችበት ጊዜ መዘግየቱን አውቃለች። እስካሁንም በህይወት ይገኛሉ አላለችም ነበር። ዶክተር ናትናኤልን በህይወት ብታገኛቸውም ስለንግሥት የምታውቀው ነገር የለም። ምንአልባትም፣ በአሁኗ ደቂቃ በህይወት ላትኖር ትችላለች። ሲሳይ ፈራች። ንግሥት በአሁኗ ደቂቃ ህይወቷ ቢኖርም፣ አባቷ ገብተው እስኪያስጠነቅቋት ድረስ ሊዘገይ ይችላል። ደውላ ልትነግራት አሰበች። ወደ ቢሮዋ ደወለች፣ ልታገኛት አልቻለችም። ከሥራ ከቀረች በርከት ያሉ ቀናት እንደሆኑ ተነገራት። መኖሪያ ቤቷ ደወለች።

ንግሥት ስልኩን አነሳች።

## 53

ከሲሳይ እንደበት የሚያስፈራውን ዜና እንደሰማች ያለችበትን ረስታ ነበር በድንጋጤ። 'ሊገልሽ ፎክሯል' የሚሉት ቃላት እንደተወነጨፈ ቀስት ልቧን ሲወጉት፣ አእምሮዋን ሲጠቀጥቁት፣ መላ አካሏን ሲበሳሱት ሠላሳ ደቂቃዎች አልፈዋል። አሁን እሷነቷን ነፃ አውጥታለች። ከእንግዲህ ደግሞ ህይወቷን ከአደጋ ውስጥ ለማውጣት መወሰድ ስላለበት ርምጃ ማሰላሰል ጀመረች።

'ግን ለምንድን ነው ላለመሞት የምጥረው?ድሮውንስ ሞቼአለሁ እኮ! ታዲያ ሞት ምን አስፈራኝ? ለየትኛው የሚያጓጓ ህይወት ነው ይሄ ሁሉ ድንጋጤና ፍርሀት? ለእኔ ከእንግዲህ ወዲህ የቀሩኝ ጥቂት ወራት ወይም ዓመታት ናቸው። መሞቱን ላወቀ ሰው ፍርሀት ምኑ ነው? አሁን ኖርኩ አልኖርኩ ምን አተርፋለሁ? ምን አጣለሁ? ቀናት ባለፉት ላይ በተከቡ ቁጥር ነፍስና ሥጋዬ የሚለያዩበት ደቂቃ በመቅረቡ የሚመጣው ሥጋት ካልሆነ ምን ጥቅም ይኖራል? ለምን እኖራለሁ? ሰው ለመሞት ይኖራል? ሞትን መፍራት የለብኝም። እንዳውም በኤድስ በሽታ ሞተች ከምባል በጥይት ሞተች መባል ትንሣኤ ነው።' አለች ለራሷ።

በዚህ ሀሳቧ አልፀናችም። በርሷ ተሎ መሞት የሚጎዱት ሰዎች ታይዋት። መጀመሪያ፣ አባትዋ ዶክተር ናትናኤል፣ በዚህች ዓለም ያለቻቸውን እሷነቷን ሲያጡ፣ ምን ዓይነት ህይወት ሊመሩ እንደሚችሉ ገመተች። ልጅ ብቻ ሳትሆን፣ እንደ ሚስት አማካሪ፣ እንደ እናት ርሳቸውን ተንከባካቢ ናት። አባት፣ አጎት፣ አክስት፣ እህት፣ ወንድም፣ ሩቅ ዘመድ፣ ጎረቤት ሁሉንም ሆና ያኖረቻቸው እርሷው ናት። እርሷን ቢያጡ በህይወት የሚኖሩ አልመሰላትም። በርሷ ሞት የሚጎዳ መስሎ የታያት ሌላ ሰው ዳንኤል ነው። በጣም እንደሚወዳትና እንደሚያመልካት ታውቃለች። ህይወትን በደስታ ለመኖር የርሷ ጥገኛ መሆን ጀምሯል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ላይ ሳለ፣ ድንገት ከመቃብር በታች ስትሸሸገው ህይወት ሳትጨፈግግበት አትቀርም። ለጥቂት ጊዜያትም ቢሆን፣ ሀዘን መዳፎቿ ውስጥ አስገብታ እንደገባስ ቆሎ ሳታሽው አትቀርም። የሁለቱም ሰዎች ሀዘን የዳሰሳቸው ገጽታዎች፣ ከፊት ለፊቷ መጥተው ተማፀኗት። ልቧ ፈራ። ሳታስበው መኖር ተመኘች። ህይወቷ መርዘም እንዳለበት ተረዳች። እናም፣ ከፊት ለፊቷ ቆሞ 'እንኳን ደህና መጣሽ !'በሚል ስሜት እጁን የዘረጋላትን ሞት የምታባርርበትን ዘዴ አሰላሰለች። የእጅ ሰዓቷን አየችና ወደ ስልኩ ተጠጋች። ቁጥሮች አዞረች።

"ሀሎ !" ከወዲያኛው ጫፍ ስልኩ ተናገረ።

"ዳንኤልን ፈልጌ ነበር።"

"ዳንኤል የለም።" አሉ ስልኩን ያነሱት የዳንኤል አባት።

"አልገባም ዛሬ?" ስትል ጠየቀች።

"አዎ! ማንልበል?"

"ንግሥት ነኝ።"

"እ!... አንቺ ነሽ !... " አሉ የዳንኤል አባት በማንጓጠጥ ዓይነት።

"አዎ።" አለች፣ አባትየው መሆናቸውን ገምታለች።

"ለምን ደወልሽ?" ሲሉ የቁጣ ቃል ባለው ድምጽ ጠየቁ።

"ለጥብቅ ጉዳይ ፈልጊው ነው።"

"እሱ ከአንቺ ጋር ምንም ጉዳይ እንደሌለው አታውቂም! አንዱን ብቸኛ ልጁን ብትተይው ጥሩ ነው !እሱ ከእንግዲህ ወዲያ ከአንቺ የሚፈልገው ምንም ጉዳይ የለም!ሰማሽ! ምንም የሚያገናኛችሁ ጉዳይ የለም! ትሰሚያለሽ ?"

በድንጋጤ ከማድመጥ ሌላ የተናገረችው ነገር አልነበረም። ጆሮዋ ላይ የሰሙችው የዳንኤል አባት ሳይሆኑ፤ የስልክ ማናገሪያው እንደሆነ ሁሉ ቶሎ ከጆሮዋ አላቀቀችና አስቀመጠችው። ዝም ብላ ቁጭ አለች፤ የምታደርገው ጠፋት። ከዳንኤል ጋር በሰደራ የመዝናናት ፕሮግራም ካለፉ በኋላ ተደብቆ የነበረው ሆደ ባሻነቷ ብቅ አለ። ከፋት። ጓደኛዋ ሆና የሰነበተው ዕንባዋ ድንገት እንደማዕበል መጣና ፊቷን አጠበው። ምርር ብላ አለቀሰች።

## 54

ዶክተር ናትናኤል ዘለቀ መኖሪያ ቤታቸው እንደገቡ ሽዋዬን ወፍራም ቡና እንድታፈላላቸው አዘዙና ወደ መኝታ ክፍላቸው ገቡ። ንግሥት መኝታ ክፍሏ ውስጥ መሆኗን ቢያውቁም፤ ሲሳይ ስለነገራቸው ጉዳይ ሊያጫውቷት አልፈለጉም- ቡና እስኪጠጡ ድረስ። ኮታቸውን አውልቀው ቁምሳጥን ውስጥ በተንጠለጠለው መስቀያ ላይ ካስቀመጡ በኋላ፤ አልጋቸው ላይ ጋደም አሉ። ዓይኖቻቸውን ኮርኒስ ላይ አሳርፈው ሲሳይ የነገራቸውን ማስጠንቀቂያ እንዴት ለንግሥት እንደሚነግሯት ማሰላሰል ያዙ። ነገሩ ከባድ መሆኑ የገባቸው እየቆየ ነው። ይህንን ጉዳይ ለንግሥት መንገር እንደማርዳት ያህል ነው የቆጠሩት- የራስ መርዶ። ሸሽቶ የነበረው ጭንቀቷን እንደገና ማምጣት መሆኑን ሳይረዱት አልቀረም። ይሁንና መናገሩ፤ ጉዳዩን ሳታውቅ ከሚመጣባት ጉዳት የተሻለ ሆኖ አግኝተውታል። ቢሆንም ነገሩን በቀጥታ ነግረዋት ሊያስጨንቋት አልፈለጉም።

የመኝታ ቤታቸውን በር ከፍታ ገባች ሽዋዬ። ኢንቢሉን ይዛለች። "ዶክተር፤ ግሩም የሚባል ሰው ይህንን ደብዳቤ አምጥቶሎታል።" ብላ ሰጥታቸው ወጣች።

ዶክተር ከአልጋቸው ላይ ቀና ብለው ማንበብ ጀመሩ-- መጀመሪያ አድራሻውን። የደብዳቤውን ፀሐፊ ወዲያው አወቁ። የት



እንደጠፋች ማወቅ ችግራቸው ነበር። በቅርብ ሆነው ስለርሷ አንዳንድ ነገሮችን ቢያጠኑ ደስ ባላቸው ነበር። ከጥቂት ቀናት በኋላ ውጤቱ ከሚታያቸው የምርምር ፍሬ ሁለተኛ ተጠቃሚ ሊያደርጓት ይፈልጋሉ- ከንግሥት ቀጥሎ። ደብዳቤውን ማንበብ ጀመሩ።

ለውድ ዶክተር ናትናኤል! እንደምን ሰንብተዋል? እኔ በጣም ደህና ነኝ። ሀያሉ እግዚአብሔር ይመስገነው! ዶክተር፤ ለጊዜው ድምጼ ጠፍቶ መቆየቴ ሳያስገርምዎት አይቀርም። እኔ አሁን ያለሁት ፍጹም ሰላምና ደስታ ከገኘሁበት ቦታ ነው። አሁን ካለሁበት ቦታ የመንፈስ ህክምና አግኝቼ ድኛለሁ። እስካሁን ድረስ ተነፍጌው የቆየሁትን ሰላም በማግኘቴ፤ እጅግ ከፍተኛ ደስታ ተሰምቶኛል። ዛሬ ከታላቁ አምላኬ ጋር በየቀኑ የምገናኝበት ቦታ ውስጥ ነው ያለሁት። እድሜ ለርስ! ለአምላኬ ፀሎት እንዳደርስና ፊቴን ወደ እርሱ እንዳዞር ሀሳብ የሰጡኝ እርስዎ ኖት። አሁን ደብረሊባኖስ ከሚገኘው ገዳም ውስጥ እገኛለሁ። ከእንግዲህ ወዲያ፤ ለአለማዊው ኑሮ ግድ ባይኖረኝም፤ ሥጋዊ አካሌን አድኜ ለተጨማሪ ዓመታት እዚሁ ሆኜ አምላኬን ለማገልገል ትልቅ ምኞት አለኝ። መድሀኒት እየፈለሰፉኩ ነው ብለውኝ ነበር። ከምን ደረሱበት? እንደተሳካሎት የመጀመሪያ ተጠቃሚ እንደሚያደርጉኝ ርግጠኛ ነኝ። የእርሶ ባይሳካ፤ በሌላ ሀገር የተገኘ እንደሆነም፤ የተቻሎትን አድርገው የምድንበትን ዘዴ እንደሚፈልጉልኝ ታላቅ እምነቴ ነው።

አድራሻዎን ባለማወቄ ነው፤ በግሩም በኩል የጻፍኩልዎ። ከሳውቁኝ ግን፤ በቀጥታ እጽፍሎታለሁ። ለልጆ-በሚን ረስቼዎለሁ- የእግዚአብሔር ሰላምታ ያቅርቡልኝ። እግዚአብሔር ከእርሶ ጋር ይሁን!

ፊርማ
ሺታዬ ጋሻቸው።

ዶክተር ናትናኤል አንብበው ከጨረሱ በኋላ፤ አጣጥፈው ከአልጋቸው ጎን ካለው ኮመዲኖ ላይ አስቀመጡት። ስለልጃቸው ማሰብ ጀመሩ። ሺታዬ ያለችበት ቦታ ለንግሥት ሰላም የሚሰጥ መሸሸጊያ መሆኑን አመኑበት። ይህንኑ ሀሳብ ሊያዋዩዋት ፈለጉ። የመድሀኒቱን ውጤት እስኪያውቁ ድረስ፤ የመንፈስ እረፍት ታገኝ ዘንድ ሊረዳት የሚችል ሆስፒታል ይኸው ገዳም መሆኑን ቢረዱም፤ ለመንገር ፈሩ። ልጃቸው ገዳም ከገባች በኋላ ላትወጣ ትችላለች የሚል ስጋት

አደረባቸው። ሽታዬን የማረካት ሀይል በልጃቸው ላይ ከተጋባ፣ የንጉሴት የልጅ ልጅ ማየት ተግባር ከንቱ ይሆናል ብለው ገመቱ። በመንፈሳዊ ሀይል የተሸነፈን ሰው ፈልቅቆ በማውጣት፣ ዓለማዊ ማድረግ አስቸጋሪ እንደሚሆን ያምናሉ።

ይሁንና፣ በዚህ አልፀኑም። ደብዳቢውን ሊያስነብቧት ወደ ንግሥት መኝታ ቤት አመሩ።

## 55

ሽዋዬ የመኝታ ክፍሏን ክፍታ ስትገባ፣ ንግሥትን አልጋዋ ላይ ጋደም ብላ መጽሐፍ ስታነብ አገኘቻት።" ንግሥትዬ! ሰው ይፈልግሻል።" ብላ ሄደች።

"ማ?"አለች፣ ትንሽ ግንባሯን ቋጥራ። ዳንኤል ይሆናል እንዳትል፣ እርሱ ሀገር ውስጥ የለም። ለሥራ ወደ ፈረንሳይ ከሄደ ሦስት ሳምንታት ተቆጥረዋል። የሚመጣበት ቀን ከአንድ ሳምንት በኋላ እንደሚሆን ስለነገራት፣ እርሱ እንደማይሆን ታውቃለች። ከርሱ ሌላ የወንድም ሆነ የሴት ጓደኛ እጥታ ብቻዋን ከሆነች ቀናት አልፈዋል። ግንኙነቷ ቤት ውስጥ ካሉ ሰዎችና ውጭ ደግሞ ፣ ከዳንኤል ብቻ ሆኗል። የመሥሪያ ቤት ጓደኞቿም ሥራዋን ከተወች ጊዜ ጀምሮ ርግፍ አድርገው የተዋት መስለዋል።

የእጅ ሰዓቷን አየች። ከምሽቱ አንድ ሰዓት ተኩል ሆኗል። በዚህ ጨለማ የፈለጋት ሰው ማን እንደሆን ልትገምት አልቻለችም። ዶክተር ናትናኤል አደገኛነቱን በሲሳይ ምስክርነት ለአለቃው ነግረው አርአያ ለጊዜው በቁጥጥር ሥር እንዲውል ባያስደርጉ ኖሮ፣ አርአያ ሊገላት እንደመጣ ገምታ ትደነግጥ ነበር። አርአያ እንደማይሆን ርግጠኛ ሆነች። ይሁንና በእርግጠኛነቷ አልፀናችም። አርአያ ተፈቶ ሊመጣ እንደሚችል ጠረጠረች። አርአያ ለጊዜው እንዲታሰር ያደረጉት መኮንን፣ መጀመሪያ ላይ ኢሰብአዊ ነገር መሆኑን ለአባቷ በማስገንዘብ በቁጥጥር ሥር እንዳይውል ተቃውመው ነበር። ማን ያውቃል፣ አሁን በቀድሞው ሀሳባቸው በመጽናት ፈተውት እንደሆነስ?

ንግሥት ፈራች። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የአባቷ የምርመር ውጤት በመዘግየቱ ተበሳጭታ ራሷን ለማጥፋት እንዳልተመኘች ሁሉ አሁን ፈራች። ሞት ሩቅ መስሏት ነበር። አሁን ቀርቧት ሲመጣ፣ የምትገባበት ጉርጓድ ጠፋት። ላለመውጣትና ለመደበቅ ወሰነች። በዚህ ውሳኔዋ አልፀናችም። ስታስበው አርአያ እርሷን ወይንም አባቷን



ለመግደል መዛቱን አስታወሰች። አባቷ በእርሷ ሳቢያ እንዲቀጡ አልፈለገችም። ጥቃቱን እርሷ ባመጣችው መዘዝ፣ በእርሷ ላይ ብቻ እንዲያርፍ ወሰነች። ጋቢ ደርባ ከዋናው ቤት ወጥታ ወደ ግቢው በር ተጠጋች።

ግቢው ጭር ብሏል። ሌላ ጊዜ ያደምቁት የነበሩ ታካሚዎች ዛሬ የሉም። የዶክተር ክሊኒክ ዝግ በመሆኑ፣ በግቢው ውስጥ ያሉት አምፑሎች ሁሉም አልበሩም። አባቷ በጥናትና ምርምር ክፍላቸው ውስጥ መሆናቸውን አውቃለች።

ፈራ ተባ እያለች፣ ወደ በሩ ተጠጋች። አንድ አጠር ያለ ወጣት ገርበብ ብሎ ከተከፈተው በር ላይ ቆሞ አየች።

እርሱም ተጠጋት። እጆቹን ኪሶቹ ውስጥ ከቷል።

ንግሥት ማንነቱን ወዲያው ልታውቅ አልቻለችም። የዳንኤልን ስም ሲያነሳላት ነው፣ የት እንዳየችውና ማን እንደሆን ያስታወሰችው። የዳንኤል የእኅት ልጅ!

ተገቢውን ሰላምታ ከሰጠችው በኋላ፣ "ዳኒ መጣ እንዴ?" አለች በጉጉት።

"አይ፣አልመጣም። ይህንን ደብዳቢ ዛሬ በመጣ ሰው ልኮልሽ ልሰጥሽ ነው የመጣሁት።" አለና አንድ ፖስታ አውጥቶ ሰጣት።

ዳንኤልን ያገኘች ያህል፣ ተንገብግባ ተቀበለችው። "ቤቴን እንዴት አወቅሽው?" ስትል ጠየቀችው።

"አንድ ጊዜ፣ ዳንኤል ሊታከም እዚህ የመጣ ጊዜ፣ አብረን ነበር የመጣነው። ያን ጊዜ ስላየሁት አልጠፋኝም።"

ንግሥት ኢንቬሎፑን ሳመችውና ልጁን አመስግና ገባች።

'ድንቄም ተሰሟል!' አለና በሆዱ መንገዱን ቀጠለ። ንግሥት ደብዳቢውን አሁኑኑ እንደምታነበው አውቋል። እርሷን ከዳንኤል ለማራቅ እርሱ፣ የዳንኤል አባትና እናት የቀየሱት ዘዴ ምን ያህል ውጤታማ እንደሚሆን ግን ሊገምት አልቻለም።

መኝታ ቤቷ እንደገባች ፖስታውን ቀደደችው። ደብዳቢውን ዘረጋች። ቁልጭ ባለ የእጅ ጽሑፍ የተጻፈ ነው። የዳንኤልን የእጅ ጽሑፍ አይታ አታውቅም።

"ውብ አጣጣል!" አለችና ማንበብ ቀጠለች።

ውድ ፍቅረኛዬ ወይዘሪት ንግሥት! የተከበረው የናፍቆትና የፍቅር ሰላምታዬ ከፈረንሳይ መዲና ከፓሪስ ይድረስሽ !

ንግሥትዬ! እወድሻለሁ። አፈቅርሻለሁ። አመልክሻለሁ። ከዚህ የተነሳ እስከ ዕለተ ሞቴ ድረስ ከአንቺ ጋር በትዳር ዓለም ለመኖር ፍላጎት እንዳለኝ ታውቂያለሽ። ይሁንና የእኔን ፍላጎት የሚያሰናክሉ አንዳንድ ነገሮች እየተፈጠሩ ነው። እስከአሁን ድረስ መሰናክሎቹን እያለፍኩ በአሸናፊነት በመወጣት አንቺን በልቢ ውስጥ እንዳለሽ ለማቆየት ብሞክርም አልቻልኩም።

ንግሥቴ! እኔ የተፈጠርኩት የራሴን ህይወት ለመኖር እንዳልሆነ የተረዳሁት አሁን ነው። አሁን ባለሽበት ሁኔታ እንደምወድሽ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች ነግሬሻለሁ። ይሁንና፣ ይህንን ሁኔታ አባትና እናቴ ሊቀበሉት አልቻሉም። ግን እንደነገራቸው አላውቅም። በኤድስ በሽታ መለከፍሽን አውቀዋል። ከሶደሬ ከተመለስን በኋላ ስለነገሩ እውነትነት ሲጠይቁኝ ትክክለኛውን ነግሬያቸዋለሁ። አንቺን በአለሽበት ሁኔታ እንደምወድሽና አብረን መቆየት እንዳለብን ነግሬያቸው ነበር።ሊቀበሉት አልቻሉም። እኔም በተቻለኝ መጠን ላሳምናቸው ሞክሬ ነበር። አልቻልኩም። በብዙ ነገሮች ሊያስፈራሩኝ ሞክረዋል። አሁን የምመራውን የንግድ ድርጅት እንደምነጠቅ አስጠነቀቁኝ። እኔ ግን ልሸነፍላቸው አልቻልኩም ነበር። ድርጅቱን ቢነጥቁኝም በእውቀቴ አንዱ ቦታ ተቀጥሬ በማገኘው ገንዘብ፣ ከአንቺ ጋር ለመኖር ወስኜ ነበር። በዚህ በመጽናቴም ከአባቴ ከባድ ተግሳጽ ደርሶብኛል። በእኔ የተነሳም አባትና እናቴ ተጋጭተዋል። እናቴ አቋሜን ደግፋ ሳይሆን በእናትነት አንጀቷ ከእኔ ጎን በመቆሟ፣ ከቤት ወጥታለች። ለአያሌ ዓመታት ፍቅርና ሰላም ነግሶበት የነበረው ቤት እንደ በረዶ ቀዝቅዟል። አባቴም አንቺን ትቼ፣ የቤተሰቡን ፍቅርና ሰላም እንድመልስ ተማጽኖኛል። ከላይ የጠቀስኳቸው ማስፈራሪያና ግፊቶች ቢጫኑኝም፣ ጫንቃዬ ተቋቁሟቸው ነበር። ለአንቺ ፍቅር ስል ያልቻልኩት ነገር አልነበረም። ሆኖም፣ እናቴ በስተርጅና ከሞቀ ቤቷ፣ እንደ አሮጌ ቁና ተጥላ፣ አይታው በማታውቀው የችግር ልምጭ ስትገረፍ የማየቱ ተግባር፣ ጫንቃዬንና ትዕግስቴን እያሳሳው መጣ። እናቴ ለእኔ ለአንድ ልጇ ፍላጎት ስትል ባደረገችው ግጭት ሳቢያ፣ በመቅመስ ላይ ያለችው የችግር ኑሮ በቀላሉ የማየው ሆኖ አላገኘሁትም። ስለዚህ፣ ስለ ጉዳዩ ከአንቺ ጋር መወያየትና መፍትሄ መፈለጉ መልካም አማራጭ ሆኖ አገኘሁት። ይሁንና፣ ቀላል ነገር አልሆነልኝም። ፍቅርሽን ከልቢ ውስጥ መንጭቄ ማውጣት አልቻልኩም። ጉዳዩን አንስቼ ላጫውትሽ አልደፈርኩም። በመሆኑም፣ አንቺን መሸሽ ጀምሬያለሁ - ስለተፈጠረው ጉዳይ ከመነጋገር ይልቅ። ፈረንሳይ ሀገር ለሥራ ብሄድም ይህን ያህል ጊዜ የሚያቆይ አልነበረም፣ የአንቺን የቅሬታ ፊት ላለማየት ስል ነው የምመጣበትን ጊዜ ለማራዘም የተገደድኩት።

ንግሥትዬ! ከላይ በጠቀስኩልሽ መሠረት ከፊቴ ያለውን ችግሬን የተረዳሽ ይመስለኛል። በዚህ መሠረት፣ ልቤ እያፈቀረሽ ለቤተሰቤ ፍቅርና ሰላም ስል ልለይሽ ተገድጃለሁ። ችግሬን ስለምትረጅልኝ እንደማትቀየሚኝ ርግጠኛ ነኝ። መልካሙን እመኝ ልሻለሁ።

ያንቺው የቀድሞ ፍቅረኛ
ዳንኤል ፈጠነ
ከፓሪስ

ያነበበችውን ደብዳቤ ልታምን አልቻለችም። ደጋግማ አነበበችው። መልዕክቱ ያው ነው። በዚያ እንደማር በሚጣፍጠው አንደበቱ፣ ከፊት ለፊቷ ቆሞ 'ትቼሻለሁ!' ያለ ነው የመሰላት። በኤድስ ቫይረስ ተይዘሻል ተብሎ የተነገራትም ቀን እንዲህ አልደነገጠችም ነበር። አሁን ገና ነው መሞቷን የተረዳችው። እስከዛሬ ድረስ የህዋሱ ተሸካሚ ነሽ ተብሎ ቢነገራትም፣ እውን መስሎ አልታያትም ነበር። ህልም፣ ኸረ እንዳውም መባነን የሚያባርረው መጥፎ ቅዠት መስሎ ነበር ያሚሰማት። ግን ተሳስታ እንደነበር ተረዳች፣ በእውን አለም ውስጥ መሆኗን ልብ የሚፍቀው ደብዳቤ ነገራት። እስካሁን ስትኖርለት የነበረው የዳንኤል ፍቅር መና ሆኗል። ከእንግዲህ፣ በዚህች ምኗም ባልታወቀ ምስጢር በሆነች አለም ውስጥ፣ የምትኖርበት ምክንያት ያለ አልመሰላትም። ሰውን እንዲኖር የሚያስገድደው ነገር ደስታ ነው። ደስታ ደግሞ ከፍቅር ይገኛል። ፍቅር ከሌለ ደስታ የለም። ደስታ ከሌለ ህይወት የለም።

እኚህ መከረኛ ብቸኛ አባቷ በዓይነ ህሊናዋ ከፊት ለፊቷ መጥተው ጉብ አሉ። ከእርሷነቷ ጋር በመወቃቀስ ዓይነት ውይይት የጀመሩ ሆኖ ተሰማት።

'ለምን ተስፋ ትቆርጪያለሽ የእኔ ልጅ?'

'ህይወትን ስኖርለት የነበረው ሰው ከዳኝ! ከእንግዲህ መኖር አልችልም!'

'ተይ እንደእሱ አይደለም። ህይወትን ትኖሪ የነበረው እኮ ለዳንኤል ብቻ አይደለም። ለእኔ ለአንድ አባትሽም ጭምር ነው። እኔ

አባትሽ ያለ አንቺ መኖር አልችልም እኮ። አንቺ ነሽ እስትንፋሴ። ሥጋዊ አካሌ ናትናኤል ቢሆንም፣ ነፍሴ እኮ አንቺ ነሽ።'

'እስከመቼ ድረስ ለሰዎች ስል እኖራለሁ? ህይወትን እኮ ሰው ሁሉ ለራሱ ነው የሚኖራት። አንዱ ለሌላው አይኖርም አባዬ።'

'ውሸት ልጄ። የእኔ መልፋት፣ መድከም፣ ያለ ዕረፍትና ዕንቅልፍ ከወረቀት ጋር መታገል ሌላውን ለማኖር አይደለም? አንቺና መሰል ጓደኞችሽን በህይወት ለማቆየት አይደል?'

'ነው። ግን ድካምና ዕረፍት ማጣት ብቻ ዋጋ የለውም። ተግባርና ውጤት ይፈልጋል። አንተ ግን ዘግይተሀል። ህይወትን ለራስህ ብቻ በመኖር አይደል የአንተን የጭንቅላት ውጤት በመጠባበቅ ላይ ያለነውን ምስኪኖች ችላ ያልከን?'

'አይደለም። ችላ ማለት እኮ አይደለም። ህይወትን የማዳን ተግባር ጊዜ ይጠይቃል። በችኮላ የሚሆን ነገር የለም። ጊዜው ሲደርስ ይሆናል።'

'አይ !ክልብ የሚወጾት ፍትረኛ ከከዳና ከሸሸ በኋላ ቢደርስ ምን ዋጋ አለው? ፍቅርን ካጡ በኋላ ተአምር ቢሠራ ምን ይረዳል?'

'ተይ ልጄ። እንደሱ መሆን አይገባም፣ ትንሽ ታገሺ!'

'አልታገስም!'

'እህ ምን ልትሆኚ?'

'የምሆነውን እኔ አውቃለሁ!'

እንደሚጥረዱ ቢላዎች በአእምሮዋ ውስጥ የሚፋጩት ሀሳቦች የፈጠሩባት መንፈስ ለዕንባዋ በር ቀደደ። እንዚያ ትላልቅ ዓይኖቿ እንደወትሮው አነቡ። የዛሬው ግን ውሀ መልክ ያለው ደም ነበር...

## 56

ከምሽቱ አራት ሰዓት ሆኗል። ንግሥትን ዛሬ አላዩዋትም። በሽታዋን ካወቀችበት ቀን ጀምሮ በየጊዜው መኝታ ክፍሏ በመሄድ ሲያጫውቷት ሲያጽናኗት ቆይተዋል። ዛሬ ሥራ በዝቶባቸው በጊዜ አላዩዋትም። እናም፣ ዛሬ የመጣው ደብዳቤ በርሷ ላይ ያደረሰውን ስሜት አላዩም። እስከ ዛሬ ድረስ ሲደክሙለት የነበረው ምርምር ውጤት በዚህች ምሽት ይታወቃል። የኤች አይ ቪ ቫይረስ ሰለባ የሆነውን የአለምን ህዝብ ነፃ ማድረግ መቻል አለመቻላቸው የሚለየው



አሁን ነው። በረሀብ፣ በጦርነት እንዲሁም በሩጫ ውድድር አሸናፊነት ስትታወቅ የነበረችው አገራቸው የዓለም መድህን ሆና ብቅ እንድትል የሚያደርጋት መፈወሻ ውጤት ዛሬ ነው የሚረጋገጠው። ለዚህም ነው ዶክተር ናትናኤል ከቀኑ አሥራ ሁለት ሰዓት ጀምሮ ከጥናትና ከምርምር ክፍላቸው ውስጥ ሆነው የምርምራቸውን የመጨረሻ ውጤት ሲከታተሉ የቆዩት።

ከሰዓታት በኋላ ዶክተር ናትናኤል የድካማቸውን መጨረሻ አወቁ። አእምሮአቸው ውጤቱን ሲረዳ፣ ዓይኖቻቸው ብልጥጥ አሉ። ግንባራቸው ላብ ቋጠረ። ፊታቸው ለጊዜው ትርጉሙ ምን እንደሆነ ሊያስረዳ የማይችል ስሜት አስነበበ። ለጠጥ ብለው ወንበራቸውን ተደገፉና ጣራ ጣራውን አፍጠው አዩ። አምላካቸውን ሊረግሙ ይሁን ሊያመሰግኑ ባልታወቀ ስሜት። ምንም አልተናገሩም። ባደረባቸው ስሜት የደም ብዛታቸውና የልብ ድካማቸው ሞት ደጃፍ እንዳያደርሳቸው ያሰጋል።

ድንገት ከመቀመጫቸው ተነሱና ጣራ ጣራውን አዩ። እጆቻቸውን እንደ ህንድ ፀሎት አድራጊ አገጣጥመው ከንፈሮቻቸውን አላወሱ። "ተመስገን! ተመስገን! አምላኬ ሆይ! ትልቅ ምስጋና ይድረስህ!" ሲሉ የደስታ ቃላት አወጡ። የመጨረሻውን ዓረፍተ ነገር ሲናገሩ እጅግ ጮኸው ነበር። ወዲያው መሬት ሳሙ።

በዚህች ደቂቃ፣ በዓለማችን በብዙ ሺህ ለሚቆጠሩ የኤድስ በሽተኞች በሚሊዩን ለሚቆጠሩ የቫይረሱ ተሸካሚዎች፣ መድሀኒት ከኢትዮጵያ ምድር እንደተገኘ የሚያውቁት ዶክተር ናትናኤል፣ ፈልሳፊው ኢትዮጵያዊ ሳይንቲስት ብቻ ናቸው! ኢትዮጵያ፣ በህክምና ሳይንስ ዝና ያገኙትን በጣት የሚቆጠሩ ልጆቿን ቁጥር ከፍ አደረገች። ደስታው ለሳይንቲስቱ ብቻ ሳይሆን፣ ለመላው ኢትዮጵያውያንና ለተቀረው የዓለም ሕዝብ ነው።

ዶክተር ናትናኤል ወደ ወንበራቸው ተመልሰው ተቀመጡ። ምን እንደሚያደርጉ ግራ ገብቷቸዋል። ይህንን ዜና ቀድመው ለማን ማሳወቅ እንዳለባቸው ጨነቃቸው። የክሊኒካቸው ረዳት ለሆነው ለዶክተር ካሳሁን ሊደውሉለት አሰቡ። ከዚያም ለመሥሪያ ቤት ጓደኞቻቸው። ከዚያስ? ለማን እንደሚነግሩ ግራ ገባቸው። በአሁኗ ደቂቃ በመላው ዓለም ውስጥ ለሚገኙ ህሙማን ሁሉ ነግረው ይህችን ሌሊት በጥሩ ተስፋ እንዲያድሩ ማድረግ ቢችሉ እጅግ ደስ ባላቸው ነበር! ድንገት ከወንበራቸው ብድግ አሉ። ከሁሉም-ከሁሉም፣ የምርምር ውጤታቸውን ስትናፍቅ ለቆየችው ልጃቸው መንገር እንዳለባቸው ምን

እንዲዘነጋቸው ሊገባቸው አልቻለም። ይህንን ውጤት ከርሳቸው ጋር ሁለተኛ ሰው ሆና መጀመሪያ መስማትና እስካሁን ርቋት የነበረውን ፅንቅልፍ እንድታገኝ መደረግ ያለባት ንግሥት መሆኗን አመኑ። እየሮጡ ወደ መኝታ ክፍሏ አመሩ። ከጥናትና ምርምር ክፍላቸው ጀምሮ "ንግሥቴ! ንግሥቴ !"እያሉ መኝታ ክፍሏ ውስጥ ገቡ። ዓይኖቻቸውን አልጋዋ ላይ ወረወሩ።

የለችም።

ተጣሩ።

በክፍሉ ውስጥ ምንም ሊያገኙ አልቻሉም።

ወደ ሌሎች ክፍሎች እየተዘዋወሩ ተጣሩ። ድምጿ አልተሰማም። ሽዋዬ ወደምትገኝበት ተጓዳኝ ክፍል ሄዱ። ሽዋዬ ለመተኛት አልጋዋ ላይ በመውጣት ላይ ነበረች። የዶክተርን ድምጽ ስትሰማ ከፈተችላቸው። ንግሥት መኝታ ክፍሏ ውስጥ እንደነበረች ብቻ ነው የነገረቻቸው ። ወደ መኝታ ክፍሏ ተመለሱ። ንግሥትን ሊያገኟት አልቻሉም። በምትኩ፣ አልጋዋ ላይ ሰው እንዲያገኘው ተደርጎ የተቀመጠ ደብዳቤ መኖሩን ተረዱ። ለቀም አደረጉና ማንበብ ቀጠሉ።

ውድ አባዬ!ዛሬ ዓይኖችህን አላየሁዋቸውም። እንደምን ዋልክ? በዚህ ደብዳቤ የማትፈልገውን ነገር ስነግርህ በጣም አዝናለሁ። ወድጄ አይደለም። ተቸግሬ ነው። የችግሬ መነሻ ምን እንደሆነ ለአንተ መንገር የሚያስፈልግ አይደለም። በውስጤ ያለው ህዋስ ከቆሙት በታች ከሞቱት በላይ አድርጎኝ ኗሯል። በሥጋት አኝኮኝ ቆይቷል። ጉዴን ከነገርከኝ ቀን ጀምሮ እኔ ሳልሆን ሬሳዬ ነበር በዚህች ዓለም ላይ ሲኖር የነበረው። ነፍሴ ሳትወጣ ከሞትኩ ቆይቻለሁ። ነፍሴ ከሥጋዬ ሳትላቀቅ የቆየችው ለሁለት ነገሮች ነበር። ለአንተና ለዳንኤል ፍቅር። እንዱን እጥቼያለሁ። ዳንኤል በደረሰብኝ ችግር ከዶኛል። ለአንተ ፍቅር ስል መኖር ባቅድም፣ የሚሳካልኝ ሆኖ አልታየኝም። እኔ ባደረስኩት በደል ሻምበል አርአያ የሚባል ሰው ሊገድልህ ይፎክራል! እኔንም ሊገድለኝ ይፎክራል። የእኔን ባደረገው በወደድኩት። ሆኖም እጅግ ዘግይቶብኛል። በአንተ ላይ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ በህይወት ሆኜ ማየት አልፈለኩም። በአጠቃላይ ይህችን ዓለም ለመሸሽ ተነስቻለሁ። ከዛሬ ጀምሮ እንገናኛም፣ አባዬ። በአካል ሳልሰናበትህ ከዚህች ዓለም በመሰወሬ አዝናለሁ።

ልጅህ ንግሥት ናትናኤል



በድንጋጤ በድን ሆነው ቀሩ። ልባቸውም ደማቸውም ሥራቸውን ያቆሙ ያህል ተሰማቸው። ዓይኖቻቸው የተለያዩ ቀለማት ያለው ነገር ማየት ጀመሩ።

ወዲያው አንድ ድንገተኛ ጩኸት ከሌላው ክፍል እያስገመገመ መጣ። "ዶክተር! ዶክተር! "

በደመነፍስ ሽዋዬ ወደአለችበት ክፍል ሮጡ። የመታጠቢያ ቤቱ ወለል በውሀ ተሸፍኗል። ሽዋዬ የውስጥ ልብሷን እንደለበሰች እስከ ቁርጭምጭሚቷ በሸፈናት ውሀ ውስጥ ሆና፣ ዓይኖቿን ለማፈናጠር እንደፈለገች ሁሉ ጉልጉል አድርጋ፣ በሁለት እጆቿ ጭንቅላቷን ይዛ፣ ወደ አንድ አቅጣጫ ስታይ ደረሱ። እየተንቦጫረቁ ገቡና ሁኔታውን አዩ። የመታጠቢያ ገንዳው በውሀ ተሞልቶ ይፈሳል። ፀጉሯ ተበታትኖ፣ ትላልቅ ዓይኖቿ ፈጠው፣ አፏ ተከፍቶ፣ የሌሊት ልብሷን እንደለበሰች ሰጥማ አይዋት ንግሥትን። እጆቻቸውን አጠለቁና ንግሥትን ሊያወጧት ሞከሩ። ህይወት እንዳልነበራት ሲረዱ ድንጋጤው ፊታቸውን ምጥጥ አደረገው። ልባቸው ሥራውን አቆመ። እንደተነፈሰ ፊኛ ሙሽሽ ብለው ወደቁ።

ንግሥት ፀረ ተሀዋስያን መድሀኒት በብዛት በመውሰዷ ሰውነቷ ስለተቃጠለ ነበር ገንዳ ውስጥ የገባችው።

የሽዋዬ ጩኸት አየለ። የምታደርገው ጠፋት። እየሮጠች ወጣች። የግቢውን ጠባቂ ተገኝን እስከትላ መጣች።

ዶክተር ናትናኤል ህይወት ለሰው ልጅ የምታደርሰውን እጅግ ከፍተኛ የሆነ ደስታና ሀዘን በዚህች ደቂቃ ቀመሱ። ህይወት መንታ መልኳን አሳይታ ሸኘቻቸው ወደ ወዲያኛው ዓለም....

ተ ፈ ፀ መ